የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የትግል ውሎ በኢንተርኔት

የተመረጡ ጽሑፎች

ጥንቅር እና አርትዖት

የፌስቡክ ጸረ-አሕባሽ ቡድን

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የትግል ውሎ በኢንተርኔት

የተመረጡ ጽሁፎች

Ethiopian Muslims Online Struggle

Selected Essays

ቅጽ-1

Volume-1

ጥንቅርና አርትኦት

የፌስቡክ ጸረ-አሕባሽ ቡድን

Compiled and Edited By

Anti-Ahbash Group on Facebook

ሰኔ 2004

June 2012

Say 'NO'
To
'አህባሽ'

ማውጫ

አርእስት ገጽ

መግቢያ ……7

የአርታኢያኑ ማስታወሻ ……9

ክፍል አንድ፡በኢትዮጵያዊያን ሙስሊም ወጣቶች የተጻፉ መጣጥፎች……10

Part One: Essays Written By Ethiopian Muslim Youth

1. አሕባሽ ማንነው? ምንድነው? (አጠቃላይ ዳሰሳ)……11
   ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ
2. የፍትሕ ጥያቄያችን ከግቡ እንዲደርስ……16
   የፌሰ ቡክ ጸረ-አሕባሽ ቡድን
3. አሕባሽ ሆይ! የሱስንዮስና የዮሀንስ ዘመን አልፏል!……19
   ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ
4. አሕባሽ፤ ዴቪድ ሺን እና የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ስጋት……21
   ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ
5. አሕባሽና ጽዮናዊው Anti Defamation League……24
   ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ
6. ታሪክ አለን!……29
   ሙኒር አህመድ
7. 1987ን እንደ መስተዋት……33
   የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄት የፊቸር ጸሐፊ ቡድን
8. የሰማዩን እንኳ ተዉልን!……47
   አክመል ነጋሽ
9. የመለስ ዲስኩር ግዝፈትና ግድፈት……51
   አክመል ነጋሽ
10. የመጅሊስ ምርጫ፡ ከ'ግሎባል' ወደ 'ማዘጋጃ'……56
    ቢን ምህ
11. የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴው ጉዞና የሰላማዊ ትግሉ ሁነቶች……60
    ቢን ምህ
12. አንድነታችን- "የዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ" ትልቁ ውጤት……68
    ዑመር አህመድ ረመዳን

13. Ethiopian Muslims and the Ahbash Controversy……72
Muhammad Ali Alula al-Hashimi
14. Growing Muslim Activism and the Ethiopian State: Accommodation or Repression?.....85
Jawar Mohammed
15. "Ahbashism", Government and Ethiopian Muslim Protests…100
Yuunus Hajji Mul'ataa.

ክፍል ሁለት፡ በአሕባሽ ላይ ያተኮሩ ጠቃሚ ጽሁፎችና ፈትዋዎች.....119

Part Two: Important Articles and Fatwas on Ahbash

16. A Sufi Response to Political Islamism: Al-Ahbash of Lebanon.....120
A. Nizar Hamzeh and R. Hrair Dekmejian
17. Al-Ahbash and Wahhabiya: Interpretations of Islam……..143
Mustafa Kabha and Haggai Erlich
18. Islam and Conflict in the Horn of Africa……..174
David H. Shinn
19. Offical Al-Azhar Fatwa on Ahbash……..184
Al-Azhar University
20. Exposing Abdallah al-Harari and His Sect the Ahbash of Lebanon ("Association of Islamic Charitable Projects")……186
Markaz al-Nasr li Ahl al-Sunnah wal-Jamaah, Jakarta, Indonesia

ክፍል ሶስት፡በብዛት የተነበቡ ዜናዎችና የአቋም መግለጫዎች.....205

Part Three: Popular News Articles and Press Releases

21. Ethiopian Muslims Decry Ahbashism Campaign……..206
From OnIslam Website
22. Five Kllled as Ethiopian Muslim Protests Continue……209
From Ethiomedia Website
23. Ethiopian Government, Muslims Clash about Ideology……215
VOA English Website
24. Who Are Al Ahbash? ……..218

From Wired Journalists Website

25. Muslims Accuse Ethiopian Government of Meddling in Mosques……221
From Christan Science Monitor
26. የሃሰት ፕሮፖጋንዳ መደጋገም የእምነት ሙበት ጥያቄን ህገወጥ አያደርገውም!.....226
የሙስሊሙ ህብረተሰብ ያቋቋመው መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ለ10 የሚኒስቴር መ/ቤቶች ያስገባው ደብዳቤ
27. የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ስም ዝርዝር……242

ክፍል አራት፡ የፎቶ ጋለሪ……243

Part Four: Photo Gallery

ክፍል አምስት፡ ጠቃሚ የኢንተርኔት የመረጃ ምንጮች……276

Part Five: Guide to Important Online Resources

A. Guide to Watch/Read Important Online Documents and Media Reports about the Ethiopian Muslims Struggle Against the Ahbashism Campaign……277
B. Important Documents and Video Links…… 279
C. Internet Guide to Ahbash……280
D. Some of the Online Sources That Report About Ethiopian Muslim Struggle……282

መግቢያ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ ጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ሁሉ ለርሱ የተገባ ይሁን፡፡ የአላህ ሶላት (የአክብሮት እዝነት)፤ ሰላምና በረከቱ በመልእክተኛው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እርሳቸውን በቅን ልቦና በተከተሉት ሁሉ ላይ ይሁን፡፡

የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን እንዲወክልና ሀይማኖታዊ እንቅስቃሴዎቻቸውን እንዲያቀላጥፍ ተብሎ በሙስሊሙ ህዝብ ትግል የተቋቋመው **የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት (መጅሊስ)** መሪዎች *"በሀገራችን ለሚታየው የጽንፈኝነት ችግር መድሃኒቱ አሕባሽ የሚባል ቡድን በሚያስተምረው ርዕዮት መጠመቅ ነው"* በሚል እሳቤ ሙስሊሙን ማሸበርና ማሸማቀቅ ከጀመሩ እነሆ አንድ ዓመት ሊሆነው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገሮች ተከስተዋል፡፡ አሳዛኝና አሳፋሪ ኩነቶች ተመዝግበዋል፡፡ ሙስሊሞች ያለ አንዳች ማስረጃ "አሸባሪ" እና "ጽንፈኛ" እየተባሉ ወደ ዘብጢያ ተግዘዋል፡፡ መድረሳዎችና መስጂዶች የ"ጽንፈኞች መፈልፈያ" እየተባሉ ተዘግተዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየግቢያቸው ሀይማኖታዊ ግዴታዎቻቸውን እንዳይወጡ ከመደረጋቸውም በላይ በግለሰብ ቤት ተከራይተው በ"ጀመዓ" (ህብረት) እንዳይሰግዱም ተደርገዋል፡፡ በአሳሳ ከተማ *"በአሕባሽ ፍልስፍና አልጠመቅም"* ያለውን ሰላማዊ ሼኽ ፖሊሶች "ጂሀድ እየቀሰቀሰ ነው" በሚል የሀሰት ውንጀላ ወደ እስር ቤት ሊወስዱት ሲገፈታትሩት *"ሰውዬው ንጹህ በመሆኑ ልቀቁት!"* ብለው የተቃወሙ ንጹሀን ወገኖቻችን የጥይት እራት ሆነዋል፡፡ ከዚያም ወዲህ መከራና ፈተናው እንደቀጠለ ነው- በ*"ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ" (Ahbashism Campaign)*!

ህዝበ ሙስሊሙ ሳይመርጣቸው "ፕሬዚዳንት"፣ "ሊቀመንበር"፣ "ሰብሳቢ"፣ "አለቃ"፣ "ምክትል"፣ "አስተባባሪ" ወዘተ... እየተባባሉ ሲሿሿሙ የነበሩት የመጅሊስ መሪዎች *"ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ"*ን በተግባር ላይ ለማዋል የተነሱት *"ለሙስሊም ዑለማ ስለ ሀጉመንግስታችን ማስተማር አለብን"* ከሚሉት የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የስራ ሃላፊዎች ከተቀናጁ በኋላ ነበር፡፡ በየመድረኩ ሲሰራ የነበረው ግን "ህገ-መንግስት"ን የመናድ ስራ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሀምሌ ወር 2003 በሀረር ከተማ ከተዘጋጀው የመጀመሪያ ዙር ስልጠና ጀምሮ የአሕባሽ ሊቃውንት *"ወሀቢያን አውግዙ፤ እገሌ የተባለው ሼኽ ካፊር መሆኑን አውጁ፣ አቂዳችሁን ለማስተካከል እንደገና ሸሀዳ ያዙ"* እያሉ የሚያወርዷቸው ትእዛዞች በሀገሪቱ ዑለማዎች እንዲፈጸሙ የመንግስት ሀላፊዎችና የጸጥታ ተቋማት ግልጽ አመራር ሲሰጡ ታይተዋል፡፡

ይሁን እንጂ የመጅሊስ አመራሮች ያሰቡት አልሆነላቸውም፡፡ በተራ ጮሌነት ሊሸነግሉት ከሚቃጡት ህዝበ ሙስሊም የገጠማቸው እምቢ ባይነት እነርሱ ያልጠበቁት ዓይነት ነው የሆነባቸው፡፡ ይባስ ብሎም በጥር ወር መግቢያ ላይ የተቀጣጠለውና በዓለም የመገናኛ ብዙሃን

የመነጋገሪያ አጀንዳ ለመሆን የበቃው ሰላማዊ ትዕይንት ብዙ ሚሊዮን ብር የፈሰሰበትን *"ዘመቻ ጥምቀተ ኦሕባሽ"* በአሸዋ ላይ የተገነባ ቤት እያደረገው ነው፡፡

የዘመቻው አስተባባሪዎች *"ኦሕባሽ ነባሩ እስልምና ነው እንጂ መጤ ሀይማኖት አይደለም፤ መጤዎቹ ሰለፊዎች ናቸው"* እያሉ ቢያምታቱም ህዝቡን ማማለል አልቻሉበትም፡፡ በጉያቸው ውስጥ ያቀፉትና መሀል ሰፋሪ ሆኖ አስጨናቂውን ጊዜ ለማሳለፍ የሚጥረው አማኝ እንኳ ሲከዳቸው እያየን ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል የዘመቻው ጠንሳሾች በስልጣን ላይ ያሉትን የመጅሊስ ሹመኞች በሌላ ታማኝ ሀይል ለመተካት *"ምርጫ ይካሄዳል"* ከሚል ድንገተኛ የሽንገላ ውሳኔ ላይ የደረሱት፡፡ ሆኖም ህዝበ ሙስሊሙ በዚህ ሽንገላ በመረታት *"ዘመቻ ጥምቀተ ኦሕባሽ"*ን ለመመከት የገነባውን ህብረት፤ ወኔና ሰላማዊ ጨዋነት አፈር ድሜ ያስግጠዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ኢንሻ አላህ!!

"ዘመቻ ጥምቀተ ኦሕባሽ" ቀጥሏል፡፡ ህዝበ ሙስሊሙም ትግሉን ቀጥሏል፡፡ የዚህ ግብ ግብ መጨረሻ ምን ሊሆን እንደሚችል አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ሆኖም አላህ ሊንከባከበው ቃል የገባለትን ቀጥተኛውን ኢስላማዊ ጎዳና ለክለሳና ብረዛ እንዳማያጋልጠው በርሱ ላይ ሙሉ እምነት አለን፡፡ ጌታችን መጪውን ጊዜ የሰላምና የደስታ ያድርግልን!

አሚን!!

የፌሰ ቡክ ጸረ-ኦሕባሽ ቡድን

የአርታኢያኑ ማስታወሻ

ይህቺ ድርሳን የ*"ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ"*ን የአንድ ዓመት ውጣ ውረድ አትዘግብም፡፡ሆኖም በመረጃ መረብ (ኢንተርኔት) ዘመቻውን ለማከሸፍ ሲደረግ የነበረው ርብርቦሽ ምን ይዘት እንደነበረው በመጠኑ የምታሳይ ልትሆን ትችላለች፡፡ በሌላ በኩል ዘመቻውን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የነበሩት ወገኖች *"ጽንፈኛ ወሀቢያዎች በኢንተርኔትና በፓልቶክ እየተጠራሩ ሁከትና ሽብር ይቀሰቅሳሉ"* በሚል በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚያቀርቡት ክስ አንዳች መሰረት እንደሌለው በተገቢ ሁኔታ ልታስረዳ ትችላለች፡፡

በመጽሀፊቱ የቀረቡት ጽሁፎች በበርካታ ጸሀፊዎችና የፖለቲካ ተንታኞች የተደረሱ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ጽሁፎች ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በ*"ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ"* ላይ ያላቸው ቅዋሜ ነጸብራቆች ናቸው፡፡ አንዳንድ የመንግስት አካላት የ"*ነባሩ እስልምና ምሳሌ ነው"* እያሉ የሚያንቆለጳጳሱትን የ"አሕባሽ" አንጃ አወቃቀርና ጥንተ ታሪክ የሚያስረዱ ሌሎች ጽሁፎችም ተካተዋል፡፡ "አሕባሽ" በዓለም ሙስሊሞች የተላለፈበትን ውግዘት የሚያስረዱ ፈትዋዎችም በመጽሀፊቱ እንዲያዙ ተደርገዋል፡፡ ሙስሊም ወጣቶች መረጃ በሚለዋወጡበት የፌስቡክ መረብ የተለቀቁ ፎቶግራፎችም በትንሹ ቀርበዋል፡፡ የመገናኛ ብዙሃን በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰላማዊ ተቃውሞ ዙሪያ ካስተላለፏቸው ዘገባዎች አንዳንዶቹ ተመርጠው ገብተዋል፡፡

ይህች መጽሀፍ የመጀመሪያችን ናት፡፡ በቀጣይም *"የዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ"*ን አስጨናቂ ጉዞ በስፋት የሚዘግብ ድርሳን የማዘጋጀት እቅድ አለን፡፡ እቅዳችን ይሰምር ዘንድ ፈጣሪያችንን እንለምነዋለን፡፡ እርስዎም (እናንተም) የጥረታችን አጋዥ እንዲሆኑ (እንድትሆኑ) የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

ድል የኢስላም ነው!

አላሁ አክበር!!

የፌስ ቡክ ጸረ-አሕባሽ ቡድን

ክፍል አንድ

በኢትዮጵያዊያን ሙስሊም ወጣቶች የተጻፉ መጣጥፎች

Part One

Essays Writen by Ethiopian Muslim Youth

አሕባሽ ማንነው? ምንድነው? (አጠቃላይ ዳሰሳ)

ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ[1]

መስከረም 15/ 2004

አህባሽ የሚባለው አንጃ ከውጪ ሲታይ የሚከተሉት ገጽታዎች አሉት፡፡ [2]

1. "አሕባሽ" የኢትዮጵያ ተወላጅ በነበሩት *ሼኽ አብዱላሂ ሙሐመድ ዩሱፍ* (ወይም *ሼኽ አብዱላህ አል-ሐረሪ አል-ሐበሺ*) ጠንሳሽነት በሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት ውስጥ በ1983 ዓ.ል. የተመሰረተ ፖለቲካና ሀይማኖትን አንድ ላይ አጣምሮ የሚራመድ አንጃ (ጀመዓ) ነው፡፡
2. አንጃው በአረብኛ አጠራር *"ጀምዒያቱል መሻሪዒል ኼይሪያቱል ኢስላሚያ"* ይባላል፡፡ የእንግሊዝኛ ስሙ *"Association of Islamic Charitable Projects"* የሚል ነው፡፡[3]

3. "አሕባሽ" የአንጃው ተከታዮች በጋራ የሚጠሩበት የቡድን ስማቸው ነው፡፡ እያንዳንዱ የጀመዓው አባል *"ሐበሺይ"* ይባላል (ሴት ከሆነች *"ሐበሺያ"* ትባላለች)፡፡ በሀገራችን ውስጥ ያሉት የአንጃው ተከታዮች ግን "አሕባሽ" ከሚለው ስም ይልቅ "የሼኽ ጀመዓ ነኝ" ማለትን ይመርጣሉ፡፡
4. "አሕባሽ" የሚለው ቃል ምንጩ "ሐበሻ" የሚለው የሀገራችን የዐረብኛ ስም ነው፡፡ ይህም የአንጃው መስራች የተወለዱበትን ሀገር (ኢትዮጵያን) ያመለክታል፡፡ የጀመኣው አባላት ይህንን ስም ይወዱታል እንጂ አይቃወሙትም፡፡[4]

ስለዚህ እኛ የ"አሕባሽ" ተቃዋሚዎች ያወጣንላቸው ስም አድርጋችሁ እንዳታዩት ያስፈልጋል፡፡ (እውነቱን ለማወቅ አህባሾችን ራሳቸውን ጠይቋቸው፡፡ ዌብሳይቶቻቸውንና የፌስቡክ ቡድኖቻቸውን የሚጠሩበትንም ስም ተመልከቱ)፡፡

5. አንጃው በሄደበት ሀገር ሁሉ "መንግስታዊ ያልሆነ ማህበር" ተብሎ ነው የተመዘገበው፡፡[5] በመሆኑም ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን (እንደ መድረሳና የጤና ክሊኒክ የመሳሰሉትን) ከፍቷል፡፡ በሀገራችን ውስጥ ግን እንዲህ አይነት ፕሮጀክቶችን የሰራ አይመስለኝም፡፡
6. "አሕባሽ"ን የመሰረቱት "ሼይኽ አብዱላህ አል-ሀረሪ"[6] ከሶስት አመታት በፊት ቢሞቱም እስካሁን ድረስ የአንጃው ከፍተኛ መንፈሳዊ መሪ ተደርገው ይታያሉ፡፡ በመሆኑም የጀመዓው

አባላት "ሼይኹና" ወይም "ሰይዱና" ይሏቸዋል፡፡ በቤታቸው ግድግዳና በሌሎችም ቦታዎች (በሞባይል ስልካቸውም ጭምር) የመሪያቸውን ፎቶ ያስቀምጣሉ፡፡

7. የአንጃው ዋና ማዕከል (Head Quarter) ያለው በሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት ውስጥ ነው፡፡ በተጨማሪም በሶሪያ፣ ዮርዳኖስ፣ ግብጽ፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ካናዳ፣ ጀርመን፣ ዴንማርክ፣ አውስትራሊያ ወዘተ… ቅርንጫፎች አሉት፡፡[7]
8. "አሕባሽ" በርካታ ተከታዮች ያሉትም እዚያው በሊባኖስ ሀገር ሲሆን በአሜሪካ፣ ካናዳና አውስትራሊያም ጠንካራ ጀመዓ እንደመሰረተ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ሀገራችን ከገባ ከአስር ዓመታት በላይ ቢሆነውም ብዙ ተከታዮችን መመልመል አልቻለም፡፡ አብዛኛው ህዝብ አንጃው እዚህ መኖሩን እንኳ ያወቀው በቅርቡ ነው፡፡
9. አንጃው የሻፊዒይ መዝሀብ ተከታይ ነኝ ይላል፡፡ የዓቂዳ ትምህርቱም "አሽዐሪ" (ኢማም አቡል ሐሰን አል-አሽዐሪ ያስተማሩት መንገድ) እንደሆነ ያወሳል፡፡ የ"ሪፋዒያ" የሱፊ ጠሪቃ ተከታይ እንደሆነም ይገልጻል፡፡[8]
10. "አሕባሽ" በአለም አቀፍ ደረጃ የሚያሳትመው መጽሄት *"መናረል ሁዳ"* ይባላል፡፡ በቤይሩት ከተማ *"ሰውቱል ኒዳ አል-መዓሪፋ"* የሚባል ሬድዮ ጣቢያ አለው፡፡ በአለም ዙሪያ በርካታ የኢንተርኔት መረቦችንም ዘርግቷል፡፡ ከነዚህም መካከል www.aicp.org ዋነኛው ድረ-ገጽ (ዌብሳይት) ነው፡፡[9]
11. አንጃው ስብከቱን ለተከታዮቹ የሚያስተምርበት "መርከዝ" (ማእከል) አለው፡፡ በየመርከዙ የሚቀመጡ ሼይኾችንም በቤይሩት እያሰለጠነ በዓለም ዙሪያ ያሰራጫል፡፡ በመርከዙ ተምረው የሚወጡ ጎበዝ ተማሪዎችም ቤይሩት ሄደው የሚማሩበት የከፍተኛ ትምህርት እድል (scholarship) ይሰጣቸዋል፡፡
12. የአንጃው መንፈሳዊ ትምህርቶች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በአቂዳ፤ "ፊቅህ" እና "ተሰውፍ" (Sufism) ላይ ነው፡፡ የትምህርት ቋንቋውም ዐረብኛ ነው፡፡
13. አንጃው ተከታዮቹን ከሚያስተምርባቸው የመማሪያ መጽሀፍት መካከል በስፋት የሚታወቁት ሁለት ናቸው፡፡
    13.1. ***"ሙኽተሰር አብዱላህ አል-ሀረሪ"***

    ሀ/. ይህ ጀማሪዎች የሚማሩበት መጽሀፍ ሲሆን የአቂዳ፤ ፊቅህ፤ ከላም (speculative theology) ትምህርቶችን አካቷል፡፡

    ለ/. መጽሀፉ የዛሬ 100 አመት ገደማ በአንድ የመናዊ ሼኽ እንደተጻፈ በመግቢያው ላይ ተጠቅሷል፡፡ "ሼኽ አብዱላህ የጻፉት ሸርሁን (ማብራሪያውን) ነው" ተብሎም ተጽፎበታል፡፡ ነገር ግን ከመጽሀፉ 70% በላይ የሚሆነው ክፍል የተያዘው በ"ሸርሁ" ነው፡፡

    ሐ/. መጽሀፉ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ተተርጉሟል፡፡ የእንግሊዝኛው ትርጉም ቀለል ባለ አቀራረብ የተዘጋጀ ሲሆን አማርኛው ግን ልክ እንደ አረብኛው "የመጽሀፉ አዘጋጅ

እንደዚህ አሉ!" እያለ ነው ትምህርቱን የሚዘረዝረው፡፡ (የአረብኛው መጽሀፍ "ቃለል ሙአሊፉ" እያለ የሚሄድ የትረካ አቀራረብ አለው)፡፡

መ/. መጽሀፉ ላይ ላዩን ሲታይ እስላማዊ መንገድን የተከተለ ይመስላል፡፡ ነገር ግን በእስልምና ውስጥ የማይታወቁ አስገራሚ አቋሞች ይበዙበታል፡፡ ይህንን በትክክል የምትረዱትም ከዋናው ምንባብ ሳይሆን "ሸርህ" ተብለው ከቀረቡት አደገኛ ትንተናዎች ነው፡፡

ሠ/. ከሁሉም በላይ ደግሞ "ይህንን ያላለ ይከፍራል"፤ "በዚህ ያላመነ ከኢስላም ወጥቷል"፤ "ይህንን ያደረገ ካፊር ነው" የሚሉ አስፈሪ አባባሎች ስለሚበዙበት በትእግስት አንብቦ መጨረሱ ራሱ ከባድ ነው፡፡

13.2. ***"ቡግየቱ ጣሊብ"***

ሀ/. በዚህኛው መጽሀፍ የሚማሩት በትምህርት ከፍ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ (ይህኛው መጽሀፍ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ስለመተርጎሙ አላውቅም)፡፡

ለ/. ቡግየቱ-ጣሊብ በስፋት ካልሆነ በስተቀር በይዘቱ ከሙኽተሰር ጋር አንድ ነው፡፡ ቢሆንም በሙኽተሰር ውስጥ የሌሉ በርካታ አስገራሚ ፈትዋዎች አሉበት፡፡

14. ይህ አንጃ

14.1. በአፈጣጠሩ፣ በእድገቱ፣ በእምነት ፍልስፍናውና በድርጊቶቹ በጣም ግራ የሚያጋባና አነጋጋሪ (controversial) የሆነ ነው፡፡

14.2. በጅምሩ ላይ ከሶሪያ ጋር ይቀራረብ ስለነበር በሶሪያ ተጽእኖ የሚመራ ይመስል ነበር፡፡ እስካሁን ድረስም ከሶሪያ መንግስት ጋር መልካም ግንኙነት አለው፡፡ ሌሎች ድርጊቶቹን ስናይ ግን *"አህባሽና ሶሪያ የጥቅም ግንኙት እንጂ የፍቅር ግንኙነት የላቸውም"* ማለታችን አይቀርም፡፡

14.3. መላው የሊባኖስ ህዝብ በሹክሹታ እንደሚያወራውና በኢንተርኔት እንደሚጻፈው ከሆነ አህባሽ የእስራኤል የስለላ ቡድን (ሞሳድ) በረቀቀ ዘዴ የሚያሸከረከረው ድርጅት ነው፡፡[10] በመሆኑም በሊባኖስ ውስጥ ጸረ-እስራኤል አቋም ያላቸውን ማህበራትና የፖለቲካ ቡድኖች በሙሉ "ጠብ አጫሪዎች ናችሁ" እያለ ይቃወማል፡፡ የፍልስጥኤም የነጻነት ጥያቄን በሚመለከትም "በሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው መፈጸም ያለበት" የሚል ያልተብራራ አንቀጽ በፖለቲካ ማኒፌስቶው ላይ እንዳሰፈረ የዛሬ 15 አመት ገደማ ስለቡድኑ የጻፉት ኒዛር ሀምዛ እና ህሬር ዴክሜጂያን ይገልጻሉ፡፡[11]

14.4. በቅርቡ እነ ሀጋይ ኤርሊችን የመሳሰሉ ጽዮናዊያን *"አህባሽ የሚከተለው ለዘብተኛ ኢሰላማዊነት ለዓለም አስፈላጊ የሆነ የሰላም መድሀኒት ነው"* እያሉ መጻፋቸውም ከላይ የተባለውን ጥርጣሬ ወደ እውነታ ከፍ ያደርገዋል፡፡

14.5. ከሁሉም በላይ አህባሽ በአለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞችን ያስደነገጠው በሶስት አቋሞቹ ነው፡፡

ሀ/. በቅድሚያ ከየት እንደተገኙ የማይታወቁ የእምነት ፍልስፍናዎቹን የማይቀበሉ ሙስሊሞችን በጅምላ "ካፊር ናቸው" በማለት ይፈርጃል፡፡

ለ/. በሁለተኛ ደረጃም ከምዕራባዊያን ጋር ቅጥ ያጣ የወዳጅነት ትስስር አለው፡፡ ሙስሊሙን እንደጠላት ለሚያዩት ምዕራባዊያን አህባሽ ውድ ልጃቸው ነው፡፡ በተለይ ከሴፕቴምበር 11/2001 ወዲህ ተፈላጊነቱ ጨምሯል፡፡

ሐ/. በሶስተኛ ደረጃም ሙስሊሞችን ለጥቃት የሚያሳድድ "ሙስሊም ነኝ" ባይ አንጃ መሆኑ በጣም እያነጋገረ ነው፡፡ አንጃው በይፋ ሲናገር "ጠላቶቼ ወህቢዎች ናቸው" ይላል፡፡ ይህ ግን የአንጃው የማስመሰያና የመከፋፈያ ስልት መሆኑን ቡድኑን በቅርበት የሚያውቁ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ "ጠላቶቹ መላው ሙስሊሞች ናቸው" በማለትም ያስረዳሉ፡፡

አህባሽ በጥቅሉ ሲታይ ይህንን ይመስላል፡፡

---

1. ***ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ*** የምስራቅ አፍሪካ የእስልምና ታሪክ ተመራማሪ ናት፡፡
2. ይህ ጽሁፍ በቅድሚያ የተለቀቀው ፌስቡክ በተሰኘው ማህበራዊ ድረ-ገጽ ነው፡፡ በማስከተልም በተለያዩ ድረ-ገጾች ላይ ወጥቷል፡፡
3. Nizar Hamzeh and R. Hrair Dekmejian፡ *A Sufi Response to Political Islamism: Al-Ahbash of Lebanon*፡ 1996 Mustafa Kabha and Haggai Erlich፡ *Al-Ahbash and Wahhabiya: Interpretations of Islam*፡ 2006
4. Mustafa Kabha and Haggai Erlich፡ ibid: 2006 የአሕባሽ ድረ-ገጽ www.aicp.org
   መጅሊስና አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት ከሰሞኑ "አሕባሽ" የሚባል ነገር የለም፤ ይህ ወሃቢዮች የሚያሰራጩት የፈጠራ ወሬ ነው" እያሉ ነው፡፡ ድርጅቱ ግን "አለሁ፤ አሕባሽ ነኝ" ይላል፡፡ ሁሉም የአንጃው ተከታዮች "አሕባሽ" በሚለው ስም ከልክ ያለፈ ደስታ እንደሚሰማቸው ይገልጻሉ፡፡ በቅርቡ አቡ ኢብራሂም አል-ሀረሪ የተባሉ የአሕባሽ ተከታይ ለዚህ የኡባህ አብዱሰላም ጽሁፍ መልስ ይሆናል ብለው ባሰራጩት የ37 ገጽ ድርሳን "እኛ አሕባሾች" የሚለውን አባባል ይደጋግሙታል፡፡
5. Nizar Hamzeh and R. Hrair Dekmejian፡ ibid: 1996 Mustafa Kabha and Haggai Erlich፡ ibid: 2006 የአሕባሽ ድረ-ገጽ www.aicp.org
6. አሕባሽን የመሰረቱት ሼክ አብዱላሂ አል-ሐረሪ የተወለዱት በ1910 ዓ.ል. ሐረር ከተማ ውስጥ ነው፡፡ እስከ ጉልምስና ዘመናቸው በኖው ሀገር ሲማሩና ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ በ1948 ዓ.ል. ወደ መካከለኛው ምስራቅ ተሻገሩ፡፡ ለአንድ ዓመት ያህል በሶሪያ ዋና ከተማ በደማስቆ ቆዩ፡፡ ከዚያም በ1950

ዓ.ል. ወደ ሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት በመግባት እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ ድረስ በዚያው ሀገር ኖሩ፡፡

Nizar Hamzeh and R. Hrair Dekmejian፡ ibid: 1996፡ Mustafa Kabha and Haggai Erlich፡ ibid: 2006

7. Mustafa Kabha and Haggai Erlich፡ ibid: 2006
8. Mustafa Kabha and Haggai Erlich፡ ibid: 2006 የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት፤ *የሼኽ አብዱላሂ አል-ሀረሪይ እውነታዎች*፤ 2004 ገጽ 9-10
9. ስለአሕባሽ ብዙ የጻፉት Thomas Pierret እንደሚገልጹት የአንጃው የኢንተርኔት አጠቃቀም ከተከታዮቹ ቁጥር አንጻር ሲመዘን ጠላቶቹ ናቸው ከሚላቸው "ወሃቢዮች" በብዙ እጥፍ ይበልጣል፡፡ Thomas Pierret, "Internet in a Sectarian Islamic Context," *The International Institute for the Study of Islam in the Modern World* 15 (2005):
10. Nizar Hamzeh and R. Hrair Dekmejian፡ ibid: 1996
11. Nizar Hamzeh and R. Hrair Dekmejian፡ ibid: 1996

የፍትሕ ጥያቄያችን ከግቡ እንዲደርስ

የፌስ ቡክ ጸረ-አሕባሽ ቡድን

መስከረም 1/ 2004

እኛ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች "አሕባሽ"ን የምንታገለው አንጃው ከኛ የተለየ አመለካከትና የእምነት ፍልስፍና ስለያዘ አይደለም፡፡ የትግላችን መነሾዎች

1. አንጃው የሀገራችን ሙስሊሞች ሁሉ የጋራ ተወካይና መንፈሳዊ መሪ መሆኑ የሚታመንለትን የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት በሞኖፖል በመቆጣጠሩ በኑፋቄና በጥመት የተወገዘውን የእምነት ፍልስፍናውን በመላው ኢትዮጵያ የሚሰራጭበት እድል በመፈጠሩ
2. አንጃው ባለው የፅንፈኝነት ባህሪ ከርሱ ጋር የማይጣጣሙትን ሁሉ "ከፍራችኋል" (ከኢስላም ወጥታችኋል) እያለ በወንድማማቾች መካከል የጥላቻና የሽብር መርዝ ሲዘራ እንደነበረ በስፋት ስለሚታወቅና "ይህንን ድርጊት በሀገራችን መድገሙ አይቀርም" ብለን ስለሰጋን
3. አሜሪካ "የወሃቢያን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር" በሚል ሽፋን በሙስሊሞች ላይ ለከፈተችው ኢ-ፍትሐዊ ዘመቻ ይህን በኑፋቄና በጥመት የተወገዘ የ"አሕባሽ" አንጃ ፊታውራሪ አድርጋ ማሳለፏ በበቂ ማስረጃዎች በመረጋገጡ
4. የአንጃው ጽንፈኛ አመለካከቶች በሙስሊሙና በሌላ ሀይማኖት ተከታዮች መካከል ለረጅም ዘመናት ጸንቶ የቆየውን የመተባበርና የመቻቻል ባህል ያደፈርሳል ብለን ስለሰጋን እና ሌሎችም ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ይህ አንጃ በእምነታችንና በሰላማችን ላይ የደቀነውን አደጋ ለመቀልበስ በምንችለው ሁሉ ለመታገል ቆርጠን ተነስተናል፡፡ ትግላችንን የምናካሄደው በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ግባችንም በሀገራችን ህገ መንግስት የተረጋገጠልንን የእምነት ነጻነት መብታችንን ማስከበር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የሚከተሉት የትግል ስልቶችን መንደፍ አስፈላጊ ሆኖ ታይቶናል፡፡

1. መንግስታትን በሚመለከት

1.1. የኢትዮጵያ መንግስት አካላት (ባለስልጣኖችም ሆኑ ተቋማት) ስለ "አሕባሽ" ምንነት በቂ መረጃ ያላቸው አይመስለንም፡፡ የአንጃው የእምነት ፍልስፍና አጠቃላዩ የዓለም ሙስሊም ህብረተሰብ ከሚከተላቸው የእስልምና አስተምህሮዎች የቱን ያህል እንደሚራራቅ በደንብ አያዉቁትም፡፡ ስለዚህ "አሕባሽ" በብቸኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርቱን እንዲሰጥ መፍቀድ ማለት "እስከዛሬ ድረስ የምትከተሉትን እምነት ቀይሩ"

የማለት ያህል እንደሆነ ለሁሉም የመንግስት አካላት በምንችለው መንገድ ሁሉ ማሳወቅ አለብን፡፡

1.2. ከዓለም አቀፍ ፖሊሲ ትንተናው በመነሳት "አሕባሽ"ን ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች መሪነት ለመረጠው የአሜሪካ መንግስት ትንተናው በተሳሳተ ግምገማ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ በሚቻለው መንገድ ሁሉ ማሳወቅ አለብን፡፡ (ለምሳሌ የአሜሪካ መንግስት እንደሚለው የአክራሪነትና እና የጽንፈኝነት አመለካከቶች በሀገራችን ውስጥ መሰረት እንደሌላቸው ማሳወቅ አለብን)፡፡

1.3. "ሽብርተኝነት"ን ለመዋጋት መፍትሔው በቀድሞው የሊባኖስ ጠቅላይ ሚኒስትር ግድያ ከተወነጀሉት የሽብር ግብረ-ሃይሎች አንዱ የሆነውን "አሕባሽ"ን ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች መሪነት መምረጥ ሳይሆን ሽብርተኝነት በኢስላም ሃይማኖታዊ መሰረት እንደሌለው የሚያውቁትን ሙስሊሞች በጋራ ማንቀሳቀስ እንደሆነ ማስረዳት አለብን፡፡ (ኢስላምን አስታከው ድብቅ አጀንዳቸውን ማራመድ የሚፈልጉ ሃይሎች ካሉ ሙስሊሙ ራሱ ሊቆጣጠራቸው ይችላል)፡፡

2. አህባሾችን በተመለከተ

2.1. አህባሾች በአራት ክፍል እንደሚመደቡ መታወቅ አለበት፡፡ እነርሱም

ሀ/. ***ዓለም አቀፍ አህባሾች***፡- እነዚህኛዎቹ በሀገራችን ውስጥ በብዛት የሉም፡፡ ሆኖም በማእከሎቻቸው በአስተማሪነት ይመደባሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በእምነት ስም በሌላው አለም (በተለይ በሊባኖስ) የለመዱትን በመርዝ የተለወሰ የጥላቻ ትምህርት በሀገራችን እንዲያስፋፉ የሚፈቅድላቸው የህግ የለም፡፡ ሰላማዊ ስብከት እንጂ *"እገሌ ካፊር ነው በሉ"፤ ከወሃቢያ ጋር ቡና አትጠጡ፤ ምሳ አትብሉ፤ ትከፍራላችሁ"* እያሉ እንዲያስተምሩ የሚፈቅድላቸው የህግ አንቀጽ የለም፡፡ ስለዚህ የጥላቻ ዘመቻቸውን ማጋለጥና በህጋዊ መንገድ መታገል ይገባል፡፡ (እነ ዶ/ር ዛኪርን በ"ኩፍር" የወነጀሉት እነዚህ አለም አቀፍ አህባሾች ናቸው፡፡)

ለ/. ***በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆኑ ጽንፈኛ አህባሾች***፡- እነዚህኛዎቹን በኢስላማዊ አስተምህሮ እየተከራከሩ መመለሱ በእጅጉ ይከብዳል፡፡ ስለዚህ ብዙም ባናተኩርባቸው ይሻላል፡፡

ሐ/. ***ኢትዮጵያዊ የሆኑ ለዘብተኛ አህባሾች***፡- እነዚህኛዎቹ ከሌላው ሙስሊም ጋር ይቀራረባሉ፡፡ ከኛ ጋር በጀመአ በአንድ መስጊድ ሊሰግዱም ይችላሉ፡፡ (በ"ለ" የተጠቀሱት ግን ጁምዓ እንኳ ለብቻቸው ካልሆነ በስተቀር ከኛ ጋር አይሰግዱም)፡፡ ስለዚህ በዚህ ስር የሚጠቃለሉትን የአህባሽ ሰዎች እስከምንችለው ድረስ መምከርና ለመመለስ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

መ/ ***"አኩራፊ አህባሾች"***፡- እነዚህኛዎቹ በኛው አያያዝ ተናደው ወደ አህባሽ የተጠጉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ የሀገራችን ሙስሊሞች ከባህል የወረሷቸውና በእስልምና ተቀባይነት የሌላቸው በርካታ ልማዶች ይታይባቸዋል፡፡ እነዚህን ወገኖች ዳዒዎች በለዘብታ ቃላት ማስተማር ሲገባቸው በከረረ ቃላትና ወቀሳ (አንዳንዴም በስድብ) ይወርዱባቸዋል ("ሙሽሪክ" ብሎ የሚወነጅላቸው ሰውም አለ)፡፡ በመሆኑም እነዚህ

ወገኖች ያኮርፉና ወደ "አህባሽ" ጎራ ይገባሉ፡፡ ስለዚህ ዳዒዎች ማስተካከል ያለባቸውን ግድፈቶች ማረምና ወገኖቻችንን ማስተማር አለባቸው፡፡

2.2. በማንኛውም ወቅት የአህባሽ ጎራ ተከታይ ከሆነ ሰው ጋር ከቃላትና ከጽሁፍ የዘለለ ክርክር ማድረግ የለብንም፡፡ (ለግጭት በሚጋብዝ ሁኔታ መከራከር አይገባንም)፡፡

2.3. የአህባሽ ተከታዮችን እራሳቸው ካልፈለጉ በስተቀር ከማህበራዊ ኑሮ ማግለል አይገባም፡፡

3. የሀገራችን ሙስሊሞችን በሚመለከት

3.1. የሀገራችን ህዝበ ሙስሊም ስለአህባሽ በቂ መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ አለብን፡፡ ለዚህም አሁን ከጀመርነው የኢንተርኔት መስኮት በተጨማሪ ሌሎች መንገዶችንም መጠቀም አለብን፡፡

3.2. የሀገራችን ምሁራን በትግላችን እንዲሳተፉ መጋበዝ አለብን፡፡ (ለምሳሌ ከዚህ ቀደም "ተከፊር ወል-ሂጅራ" በተባለው ጠማማ ቡድን ላይ በርካታ መጽሀፍት እንደተጻፉት ሁሉ በአህባሽም ላይ ተመሳሳይ ድርሰቶች መጻፍ አለባቸው፡፡)

3.3. ታዋቂ ግለሰቦችም ድምጻቸውን ማሰማት እንዲችሉ መቀስቀስ ይገባል፡፡

3.4. የሙስሊም ጋዜጦቻችን የጀመሩትን አህባሽን የማጋለጥ ዘመቻ አጠናክረው ሊቀጥሉበት ይገባል፡፡

4. ከሀገራችን ውጭ ያለውን ህዝበ ሙስሊም በተመለከተ

4.1. በዲያስፖራ ያሉት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በሰላማዊና ህጋዊ ትግላችን እንዲሳተፉ መቀስቀስ አለብን፡፡

4.2. ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጉዳይ በመሆኑ ሌሎች መንግስታትና የውጪ ሀገር ዜጎች በቀጥታ የሚሳተፉበት ምክንያት የለም፡፡ ሆኖም አህባሽ በዓለም ዙሪያ ተሰራጭቶ ሙስሊሞችን እየበጠበጠ ያለ ቡድን በመሆኑ ስለ አንጃው ድብቅ ታሪኮችና እንቅስቃሴዎች፤ ስለእምነት ፍልስፍናው መሰረቶች፤ ስለ ማሳሳቻ ስልቶቹ፤ የዓለም ሙስሊም ምሁራን የሰጧቸውን ፈትዋዎች፤ የአንጃውን እንቅስቃሴ ለመገደብ የወሰዷቸውን እርምጃዎች ወዘተ... በመሳሰሉት ላይ ሃሳባቸውን በማጋራት ለመተባበር ከፈለጉ በደስታ እንቀበላቸዋለን፡፡

አሕባሽ ሆይ! የሱስንዮስና የዮሀንስ ዘመን አልፏል!

ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ

መስከረም 4 / 2004

የኢትዮጵያ ታሪክ በጦርነትና በፍትጊያ የተሞላ ነው፡፡ ከነዚህ ጦርነቶች መካከል አብዛኛዎቹ በእብሪተኛ መሪዎች ቀስቃሽነት ነበር የተካሄዱት፡፡ ዓለም በስልጣኔ ጎዳና ወደ ፊት ሲገሰግስ የያኔዎቹ የኢትዮጵያ መሪዎች ግን "እኔ አውቅልሀለሁ" በሚል ጀብደኝነታቸው ህዝቡን እርስ በራሱ ያጫርሱት ነበር፡፡ አንዳንድ መሪዎችማ ህዝቡ የቀድሞ እምነቱን ትቶ እነርሱ የመረጡለትን ጎዳና እንዲከተል ለማስገደድ ሲሉ ህዝቡን ከፍተኛ እልቂት ባስከተሉ ጦርነቶች ውስጥ ሲዘፍቁት ኖረዋል፡፡ ነገር ግን እነርሱ የፈለጉት ሃይማኖትን የማስቀየር ፖሊሲ አልተሳካላቸውም፡፡ ይህንንም በሁለት ምሳሌዎች መግለጽ ይቻላል፡፡

1. ***አጼ ሱስንዮስ (ከ1605-1632)***፡- አጼ ሱስንዮስ ከምዕራብ አውሮፓ (ፖርቱጋልና ስፔን) በመጡት የካቶሊክ እምነት ሰባኪያን ተማርኮ ሃይማኖቱን ለወጠ፡፡ ሳይውል ሳያድርም በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት ካህናት፤ ቀሳውስትና መላው የክርስቲያን ህዝብ የኦርቶዶክስ ሃይማኖቱን ትቶ ወደ ካቶሊክ እምነት እንዲገባ አዋጅ አስነገረ፡፡ ህዝቡ ግን ትዕዛዙን "አልቀበልም!" አለ፡፡ በነገሩ የተናደደው አጼም ፍላጎቱን በሃይል ለመፈጸም ተነሳ፡፡ መላው ሰራዊቱን በክርስቲያኑ ህዝብ ላይ አዘመተ፡፡ ህዝቡም ከሱስንዮስ ሰራዊት ጋር ተጋፈጠ፡፡ በሀገሪቱ ላይ የጦርነት እሳት ነደደ፡፡
   አጼ ሱስንዮስ ጀብደኝነት ባሳወረው ወኔው በጦርነቱ ገፋበት፡፡ ለ27 አመታት በዘለቀው የስልጣን ዘመኑ ምንም ሳይሰራበት ሀገሪቷን በጦርነት እሳት ሲለበልባት ቆየ፡፡ እርሱ የለኮሰው እሳት የቆመው አጼው "አለም በቃኝ" ብሎ ወደ ገዳም ሲገባና ልጁ ፋሲል በአባቱ ቦታ ንጉስ ተብሎ ሲሾም ነው፡፡
2. ***አጼ ዮሀንስ አራተኛ (ከ1870-1888)***፡- አጼ ዮሀንስ *"በአንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት"* በሚለው ፖሊሲያቸው ይታወቃሉ፡፡ ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ ለማዋል ሲሉ ከታናሻቸው ከአጼ ምኒልክ ጋር እንኳ ተጣልተዋል (ምኒልክ በሃይማኖት ፖሊሲያቸው ጥሩ ባይባሉም ከአጼ ዮሀንስ ይሻላሉ)፡፡
   አጼ ዮሀንስ ፖሊሲያቸውን ለመተግበር ሲነሱ በቅድሚያ የመረጡት የወሎ ክፍለ ሀገርን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ለብዙ ምዕተ አመታት እምነታቸውን አስጠብቀው የቆዩት የወሎ ሙስሊሞች በአንድ ወር ውስጥ ክርስትና ካልተነሱ በሰይፍ እንደሚቀጡ አዋጅ ተነገረ፡፡ ወላዋዩና ሹመት ፈላጊው (እንደ ራስ ሚካኤል አይነቱ) የአጼውን ትእዛዝ ለመፈጸም ተሸቀዳደመ፡፡ አብዛኛው ህዝብ ግን እስልምናን በምንም ዋጋ እንደማይለውጥ ለአጼው ቁርጡን ነገራቸው፡፡ በነገሩ የተናደዱት አጼ ዮሀንስ የሸብርና የጦርነት ጅራፋቸውን በወሎ ህዝብ ላይ መዘዙ፡፡ ሙስሊሙ ህዝብ በሼኽ ጠለሃ ጃዕፈር፤ በአባ ዋጠው እና በሌሎችም ሙጃሂዶች ዙሪያ በመሰለፍ እብሪተኛውን አጼ ተጋፈጠ፡፡ የአጼው ጥቃት

እየባሰበት ሲሄድም ህዝቡ ለሃይማኖቱ ሲል ወደ ሀረር፤ ባሌ፤ ጅማ እና ጉራጌ ተሰደደ፡፡ ነገሩ አንጀቱን ያሳረረው ደግሞ ወደ ሱዳን እየተሰደደ ከኢማም አህመድ አልማህዲ ጦር ጋር ተቀላቀለ፡፡

አጼው በጦርነት ፖሊሲያቸው ገፉበት፡፡ ሆኖም ጦርነቱ ሃይማኖትን ሊያስለውጥ አልቻልም፡፡ እንዲያውም የርሳቸው ህይወት እንዲቀጠፍ ምክንያት ሆነ፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው ሁለት ምሳሌዎች በርካታ ቁምነገሮችን ያስተምሩናል፡፡ ምሳሌዎቹን በትክክለኛ አእምሮ ያነበበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እምነትን በግድ ለመጫን የሚደረግ ጥረት መጨረሻው ውድቀት እንደሆነ በደንብ ይገነዘባል፡፡

ዛሬ አለም በሰለጠነበትና ጭፍንነትና አጉል አክራሪነት አንድ እርምጃ እንኳ በማያራምዱበት ዘመን አህባሾች "አይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ" ሊሉን መጥተዋል፡፡ ከኋላቸው በሚገፉቸው ስውር እጅ (አሜሪካ) እየታገዙ የመጅሊስን ስልጣን በመቆጣጠራቸው ብቻ ድል የሚቀናቸው እየመሰላቸው ነው፡፡ ህዝቡ ግን "እስከዛሬ የተከለተላችሁት እምነት ስህተት ስለሆነ በአዲስ መልክ ወደ እስልምና ግቡ" ሊሉት የመጡ መሆናቸውን በደንብ ያውቃል፡፡ የዓለም ህዝብ የሚያምንባቸውንና ለሃይማኖታቸው ከልባቸው ሲሰሩ የቆዩትን ኡለማ "ካፊር ናቸው" እያሉ በመሳደባቸው ብቻ ልቡ ቆስሏል፡፡

ስለዚህ አህባሾች የመጅሊስን ስልጣን ቀርቶ የሀገሪቱን ስልጣን ሙሉ በሙሉ ቢቆጣጠሩ እንኳ የሚለውጡት አማኝ ያለ አይመስለኝም፡፡ ይህ ህዝብ አያቶቹ ከነ አጼ ዮሐንስ ጋር እየተጋፈጡ የጠበቁትን እስልምና በተራ ጮሌነት ያስረክባል ብለው ገምተው ከሆነ በህልም አለም ውስጥ ነው ያሉትና ህዝቡ "ከህልማችሁ ንቁ!"ይላቸዋል፡፡ እውነታው ደግሞ በተግባር ይታያል፡፡ ድል የኢስላም ነው!! አላሁ አክበር!!

አሕባሽ ፤ ዴቪድ ሺን እና የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ስጋት

ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ

መስከረም 6 / 2004

የ"አህባሽ" ጀመዓ ለብዙዎቻችን ስጋት ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ አንጃው አመለካከቱን በህዝቡ ውስጥ ለማስረጽ ሲል ከጸረ-እስላም ሃይሎች ጋር እንኳ አንድ ላይ ወግኖ ሙስሊሞችን ከመጉዳት ወደ ኋላ የማይል መሆኑ ነው፡፡ የአንጃውን የኋላ ታሪክ የሚያውቁ ወገኖች ይህንን በስፋት ሲዘረዝሩ ነበር፡፡ ለመሆኑ ይህ ጽንፈኛ አንጃ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ሙስሊሞችን እንዲመራ ማን መረጠው?

ይህንን ጥያቄ መመለስ ይከብዳል፡፡ ሆኖም አንድ ነገር በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ጉዳይ ለብቻው አልወሰነውም፡፡ ነገሩ የበርካቶች እጅ አለበት፡፡ ከሁሉም እጆች የሚተልቀው ደግሞ የአሜሪካ እጅ ይመስለኛል፡፡

አሜሪካ ከመስከረም 11/2011 ወዲህ በሽብር ላይ ጦርነት ከፍቻለሁ ትላለች፡፡ ቀንደኛ አሸባሪዎችን የሚፈለፍለውም "እስላማዊ አክራሪነት ነው" ባይ ነች፡፡ በአሜሪካ አመለካከት "የእስላማዊ አክራሪነት ምንጭ "ወሃቢያ" የሚባለው ቡድን ነው፡ ኢትዮጵያም ወሃቢያ እየተጠናከረ የመጣባት ሀገር ናት፡፡ ስለዚህ የወሃቢያን አክራሪ አቋም ለመቆጣጠር በርካታ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ከሙስሊሞች መካከል ከወሀቢያ ጋር ፈጽሞ የተቃረነ ትምህርትና የእምነት ፍልስፍና ያላቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች ማጠናከርና በወሃቢያ ላይ የበላይ እንዲሆኑ መርዳት ነው፡፡" በዚህ ስሌት መሰረት ነው እንግዲህ "አህባሽ" በአለም አቀፍ ደረጃ የተመረጠልን፡፡ ለመሆኑ ይህንን ጥቆማ ለአሜሪካ የሰጠው ማን ነው?

ብዙዎች አህባሽን "ለኢትዮጵያ የመረጡት ፕሮፌሰር ሀጋይ ኤርሊች ናቸው" ይላሉ፡፡ እኔ ግን ሀጋይ ኤርሊችን ብቻ አልጠረጥርም፡፡ ከሀጋይ ኤርሊች ጋር በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩትን ዴቪድ ሺንን እጥረጥራለሁ፡፡ ምክንያቱም ሃጋይ ኤርሊች ነገሩን በይፋ በማቀንቀን የመጀመሪያ ሰው ይሁኑ እንጂ አህባሽ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢናጠከር ለኢትዮጵያም ሆነ ለአሜሪካ ጥቅም የሚበጅ እንደሆነ በፖሊሲ ደረጃ ሲሰብኩ የነበሩት ዲቪድ ሺን ነበሩ፡፡ ለዚህም አምባሳደር ዴቪድ ሺን በዲሴምበር 20/2004 ቤይሩት በሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ (American University of Beirut) ***"እስልምናና ግጭቶች በአፍሪካ ቀንድ"*** በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ግንባር ቀደም ሆኖ ይጠቀሳል፡፡[1]

አምባሳደር ዴቪድ ሺን ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ላይ በርካታ የፖሊሲ ጥናቶችን አቅርበዋል፡፡ ይህ ጽሁፋቸው ግን ***"አህባሽ በአሜሪካ መንገድ ላይ ይለፍ"*** የሚለውን አረንጓዴ መብራት ያበራ እንደሆነ ከአቀራረቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ዴቪድ ሺን ከሰባት ዓመት በፊት የተነፈሱት የፖሊሲ ሀሳብ በሙከራ ደረጃ በስራ ላይ ሲውል ቆይቷል፡፡ ለዚህም አንዳንድ መረጃዎችን ልስጣችሁ፡፡

1. የአሜሪካ ኤምባሲ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሲያዘጋጃቸው የነበሩት የረመዳን የኢፍጣር ፕሮግራሞች (በዚህ ፕሮግራም ላይ እንዲገኙ ሲጋበዙ የነበሩት እነማን ናቸው? እንዴትስ ነው የሚመረጡት?)
2. አሜሪካ በራሷ በጀት በባሌ የሚገኘውን የዲሬ ሼኽ ሁሴን መስጊድና የመቃብር ቦታ ማሳደሷ (አሜሪካ "ወሃቢያዎች ዲሬ ሼኽ ሁሴን የመሳሰሉትን ቀደምት መስጊዶችና የመቃብር ቦታዎች ማጥፋት ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ "ሱፊዎች የሚጎበኟቸውን የመቃብር ቦታዎችና ሀድራዎች ማጠናከር ያስፈልጋል" ትላለች፡፡)
3. ባለፉት ሁለት ዓመታት በተካሄዱት የአካባቢ የመጅሊስ ምርጫዎች "ወሀቢያዎች" እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉት ኮሚቴዎች እንዳይሳተፉ በሚል ሲሰሩ የነበሩት የምርጫ ቲያትሮች

ነገሩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በትጋት ሲካሄድ ነበር፡፡ ይህንንም አምባሳደር ዶናልድ ያማሞቶ በጻፉትና ዊኪሊክስ በኢንተርኔት በለቀቀው የቴሌግራም ዘገባ በስፋት ነግረውናል፡፡[2]

የሚገርመው ነገር የትኛውም የአህባሽ ጀመዓ አባል ይህንን ጉዳይ የማያስተባብል መሆኑ ነው፡፡ እንደ አህባሾች አመለካከት "ወሀቢያ የተባለው ቡድን እስልምናን ለማጥፋት በሙሉ ሃይሉ የሚሰራ የሙናፊቆች ስብስብ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱን በተቻለው መንገድ ሁሉ መታገል ያስፈልጋል፡፡" አህባሾች በቀጥታ የሚሉት ይህንን ነው፡፡

ያ ጀመዓ! "አህባሽ" ስለማንቀበለው ብቻ በተለመደው ጽንፈኛነቱ "ወሃቢያ ናችሁ!" ይለናል፡፡ አሁንማ "ባለቤቷን የተማመነች በግ ላቷን ውጪ ታሳድራለች" አይነት ነገር ሆኖብናል፡፡ አሜሪካንና መንግስትን ተጠግቶ እኛን ሊፈራ? አላህን ያልፈራ እኛን እንዴት ይፈራል? ከሰሞኑ ግር ግር እንደማየውማ "ወሃቢያ ናችሁ" በሚል የጸረ-አሸባሪነት ህግ የሚባለውን አሳሳቢ አዋጅ በሙስሊሞች ላይ እያስመዘዘ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ለስቃይ እና ለእንግልት እንዳይዳርግ ያሰጋናል፡፡ ስለዚህ ስጋታችን "ስጋት" ብቻ ሆኖ እንዲቀር ትግላችንን ማጠናከር አለብን፡፡

ያ ጀመዓ! እኔ ይህንን ብያለሁ፡፡ እናንተስ ምን ትላላችሁ? አህባሽ "አህሉ ሱንና ወልጀመዓ" የሚለውን ስም በውሸት ደርቦ "ወሃቢያ ናችሁ" እያለ የፈለገውን ሊፈጽምና ሊያስፈጽም አሰፍስፏል፡፡እርሱን በመመከቱ ዙሪያ በጋራ እንወያይ፡፡ ሀቅን እስከያዝን ድረስ የአላህ እርዳታ ከኛ ጋር ነውና፡፡

---

1. የዴቪድ ሺንን ጽሁፍ ከሚከተለው የድረ-ገጽ አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡፡

http://www.ephrem.org/dehai_archive/2005/nov04-jan05/0562.html

2. አምባሳደር ያማሞቶ ከጻፏቸው ቴሌግራሞች መካከል አንደኛውን በሚከተለው አድራሻ መከፈት ይቻላል (የሌሎቹ አድራሻ በዚሁ መጽሀፍ መጨረሻ ላይ በተያያዘው አባሪ ውስጥ ይገኛል)፡፡ http://wikileaks.org/cable/2009/07/09ADDISABABA1674.html

አሕባሽና ጽዮናዊው Anti Defamation League

ኡባህ አብዱሰላም ሰዒድ

ጥቅምት 15/2004

"አህባሽ" በሙስሊሙ ዓለም አነጋገሪ የሆነበት አንደኛው ምክንያት *"አንጃው ለጽዮናዊያን ሀይለኛ ፍቅር አለው"* ተብሎ መነገሩ ነው፡፡ በርግጥም አህባሽ ከጽዮናዊያን ጋር ሞቅ ያለ ፍቅር እንዳለው የሚያስረዳው ትልቁ ነገር ድርጊቱ ነው፡፡ የአንጃው ጽሁፎች፤ ፕሮፓጋንዳዎችና ድርጊቶች በሙሉ ጽዮናዊያን በሚፈልጉት ስልት የተቃኘ ነው፡፡ ስብከቱ፣ ተረቱ፤ ውረፋው፤ ጥላቻው፤ ወዘተ... ያነጣጠረው በሙስሊሞች ላይ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ባህሪ ነው የጽዮናዊያንን አንጀት የሚያርሰው፡፡

ሆኖም እስከዛሬ ድረስ ይህንን ጉዳይ በተሟላ ሁኔታ የሚያጠናክርልን ማስረጃ ለማግኘት ተስኖን ቆይቷል፡፡ ከሀገራችን ጉዳይ ጋር አያይዘን እንደ ትልቅ ማስረጃ የምናቀርበው የጽዮናዊውን ፕሮፌሰር የሀጋይ ኤርሊች ጽሁፎችን ነው፡፡ በርግጥም ሀጋይ ኤርሊች "አህባሽ"ን ለመሪነት ካጩልን ሰዎች መካከል ቀንደኛው ነው፡፡ ከዚያ ባለፈ ግን ነገሩን በእርግጠኝነት የምናስረዳበት ማስረጃ አልነበረንም፡፡

ዛሬ ግን ተሳክቶልናል። አልሐምዱሊላህ! የመጀመሪያው ትልቅ ማስረጃ ከእጃችን ገብቷል፡፡ ይህ ማስረጃ አህባሾች በፌስቡክ ቡድናቸውና በመርከዛቸው "ተረት ነው፤ አሉባልታ ነው፤ የጠላት ወሬ ነው!..." ወዘተ እያሉ በማጭበርበር ነገሮችን እንዲሸፋፍኑ እድል የማይሰጣቸው አይነት ነው፡፡ በዚህ በኩል ጥሩ ነው፡፡ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ሙስሊሞች የእምነት ነጻነት ላይ የተደቀነውን ታላቅ አደጋ የሚጠቁም በመሆኑ ከፍተኛ ስጋት ይቀሰቅሳል፡፡

ለማንኛውም ማስረጃውን እነግራችኋለሁ፡፡ ከዚያ በፊት አላህ ይህንን ውድና ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ በእጃችን ላይ ስለጣለልን ምስጋናችን ይድረሰው እላለሁ፡፡ በማስከተልም ይህንን ውድ ማስረጃ ያመጡልንን "የጸረ-አህባሽ" ፌስቡክ ቡድን መስራች አባላትና መሪዎች "አላህ ምንዳቸውን ያብዛው፤ ከክፉ ነገር ይጠብቃቸው" ለማለት እወዳለሁ (እናንተም ዱዓ አድርጉላቸው)፡፡

የጸረ- ሰም ማጥፋት ሊግ (Anti-Defamation League)

እንደዚህ የሚባል ድርጅት ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እኔ ግን እስከ እሁድ ሌሊት (ጥቅምት 14/ 2004 ዓ.ል.) ድረስ በዚህ ስም የሚጠራ ድርጅት ስለመኖሩ በጭራሽ ሰምቼ አላውቅም፡፡ የሚገርመው ታዲያ ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ "ሰብአዊ መብትን እናስጠብቃለን" በሚል ስም ከተቋቋሙ ጥንታዊ ተቋማት ጋር የሚመደብ መሆኑ ነው፡፡ ከፍልስጥኤማዊያን ጥያቄ ጋር በተያያዘ በአል-ጀዚራና በሌሎችም ጣቢያዎች በየጊዜው አስፈሪ ዘገባዎች የሚቀርቡበት ድርጅት መሆኑም

ሌላ ነገር ነው፡፡ የድርጅቱ ዌብሳይት እልፍ አእላፍ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ከሚያዘወትሯቸው ድረ-ገጾች መካከል የሚመደብ መሆኑም ሌላ የማላውቀው እንቆቅልሽ ነው፡፡ በአጭሩ "የኢንተርኔት ሱሰኛ ነኝ" እያልኩ ስጀነን ኖሬ እንዲህ ዓይነት ስመ-ገናና ድርጅት መኖሩን እንኳ አለማወቄ "በጣም ገና" ከሚባሉት ጀማሪዎች ጎራ ውስጥ የምመደብ መሆኑን አሳይቶኛል፡፡

"የጸረ-ስም ማጥፋት ሊግ" ዓላማው፣ ስያሜውና ድርጊቶቹ ሶስቱም ይለያያሉ፡፡ የድርጅቱን ዌብሳይት ስትከፍቱ ዓይናችሁ በቅድሚያ የሚያርፈው *"To stop the defamation of the Jewish people: To secure Justice and fair treatment for all"* ተብሎ በተጻፈው የድርጅቱ ዓላማ ማስተዋወቂያ ላይ ነው (በአማርኛ "በአይሁዶች ላይ የሚካሄደውን ስም ማጥፋት ማስቆም- ፍትሃዊነትና እኩልነትን ለሁሉም እንዲሆን ማረጋገጥ" እንደማለት ነው)፡፡ ይህንን መፈክር እንደ አላማ አድርጎ የሚጠቀመው የዚህ ድርጅት ዋነኛ ተግባር ግን "ጽዮናዊነትን ማጠናከርና የእስራኤልን ዘረኝነትና ተስፋፊነት በአለም ዙሪያ ማስተጋባት ነው"፡፡[1]

Anti-Defamation League (ADL) በ1913 በአሜሪካ ውስጥ የተቋቋመ አይሁዳዊ ተቋም ነው፡፡ በአሜሪካ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምህዋሮች ውስጥ ከፍተኛ ተጽእኖ ካላቸው ግዙፍ ተቋማት መካከልም አንዱ ነው፡፡ ሊጉ በአሜሪካ ውስጥ ካሉት ከሰላሳ በላይ ቅርንጫፎች በተጨማሪ አይሁዶች በሚበዙባቸው ሶስት ሀገራት ውስጥም (እስራኤል፤ ሩሲያና ኢጣሊያ) ውስጥ በይፋ ይንቀሳቀሳል፡፡

ADL "ዋነኛው ዓላማዬ አይሁዶችን ከጥላቻ መታደግ ነው" ይላል፡፡ የጥላቻ ጥቃቶች በሌሎች የብሄረሰብና የእምነት ቡድኖች ላይ እንዳይደርሱ ለመከላከል በሚል በርካታ እንቅስቃሴዎችንም እንደሚያደርግ ይገልጻል፡፡ ድርጅቱን ከ"ሀ" እስከ "ፐ" የሚያውቁ ወገኖች ግን የድርጅቱን መሰሪነት ነው የሚናገሩት፡፡ እኒህ ወገኖች እንደሚሉት "ADL" ፀረ-ሴማዊነትን (ጸረ-አይሁድ አስተሳሰብን) ለማጥፋት በሚል ሽፋን "ሴማዊነት"ን (የአይሁድ የበላይነትን) በሁሉም ህዝቦች ላይ ለመጫን ሌት ተቀን የሚሰራ ጽዮናዊ ድርጅት ነው፡፡ በተለይ በእስራኤል መንግስት ህገወጥ ተግባራት ላይ ትችት የሚያቀርቡ ግለሰቦች፤ መንግስታትና ድርጅቶችን "ጸረ-ሴማዊ" እያለ ማጥላላት፣ ማንጓጠጥ፣ ማስፈራራትና "ጽንፈኛ"፣ "አክራሪ"፣ "አሸባሪ" የመሳሰሉ ቅጽሎችን መስጠት ቀዳሚ ተግባራቱ እንደሆኑ ያብራራሉ፡፡

ADL ፍልስጥኤማዊያንን ለሚረዳ ማንኛውም ተቋምና ግለሰብ ምህረት የለውም፡፡ የተባበሩት መንግስታት በእስራኤል ላይ እርምጃ ለመውሰድ ቀጠሮ ሲይዝ **ADL** በጓሮ በር ወደ "ዋይት ሀውስ" ይገባና "እስራኤል ማለት አሜሪካ ማለት ናት፡፡ ስለዚህ የቬቶው ነገር እንዳይረሳ!" በማለት ቀጭን ማስታወሻ ያስነግራል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለፍልስጥማዊያን ተጨቋኞች የሞራል ድጋፋቸውን ለመግለጽ ስብሰባ ሲጠሩ **AD**L የየተቋማቱን ዲኖች በስልክ ይገናኝና "ዋ! እንዲህ አይነት ስብሰባ በግቢያችሁ ቢካሄድ ከሚቀጥለው ሴሚስተር ጀምሮ የፌዴራሉ መንግስት

ለትምህርት ተቋማት የሚልከው ድጎማ ይቋረጥብሀል” የሚል ሽብር ነዝቶ ስብሰባዎቹን ያሰናክላል፡፡

“ADL” ሽብርተኝነትና ጽፈኝነትን ከሩቁ የማሸተት ሀይል አለኝ ባይ ነው፡፡ በመሆኑም “በጽንፈኝነት” ዙሪያ የአሜሪካ መንግስትን ያማክራል፡፡ በመረጃ ቋቱ (data base) ውስጥ “ጽንፈኛ”፤ “አሸባሪ”፤ “ጸረ-ሴማዊ” ወዘተ… የሚሉ ታርጋዎችን የለጠፈላቸውን የበርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ አከማችቷል፡፡ በጸረ-ሴማዊነት ጥርሳቸውን የነከሰባቸውን ሰዎች ንግግርና ድርጊት እየተከታተለ ይቀርጽና ከመረጃ ቋቱ ውስጥ መዝግቦ ያስቀምጣል፡፡ ከነዚህ ግለሰቦች መካከል ለአንዳንዶቹ ስም የማውጣቱን ስራ አጠናቋል፡፡ የሚጠብቀው ሰዎቹን ለቃቅሞ ቂሙን የሚወጣበትን አጋጣሚ ብቻ ነው፡፡ ከነርሱ መካከል አንዳንዶቹ በማስሚዲያ የምናውቃቸው ስሞች በመሆናቸው ብዙም አያስደንቁም፡፡ ነገር ግን “ADL” ለኛ በይፋ ላልተነገሩን በርካታ ግለሰቦችና ተቋማትም የጽንፈኝነት ታርጋ እየለጠፈ በመረጃ ቋቱ ውስጥ መዝግቦአቸዋል፡፡ ለምሳሌ ታዋቂው ሙፍቲ ዶ/ር ዩሱፍ አል-ቀርዳዊ በዚህ ጽዮናዊ ድርጅት ***“Theologian of Teror”*** ተብለው ተመዝግበዋል፡፡ [2]

ባጠቃላይ ከላይ የገለጽኩት አሜሪካዊው **ADL** ሁለመናው ጽዮናዊነት ነው፡፡ “ጽዮን.. እየሩሳሌም.. አንቺን ከረሳሁ.. ዳዊት ይርሳኝ…” አይነት ነገር ነው፡፡(አላህ ያጥፋው አቦ! ይሄ ሰላቢ!!)፡

ADL እና ጉደኛው “አህባሽ”

አሁን ከዋናው ነጥባችን ላይ ደርሰናል፡፡

ዛሬ ባቀረብኩላችሁ ጽሁፍ ገኖ የዋለው **ADL** በአካል ከኛ ርቆ ነው ያለው፡፡ የጽዮናዊነት ንቅናቄውንም ከኛ በሚርቁ ሀገራት ውስጥ ነው የሚካሄደው፡፡ ስለዚህ አጀንዳችን ሊሆን ባልተገባ ነበር፡፡ የኛ አጀንዳ ሆኖ ቢገኝስ ምን ትሉ ይሆን?

ወገኖቼ! በርግጥም በአህባሽ ምክንያት **ADL** የኛም ስጋት ሆኗል፡፡ ከማንም ጋር “እሸሼ ገዳሜ” ሲል የኖረውና የጽንፈኞች ጽንፈኛ የሆነው “አህባሽ” በጽዮናዊው ADL ስር በማህበርተኝነት ከታቀፉት አባል ድርጅቶች አንዱ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሁለቱ የፌስቡክ ቡድናችን አባላት ያጋለጡት ይህንን አስደናቂ ሚስጢር ነው፡፡ በህይወቴ እንደዚህ አይነት አስደናቂ ነገር ሲገጥመኝ ለሶስተኛ፤ ወይም ለአራተኛ፤ ወይም ለአምስተኛ ጊዜ ቢሆን ነው (ተጋነነ እንዳይባል ስለሰጋሁ ነው እንጂ በሶስተኛ ላይ ማቆም ይቻል ነበር)፡፡

“አህባሽ” በጣም ወራዳና አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን “ርካሽና ዝቃጭ” ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ የበለጠ ውርደት ከየት ይመጣ ይሆን? ይህንን ውርደት ለማየት የሚሻ በግርጌ ማስታወሻው ላይ

ያስቀመጥኩትን ድረ-ገጽ ይክፍትና በጥሞና ይመልከት፡፡[3] አህባሽን በጽዮናዊው **ADL** የፊላደልፊያ ቅርንጫፍ ቢሮ ስር ከተመዘገቡት ማህበርተኞች መካከል አንዱ ሆኖ ያገኘዋል፡፡

ከዝርዝሩ እንደምትረዱት

- አህባሽ Association of Islamic Charitable Projects በሚለው የእንግሊዝኛ ስሙ በአራተኛ ተራ ቁጥር ተመዝግቦ ይታያል። (ዝርዝሩ በእንግሊዝኛ ፊደላት ቅደም ተከተል የተጻፈ መሆኑን ልብ በሉ)።
- "ሙስሊም ማለት እኔ ብቻ ነኝ" እያለ በሙስሊሞች ላይ ተከፊር ከሚያውጀው "አሕባሽ" በስተቀር "ሙስሊም" ነኝ የሚል አንድም ድርጅት በዝርዝሩ ላይ የለም፡፡ ወላ ሱኒ! ወላ ሺዓ ማፊሽ! ሌላው ቀርቶ በኑፋቄ አቀንቃኝነታቸው የሚታወቁት የአህመዲያ ፊርቃ እና የጥቁር አሜሪካዉያኑ Nation of Islam እንኳ በዝርዝሩ ላይ የሉም፡፡ አስተግፊሩላህ!!!፡፡
- ከክርስትናው በኩልም *"Metropolitan Christian Council of Philadelphia"* ከተባለ ድርጅት በስተቀር ሌላ የክርስቲያኖች ቡድን የለም፡፡

- ከሁሉም የሚገርመው ለግብረ-ሰዶማዊያንና ለሴት ለሴት ጋብቻ ሙብት እንታገላለን የሚሉ ሁለት ድርጅቶችም በዝርዝሩ ላይ ያሉ መሆናቸው ነው፡፡

የአህባሽን ቅሌት አይታችሁታል አይደል? ሰልፉ የጽዮናዊያን ብቻ አይደለም፡፡ ሌሎች ወራዳዎችና ዝቃጮችም በጥምረቱ ውስጥ አሉ፡፡ የግብረ- ሰዶማዊያን ሙብት አስከባሪዎች!

ወርደት! ውርደት! እጅግ በጣም አሳፋሪ ውርደት! የግብረ-ሰዶማዊያንን" ሙብት እናስከብራለን ከሚሉ ድርጅቶች ጋር መሰለፍ ማለት ምን ማለት ነው? እስላማዊ ነኝ የሚል ድርጅት እንዲህ አይነት ነገር ይሰራል? የትኛው የቁርአን አያህ ነው ይህንን የሚፈቅደው? በየትኛው ሀዲስ ነው ይህ የተፈቀደው? አስተግፊሩላህ! እፍረት! እፍረት! ትልቅ እፍረት!!! ያ ረቢ ኢስቱርና! ኻቲማችንን አብጀው!

ጽዮናዊው **ADL** ሌሎችን ለማደናገር የፈለገ ይመስል አህባሽ የተሰለፈበትን ጥምረት No Hate Project ብሎታል፡፡ "ጥላቻ በኛ መሀል የለም" ለማለት ነው፡፡ በእውነትም ጥላቻ በነርሱ መሀል የለም፡፡ በኛና በነርሱ መሀል ግን ከእንግዲህ ወዲህ እርቅ የለም፡፡ ከእንዲህ አይነቱ ወራዳ ድርጅት ጋር የሚደራደር ሙስሊም ከእንግዲህ ወዲህ የለም፡፡

ድል የኢስላም ነው፡፡

---

1. ለማስረጃው የሚቀጥለውን የድርጅቱን የኢንተርኔት አድራሻ (ድረ-ገጽ) ከፍታችሁ ተመልከቱ፡፡ www.adl.org
2. ለዝርዝሩ ይህንን የድረ-ገጽ መግቢያ (ሊንክ) ይከፈቱ

   http://www.adl.org/main_Arab_World/al_Qaradawi

3. http://www.adl.org/philadelphia/coalition.asp

ታሪክ አለን!

ሙኒር አህመድ

ጥር 25/2004

ታሪክ አለን ኩሩ .....ብሩህ ታሪክ አለን እጅግ የገነነ
ህዝብን ያስጠለለ.....ኢስላምን ያዳነ
ያኔ በጨቅላ እድሜ.....በቡቃያው ዘመን
እኛ ሃበሾቹ ድንቅ ታሪክ አለን
አለን ድንቅ ታሪክ .....ኢስላም የማይረሳው
'ኢላ የውሚል ሚዓድ' እስከመጨረሻው
..ሁሉም የሚያወሳው

አይሁንብን ኩራት አይሁንብን ጉራ
ድንቅ ታሪክ አለን ሁሌም የሚዘከር ሁሌም የሚወራ
ያኔ በዚያ ዘመን ቁረይሾች ሲያምጹ
በነቢያችን ላይ ሃሰት እየነዙ
.....ሰይፍ ሲማዘዙ
ያኔኮ ነበርን እኛ ሃበሾቹ
ጋሻና መከታ የስደት ቤቶቹ
ባገር ሲዋረዱ ካገር ሲደደዱ
አብሽሩ መርሃባ ያለው ነጃሺ ወንዱ
የአበሻ ልጆች መች ሰው አስከፉና
.....መች ሰው አሳደዱ
ተንከባከቡ እንጂ ፍቅር ሰላም ሰጥተው
.....ቆርሰው ከማእዱ

ያኔ ህጻን ሳሉ ሰሃቢዩ ሙስጠፋ
ጡቶቿን ደግፋ አቅፋ ደግፋ
በእናትነት ክብር በእናትነት ፈንታ
ትልቅ ስፍራ ያላት በልባችን ቦታ
ይነገር ታሪኳ.... በከንቱ አይረሳ
ያሃበሻዋ እንስት ኡሙ አይመን ትወሳ
በረካ ሃበሻ ...ትልቅ ማስታወሻ

ደግሞ እንዴት ልተርክ የዛን ወጣት ፈንታ
የዛን ኩሩ ጀግና የቢላልን ቦታ
በአረቢያ ምድር በዛ በበረሃ

ጥላ በሌለበት በሚያሰኘው ውሃ
በዚያ የጭካኔ በዚያ የግፍ ውሎ
በበረሃው ድንጋይ የኋሊት ተንጋሎ
አሃድ አሃድ ያለን
ያ የረሱል ወዳጅ ያ የጥቁር ጀግና
አይረሳም ምንጊዜም ይዘከራል ገና

ይህቺ ታሪካዊት ይህቺ የሃበሻ ምድር
የኢስላም ባለውለታ ያላት ትልቅ ክብር
የታለ አሻራዋ የኢስላም ፋናዋ
የታለ መድረሳ ኮሌጅ መማሪያዋ

ይምጡ አገር አቋርጠው ይጎኙ ይማሩባት
በሃበሻ ምድር ኢስላም ያብብባት
..... ሰላም ይስፈንባት

ዛሬ ግን.....ዛሬ በዚህ ምትክ
ዛሬ በዚህ ፈንታ
የሐሰት ምስክር የቀበሮ ባህታ
እጁን ዘረጋልኝ በቃሉ ሊያጠምቀኝ
በረብጣ ዶላሩ ኢስላሜን ሊነጥቀኝ
ዛሬ ግን.....ዛሬ በዚህ ምትክ
ዛሬ በዚህ ፈንታ
የሐሰት ምስክር የቀበሮ ባህታ
እጁን ዘረጋልኝ በቃሉ ሊያጠምቀኝ
በአይሁድ ፍልስፍና ኢስላሜን ሊነጥቀኝ

ይገርማል.....ጠላቴ ደግ ሆኖ ለእኔ መልካም ሽቶ
በሀሰት ሊያጠምቀኝ ማሰልጠኛ ከቶ
እጁን ዘረጋልኝ ሊቀብረኝ ቆፍሮ
በአይሁድ ፍልስፍና በገንዘብ ታውሮ
ግና..... አስተማረኝ እንጂ ሀ ለ ሐ
ሁበል አላለኝም...አልጠራም ላት ዑዛ
ቀስ ብሎ እስከሚያረደኝ በዋዛ ፈዛዛ
ይሄ... ውለታ ነው
የሰይጣን ስጦታ የጠላቴ ሩጫ

ሁሉም ነቅቶበታል የለውም ማምለጫ

ይገርማል... ጠላቴ ደግ ሆኖ ለእኔ ይጨነቃል
በመጥገቤ ያዝናል በመራቤ ይስቃል
ስደሰት ይከፋል ሳዝን ይደሰታል
ይሄ ሁሉ ሆኖ በጣም ያዝንልኛል
እየገዘገዘ በደነዝ ያርደኛል
ዛሬ ግን በዛብኝ ውለታው ተሰማኝ
እምነቴን ህይወቴን ኢስላሜን ሊቀማኝ
አሁን ግን... በቅቶኛል
በስሜ እሚነግድ የአይሁድ ተባባሪ
ቅቤ አንጓች ከፋፋይ ሙስሊም መስሎ አዳሪ
የሰላም እንቅፋት የልማት ቀበኛ
ሆድ አምላኪ ከርሳም አታልይ ሙሰኛ
እንዲህ ያለ ወዳጅ.... ላገሬም አይበጃት
በሰላሳ ዲናር አስማምቶ እሚሸጣት

ባያውቀው ነው እንጂ.... ሃገር አይሸጥም
ዲን በርካሽ ነገር እንዲህ አይለውጥም
ሃገሬ እናቴ ናት ኢስላም ነው ህይወቴ
መቀለጃ አይደለም ክብሬ ነው ህይወቴ
ይኸው ነው አቋሜ ...
አምጣ ለጥፉልኝ ስም አውጡልኝ ዛሬ
አሸባሪ በለኝ ለፍፍ አውራ ወሬ
አዎ... አሸባሪ ነኝ ለፍፍ በደንብ አውራ
ነገ ግን ታፍረለህ ነገሩ ሲጣራ
አንገት ተደፋለህ በዱኒያም በአኼራ
አዎ.....አሸባሪ ነኝ ፀር ነኝ ለሙሽኛ
ሃገርና ዲኔን የምጠብቅ አርብኛ
አዎ.. አሸባሪ ነኝ ለሌባ የማልመች እንቅልፍ የማልተኛ

ለጥፍልኝ ሌላም ፈልግ ስም አምጣና
የሌላ አይነ ደረቅ ሃያዕ መች ያውቅና
አከራሪ ነው በለኝ አዎ አከራሪ ነኝ!
የሰው መብት የማልነካ የራሴን የማልሰጥ
ውሸት የማይጥመኝ እውነትን የምመርጥ

ጉባዔ ተሰብሰብ ሂድ ሌላ ስም አውጣ
አንገትክን ሳትደፋ ከመጅሊስ ሳትወጣ

ያኔ ትስቃለች ፀሃይ ጥርስ አውጥታ
አሳሪው ሲታሰር ታሳሪው ሲፈታ::

---

1. በወንድማችን ሙኒር የቀረበ ጣፋጭ ግጥም (ጥር 25/2004)

1987ን እንደ መስተዋት

የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄትየፊቸር ጸሐፊ ቡድን [1]

የካቲት 2004

ትኩስ የወጣትነት ዕድሜውን ማጣጣም ከጀመረ ገና ሦስት እና ዐራት ዓመታት ብቻ ናቸው የተቆጠሩት። ምጥጥ ባለው ገጽታው ዳርቻዎች ላይ ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት የፀጉር ልቃቂቶች ‹‹ደረስክ ደረስክ››የሚሉት ይመስላሉ። ዕድሜው የሃያዎቹን መጀመሪያ መርገጡ ቢሆንም ገጽታው እና አኳኋኑ ግን የእድሜውን ያህል ትንሽ አይደሉም። ወጣት ቢላል ዛሬ ደግሞ ሁለመናው ርብሽብሽ ብሏል። አጠር ባለው ቁመናው ላይ እንደ ነገሩ የሆነው አለባበሱ ተዳምሮ ሲታይ ጋብቻ ለመፈጸም አንድ ወር የቀረው ሙሽራ አይመስልም። በአእምሮውም ከአንድ ወር በኋላ ስለሚፈጽመው ጋብቻ ሳይሆን ከአንድ ቀን በፊት ስለተፈጠረው አሳዛኝ ክስተት ነው ደጋግሞ እያሰበ ያለው።

ቢላል የትናንቱ ዓይነት ክስተት እውን እንዳይሆን ከርዕይ አጋሮቹ ጋር በመሆን ብዙ ቢጥርም ሊሳካለት አልቻለም። እንዲህም ሆኖ ግን ላለፉት ዐራት ዓመታት ሌት ከመዓልት ሲተጋለት የነበረው ማኅበራቸው ‹‹በዚህ ዱብ ዕዳ ክስተት ምክንያት ይገታል››የሚል ግምት አልነበረውም። ለዚህም ነበር ገና ከማለዳው ጉዳዮቹን ከውኖ የማኅበሩ ጽ/ ቤት ወደሚገኝበት ጉለሌ ሰፈር ሲከንፍ የነበረው። ቢላል ግምቱ ስህተት እንደነበር የተረዳው የማኅበሩ ጽ/ቤት ሲደርስ ነበር። የጽ/ቤቱ ግቢ እና አካባቢው በሥርዓቱ ታጣቂዎች ተከብቧል። ቢላል ያለምንም ፍርሃት ወደ ማኅበሩ ጽ/ቤት ቅጽር ሲገባ ቢሮው ሳይሆን የፖሊስ ‹‹ፓትሮል››ነበር የተቀበለው። በዕለቱ ቢላልን ጨምሮ ከሰባት በላይ የማኅበሩ አባላት እና ሠራተኞች በሥርዓቱ ኃይሎች ተይዘው ወደ ማዕከላዊ ወህኒ ቤት ተወሰዱ።

ከቢላል እና ባልደረቦቹ መያዝ አንድ ቀን በፊት የካቲት 14፣ 1987 የተከሰተውና ለ10 ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የአንዋር መስጊድ ግርግር ያመጣው ዳፋና ድኅረ ክስተቱ ለቢላል እና ለባልደረቦቹ ወህኒ መውረድ ብቻ የተረፈ አልነበረም። ዛሬ የኢትዮጵያ ሙስሊም ለሚገኝበት የታሪክ እውነታ ማሳያ መስታወት ነው። ክስተቱን በቅርበት የሚያውቁት አንድ ምሁር ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የታሪክ መጠምዘዣ›› ሲሉ ከ 1997 የኢትዮጵያ ፖለቲካና ምርጫ ጋር ይመስሉታል –በብዙ መልኩ ወደ ኋላ የጎተተን መሆኑን በማስታወስ። ክስተቱ በደፈናው ‹‹በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ ውስጥ የተፈጠረ የሥልጣን ሽኩቻ››ተብሎ በወቅቱ በነበሩ የመንግሥት ብዙኃን መገናኛዎች ቢገለጽም ብዙዎች ግን ክስተቱን ከሕዝብ የ‹‹ሥልጣን ይገባኛል›› ጥያቄ ጋር አያይዘው ሊያነሱት ይሞክራሉ።

የደርግ ጉባዔ

በኢትዮጵያ ለዘመናት ነግሦ የቆየው ሰለሞናዊው ሥርዓተ መንግሥት ፍጻሜ በሆነው የኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሙብት እና ኅልውና ሥልታዊ በሆነ መንገድ ይገፋ ነበር። የሙብት ረገጣዎቹ መገለጫ ዓይነት ብዙ የነበረ ቢሆንም ሙስሊሙን ኅብረተሰብ መሪ ድርጅት አልባ ማድረግ ግን ዐቢይ የሥርዓቱ መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል። እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ መቆየት የቻለው የኃይለሥላሴ መንግሥት በወቅቱ በአገሪቱ በተከሰተው ድርቅ እና ችጋር፣ በከተማና በገጠር በተነሳው የተማሪዎችና መምህራን አመፅ፣ እንዲሁም የኤርትራ የነጻነት ጥያቄ ያስነሳው ውዝግብ የሥርዓቱን ውስጣዊና ውጫዊ ጥንካሬዎች መፈረካከስ ጀምረው እንደነበር ፕሮፌሰር ላጲሶ ጌ. ዴሌቦ ‹‹የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም››በሚለው መጽሐፋቸው አስነብበዋል። የሥርዓቱ ሁለንተናዊ በደል ገፈት ቀማሾች የነበሩት ኢትጵያውያን ሙስሊሞች ለመውደቅ መንፈቅ የቀረውን የኃይለሥላሴ መንግሽት ለመቃወም በሚያዝያ 12፣ 1966 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ) ሙስሊሞች የተገኙበት ትዕይንት ሕዝብ አካሄዱ። በትዕይንተ ሕዝቡ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ የሚገቡትን የዜግነት ሙብቶች ቢጠይቅም የኃይለሥላሴ መንግሥት ለጥያቄዎቹ በጎ ምላሽ ሳይሰጥ ቆይቶ በመስከረም 2፣ 1967 ፍጻሜውን አገኘ።

በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም የተቃኘው የደርግ መንግሥት ሥልጣን ላይ ሲወጣ የሕዝቡን የመደራጀት ጥያቄ ገሸሽ ማድረግ አልተቻለውም። ለዚህም ነበር እንደ ሌሎች ሲቪል ማኅበራት ሁሉ ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ›› በሚል ሥያሜ ሙስሊሞች መሪ ድርጅት ማቋቋም የቻሉት። በወቅቱ ከፍተኛ ጉባዔው ከመላው አገሪቱ በተመረጡ የሕዝብ እንደራሴዎች መመራት ባይችልም በመሐል አገር ሕዝብ የሚያውቃቸው ሐምሳ ዑለሞችና ኢማሞች ከየብሔረሰቡ ተወጣጥተው በመሪነት ቦታው ላይ መቀመጥ ችለው ነበር። ከፍተኛ ጉባዔው የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በውስጡ ለማሳተፍ 4 ዓይነት የአባልነት ኮታዎችን አስቀምጦ የነበረ ሲሆን፤ የከፍተኛ ጉባዔውን 50 በመቶ የአባልነት ወንበር የሚይዙት ዑለማዎች እንደሆኑ፣ 30 በመቶ ምሁራን፣ 10 በመቶ አዛውንቶች፣ እንዲሁም 10 በመቶ ወጣቶች በተቋሙ ውስጥ ውክልና እንዲኖራቸው ተደርጓል።

ይህ ከፍተኛ ጉባዔ በታላቁ ዓሊም ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ሊቀመንበርነትና በሐጂ ኢብራሒም ዐብዱሰላም ምክትልነት ይመራ የነበረ ሲሆን በወቅቱ በነበረው ፖለቲካዊ ጫና ምክንያት ከፍተኛ ጉባዔው ይህ ነው የሚባል ጠንካራ ተግባር ማከናወን ሳይችል ቀርቶ እንደነበር የድርጅቱን ታሪክ በስፋት የሚያውቁት ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ዘህረዲን ያስረዳሉ። እንደ ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ገለጻ ከፍተኛ ጉባዔው እስከ 1970ዎቹ መጨረሻ ድረስ ያለ አመርቂ ሥራ ቆይቶ በ 1970ዎቹ መባቻ ወጣቶች ተሳትፎ የሚያደርጉበት ‹‹የዳዕዋና ኢርሻድ ኮሚቴ››ተቋቁሞ እንቅስቃሴውን ማሳደግ ችሎ ነበር። ይህም እንቅስቃሴ ቢሆን በአንዋር መስጊድ ኢማምና በከፍተኛ ጉባዔው ሊቀመንበር ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ሕልፈት ተገታ።

የሊቀመንበሩን ሕልፈት ተከትሎም ተተኪያቸውን የማስቀመጡ ሂደት በጉባዔው አባላት መካከል ትልቅ አለመግባባትን ፈጠረ። ይህ ክስተት የተሠጋውን ያህል ግጭት ባይፈጥርም የአዲሱ ሊቀመንበር ሐጂ ዑመር ሑሴን መመረጥ ከውዝግብ የፀዳ አልነበረም። ሐጂ ዑመር የጠቅላይ ጉባዔውና የሸሪዓ ፍ/ቤት ሊቀመንበር ሆነው መሠየማቸው በጠቅላይ ጉባዔው አባላት መካከል ከፊል ቅያሜን አሳድሮ ቢቆይም የአዲሱ ከፍተኛ ጉባዔ ሕልውና በሕ.ወ.ሓ.ት መራሹ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አዲስ አበባን መቆጣጠር ተፈተነ። በወታደራዊው መንግሥት መውደቅ ማግሥትም ጉባዔው ‹‹ከደርግ መንግሥት ጋር መቀበር አለበት›› የሚለው የብዙዎች እምነት ሆነ። በተለይም ከደርግ መንግሥት የደኅንነት መሥሪያ ቤት ጋር የቀጥታ ግንኙነት የነበረው የሐጅና ዑምራ ኮሚቴ ይፈጽማቸው ከነበሩ አሥተዳደራዊ በደሎች እና ሃይማኖታዊ ጣልቃ ገብነቶች ጋር ተዳምሮ ሕልውናው እንዲያከትም መደረጉን ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ያስረዳሉ።

ሁለቱ አንጃዎች

ከፍተኛ ጉባዔውን አፍርሶና አመራሩን አውርዶ አዲስ የሥራ አመራር መዋቅር ለመፍጠር ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተወጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ በወቅቱ ሥራውን ጀምሮ ነበር። ይህ ኮሚቴ ራሱን ‹‹ጊዜያዊ የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ››በሚል ሠይሞ በፊት አውራሪ ሐጂ ሙሐመድ ራሕመቶ ሊቀመንበርነት እንቅስቃሴውን ማድረግ ጀመረ። በሌላ አቅጣጫም ወንበሩን ላለማስነጠቅ የሚሻው የከፍተኛ ጉባዔው አመራር ‹‹ከጊዜያዊ እስልምና ጉዳዮች ጉባዔ››ኮሚቴ ጋር ፍትጊያ እና ትንቅንቅ ውስጥ ገባ። ጊዜያዊ ኮሚቴውን የሚመሩት የወቅቱ የአዲስ አበባ መስጊዶች ሊቀመንበር እና ሰብሳቢ ፊት አውራሪ ሐጂ ሙሐመድ ራሕመቶም ኮሚቴውን በማስተባበር የጉባዔውን አመራሮች ከሥልጣን ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረታቸውን ቀጠሉ።

ይህን በሁለቱ አጀንዳዎች መካከል የተከሰተውን የ‹‹ሥልጣን ይገባኛል››ውዝግብ ለመፍታት የወቅቱ የክልል 14 መሥተዳድር የአሥተዳደርና የፖሊስ ኃላፊዎች አቶ ኻሊድ ዐብዱራሕማንና አቶ ሐሰን ሺፋ ጣልቃ በመግባት ከሁለቱም አንጃዎች አምስት አምስት ሰዎች ተውጣጥተው ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ እንዲያዋቅሩ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። የዚህ አስመራጭ ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊቀመንበር ከከፍተኛ ጉባዔው አንጃ እንዲሆን ሲወሰን ምክትል ሊቀመንበሩ ደግሞ ከተቃዋሚው (ከጊዜያዊ የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ) ወገን እንዲሆን ይደረጋል። በሌላ አቅጣጫም በ 1936 በንጉሡ የወጣውን የናኢባና የሸሪዓ ፍርድ ቤት አዋጅ ለመመርመርና ለማጠናከር በሚያዚያ 1984 በተቋቋመ ኮሚቴ ውስጥ የሕዝብ ግንኙት ኃላፊ ሆነው ተመርጠው የነበሩትና ኋላም ሰብሳቢ የሆኑት የትግራይ ተወላጅ ግራዝማች ሐዲስ ኑርሑሴን ‹‹የታሪክ ማስታወሻ፤ የብሔርና የሃይማኖት ጭቆና በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ ባዘጋጁት ረቂቅ ድርሳን የወቅቱ የቅዱስ ቁርአን ማኅበር ሊቀመንበር ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ የአስመራጭ ኮሚቴ ውስጥ ለመግባት ጥረት አድርገው በአቶ ሐሰን ሺፋ ከልካይነት መሳተፍ ሳይችሉ ቀርተው እንደነበር ጽፈዋል። ግራዝማች በተጨማሪም የማስመረጥ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ ከሁለቱም ወገኖች ከተመረጡት አሥር ግለሰቦች መካከል የአብሬት ሸኽ ልጅ ከሆኑት ሰይድ መዚድ በስተቀር ሁሉም በአጭር ጊዜ

ውስጥ የሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ አቀንቃኝ ሊሆኑ እንደቻሉ ጽፈዋል። የአስመራጭ ኮሚቴው ምክትል ሊቀመንበር የነበሩት ሸኽ ሙሐመድ ዘይን በበኩላቸው አሥሩ አስመራጭ አባላት ዐራት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከወረዳ አንስቶ የተመረጡ 500 የሚደርሱ አባላት ያሉት ጠቅላይ ጉባዔ በማዋቀር ፍትሐዊ ምርጫ ማካሄዳቸውን ይገልጻሉ –አድሎአዊነት ያልነበረ መሆኑን በማስገንዘብ።

ከሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የተወጣጡ አምስት መቶ አባላት ያሉትን ጠቅላላ ጉባዔ ያዋቀረው አስመራጭ ኮሚቴ ቅድመ ሁኔታዎችን በመስቀመጥ ሊቀመናብርቶችና ሥራ አስፈጻሚ አባላትን አስመረጠ። አስመራጭ ኮሚቴው እንደ ዋና መሥፈርት አስቀምጦት የነበረውና ከፊል ውዝግብ አስነስቶ የቆየው ቅድመ ሁኔታ ‹‹ሊቀመንበሩና ምክትል ሊቀመንበሩ ዓሊም መሆን አለባቸው››የሚለው ነበር። ይህ ቅድመ ሁኔታ ከመመሪያው እንዲወጣ የሚፈልጉ ግለሰቦች ብቅ ብለው የነበረ ሲሆን ዋነኛ ምክንያታቸውም ‹‹ዑለሞች መች መምራት ይችሉና?›› የሚል ነበር። ሆኖም በጠቅላላ ጉባዔው ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ዑለሞች ‹‹መቼ የመሪነቱን እድል ሰጣችሁን?!›› የሚል ሙግት በማንሳት ቅድመ ሁኔታው እንዲጸና አደረጉ። በወቅቱ የአስመራጭ ኮሚቴው አባል የነበሩ አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ የማይሹ ግለሰብ መሥፈርቱን ከመመሪያው እንዲያወጡ ማስፈራሪያና ዛቻ ደርሶባቸው እንደነበር በመግለጽ የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት ገብተውበት የነበረውን ፍርሃትና ሥጋት ያስታውሳሉ። ይህንኑ መሥፈርት አስመልክቶ በጥቅምት 1985 የወጣው ‹‹ቢላል››መጽሔት ‹‹ምርጫው እንዲሳካ›› በሚል ርዕስ ‹‹ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ወክሎ የሚቀመጥ ሰው ከማንምና ከምንም የጠራና ስለሃይማኖቱ ብቁ እውቀት ያለው፣ ጥቅም የማያሸንፈው፣ በዘር በጎሣ የማያምን፣ ዲኑን ለማገልገል ፍላጎት ያለው››መሆን እንዳለበት በማስገንዘብ ለተቀመጠው መሥፈርት ያለውን ድጋፍ ለማሳየት ሞክሯል።

በአዲሱ አስመራጭ ኮሚቴ ከከፍተኛ ጉባዔነት ወደ ጠቅላይ ጉባዔነት ሥያሜ ለተለወጠው የሕዝበ ሙስሊሙ ተቋም መሪነት ቦታ ከጥቅምት አምስት እስከ ጥቅምት ስምንት 1985 ለዐራት ቀናት በተደረገው ጉባዔ እና ምርጫ ሸኽ ሙሐመድ አሕመድ ሰዒድ ሊቀ መንበር፣ ሐጂ ሙሐመድ ሐሰን ደግሞ ተቀዳሚ ሊቀመንበር ተደርገው ተመርጠዋል። ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ በበኩላቸው ሁለተኛ ምክትል ሊቀመንበርና የተቋሙ የኢኮኖሚ (ፋይናንስ) ዘርፍ ኃላፊ ሆነው ተመርጠዋል። ጉባዔው ከሾማቸው ሰባት የሥራ አስፈጻሚ አባላት በተጨማሪም ሃያ ስምንት የሥራ አመራርና ሰባት የአሥተዳደር ዘርፍ ሠራተኞችን መርጧል። ምርጫው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ያልነበረበት ቢሆንም ሂደቱ በውንብድና የተሞላ እንደነበር የሚናገሩ አልጠፉም። የጉባዔውንና የምርጫውን ሙሉ ሂደት የታዘበ የቀድሞ የ‹‹ቢላል›› መጽሔት አዘጋጅ ‹‹በምርጫው የመጨረሻ ሰዓታት በተሠራ አስገራሚ ድራማ ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃና ደጋፊዎቻቸው ተመርጠው የምርጫው ሒደት ተጠናቀቀ›› በማለት ለየሙስሊሞች ጉዳይ ትዝብቱን አጋርቷል። የአስመራጭ ኮሚቴው ምክትል ሊቀመንበር የነበሩት ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ኮሚቴው አስቀምጧቸው ከነበሩት ሁለት ዐቢይ ዓላማዎች አንዱን፣ ማለትም ጠቅላይ ጉባዔውን አገር አቀፍ በሆነ መልኩ በማዋቀር ረገድ የተሳካለት መሆኑን ሲገልጹ ለጠቅላይ ጉባዔው ጥራት ያላቸው መሪዎች በማስመረጥ በኩል

ግን ብዙም ሊሳካላቸው እንዳልቻለ ያስረዳሉ። ለዚህም ለተቋሙ በሊቀመንበርነት የተመረጡትን የሐጂ ሙሐመድ አሕመድ ሰዒድን አሥተዳደራዊ ብቃት አናሳነት በዋቢነት ይጠቅሳሉ። ይህም በተግባር መታየቱን የሚገልጹ በርካቶች ናቸው።

አዲሱ ጠቅላይ ጉባዔ (መጅሊስ) ከመንግሥትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ባገኘው ድጋፍ በኅዳር 1985 ወደ ሥራ በገባበት ወቅት ነበር ለየካቲት አሥራ ዐራቱ የአንዋር መስጊድ ግርግር መነሻ ክብሪት የተጫረው። የጠቅላይ ጉባዔው የሥራ አመራር ቦርድ ሥራውን በጀመረበት ወቅት ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባ አጀንዳ አድርጎ አስቀምጦ የነበረው የአቻ ማኅበራትን ጉዳይ ነበር። ጉባዔው በደርግ ውድቀት ማግሥት የተቋቋሙ የተለያዩ ኢስላማዊ ማኅበራት የሚሠሩት ‹‹የእኔን ሥራ በመሆኑ የሥራ ምስስሎሽ ያላቸው ማኅበራት አያስፈልጉም››በሚል ምክንያት ማኅበራቱ እንዲፈርሱ ውሳኔ አሳለፈ። እንዲፈርሱ ከተወሰነባቸውና በወቅቱ ከፍተኛ እውቅና አግኝተው ከነበሩ ማኅበራት መካከል ‹‹ሙነዘመተ ሽባብ››በጉልህ ይጠቀሳል።

ወጣቶቹ

ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ በግንቦት 1983 ደርግ ወድቆ የምኒልክ ቤተ-መንግሥት ከገባ በኋላ በተዋቀረው የሽግግር መንግሥቱ ቻርተር የመደራጀት ነጻነት በመከበሩ በርካታ ማኅበራትና ሲቪል ተቋማት ፈቃድ አውጥተው መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር። የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ድርጅት (ኢ.ሙ.ወ.ድ) (ወይም በተለምዶ አጠራሩ ሙነዘማ) ከእነዚህ የመጀመሪያዎቹ ማኅበራት አንዱ ነበር። ማኅበሩ ምንም እንኳ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግን ወደ አዲስ አበባ መግባት ተከትሎ ፈቃድ በማውጣት በሕጋዊነት መንቀሳቀስ ቢጀምርም ምሥረታው በደርግ የመጨረሻዎቹ የአገዛዝ ዓመታት እንደ ነበር የማኅበሩ የዳዕዋ ሥርጭት ክፍል ውስጥ ያገለግል የነበረው ወጣት ቢላል ተማም ይገልጻል። እንደ ቢላል አባባል በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይማሩ የነበሩ ሙስሊም ወጣቶች የማኅበሩን የምሥረታ እና የዓላማ ጥንስስ በውይይት ያዳብሩት ነበር።

ኢ.ሙ.ወ.ድ (ሙነዘማ) ፈቃድ አውጥቶ ሕጋዊ እውቅና ካገኘ በኋላ ሙስሊም ወጣቶችን በእምነት የማጽናት ዓላማ በመያዝ የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ጀምሮ ነበር። ከእነዚህም ሥራዎቹ ውስጥ ለወጣቶች በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ አጫጭር እና ረጃጅም ሥልጠናዎችን ማዕከሉ በሚገኝበት ጉለሌ ይሰጥ ነበር። እነዚህን ሥልጠናዎች ለመካፈል እና የማኅበሩም አባል ለመሆን በርካታ ወጣቶች ከመላዋ አገሪቱ ወደ ማኅበሩ ጽ/ቤት ይጎርፉ ነበር። በኢትጵያ ሙስሊሞች ወጣት ድርጅት ውስጥ ለአንድ ወር ከሃያ ቀን ያህል የተርቢያ ሥልጠና እንደወሰደ የሚናገረው የ 33 ዓመቱ ጎልማሳ ረጀብ ኸድር ሥልጠናውን ከማግኘቱ በፊት የነበረውን አናሳ እውቀትና ለሃይማኖቱ የነበረውን ግዴለሽነት በማስታወስ በሥልጠናው በመሳተፉ ያገኘውን ሃይማኖታዊ እውቀትና ቅንዓት ይጠቁማል። ‹‹ሙነዘማ እስከ ዛሬ ቢኖር ኖሮ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሃይማኖተኛ እና ዓሊም ወጣቶችን ማፍራት ይቻል ነበር››በማለትም ሐሳቡን ይሰነዝራል። የወጣቶቹ ድርጅት ከሚሰጣቸው የተመላላሽ እና የአዳር ሥልጠናዎች በተጨማሪም ‹‹የጁሙዓ መልዕክት››በሚል

ርዕስ በየሳምንቱ ዐርብ በምትሠራጭ በራሪ ወረቀት እና ‹‹አድ ዳዕዋ››የሚል ሥያሜ በነበራት የድርጅቱ ወርሐዊ መጽሔት ሰበካ ያካሂድ የነበረ ሲሆን ጠጠር ያሉ ኢስላማዊ ጉዳዮች የሚነሱባቸው ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችንም በቋሚነት ያሰናዳ ነበር።

እነዚህ የድርጅቱ እንቅስቃሴዎች በወጣቶች በኩል ሰፊ ተቀባይነትን ከማግኘታቸውም በላይ የወጣቶችን የዲን ትጋት በማሳደግ ረገድም ከፍተኛውን ሚና ተጫውተው እንደነበር ድርጅቱን በቅርበት ያውቁ የነበሩ አንድ ምሁር ያስረዳሉ። ምሁሩ የማኅበሩን ሥልጠና ያገኙ ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ ማኅበሩን ያገለግሉ የነበሩ ወጣቶች ሙሉ ጊዜያቸውን ለማኅበሩ አገልግሎት ሰጥተው እንደነበር ያወሳሉ። ወጣት ቢላል በበኩሉ የድርጅቱ አገልጋዮች የመኝታ ሰዓት እንኳ እንዳልነበራቸው ከመግለጽ አይቦዝንም። ‹‹ትዳር ያለው ትዳሩን፣ ሥራ ያለው ሥራውን ትቶ ለማኅበሩ እንቅስቃሴ ደፋ ቀና ይል ነበር›› በማለት የወቅቱን ሁኔታ ለማስቃኘት ይሞክራል።

የወጣት ድርጅቱ ከሌሎች አቻ ማኅበራት በተለየ መልኩ ያደርገው የነበረው እንቅስቃሴ በመንግሥትና በሌሎች ወገኖች ትኩረት ውስጥ ከትቶት እንደነበር የሚናገሩት ምሁሩ በተለይም ማኅበሩ በአደባባይ ውይይት ያደርግባቸው የነበሩ ሽሪዓ-ነክ ጉዳዮች በጠላቶች ዒላማ ውስጥ ከትተውት እንደነበር ሳይገልጹ አያልፉም። እንደ ምሁሩ ገለጻ ሁኔታውን ለማርገብ ጥቂት ግለሰቦች ወደ ማኅበሩ ሊቀመንበር ሸኽ ሰይድ አሕመድ ሙስጠፋ በመሄድ የማኅበሩን አካሄድ ለማለሳለስ ቢጥሩም ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ሁኔታዎች ግን ከመርገብ ይልቅ ተካርረው መሄዳቸውን ቀጠሉ።

በኅዳር 26፣1985 በሕንድ የዐራት መቶ ዓመታት እድሜ ያለው የአዮዲያ መስጊድ በሒንዱ ጽንፈኞች መፍረሱን ተከትሎ ኢ.ሙ.ወ.ድ (ሙነዘማ) ድርጊቱን የሚቃወም ትዕይንት ሕዝብ ለማካሄድ በታኅሣሥ 4፣ 1985 በአዲስ አበባ ከተማ ሰልፍ ጠራ። ይህ ድርጊት ሙስሊም ባልሆኑ ወገኖች ብቻ ሳይሆን በሙስሊሙ በኩልም ተቃውሞ ገጠመው። የማኅበሩ መሥራች አባል እንደሆኑ የሚናገሩትና የማኅበሩ መማክርት ጉባዔ ምክትል ጸሐፊ የነበሩት ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ የሰልፉን ሐሳብ ውድቅ በማድረግ የማኅበሩ አመራሮች የሰልፉን ሐሳብ እንዲሰርዙ ቢወተውቱም ሊሳካላቸው አልቻለም ነበር። ሐጂ ሙሐመድ አወል በአመለካከት ረገድም የወጣት ድርጅቱ የ‹‹ሠለፊያ››ን አስተሳሰብ ለማስፋፋት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ብልሃት ያልታከለበት መሆኑንና የሌሎችንም ቡድኖች አስተሳሰብ መጫን እንደሌለበት የሚያስታውሱ ተደጋጋሚ ምክሮችን ለድርጅቱ አመራሮች መለገሳቸውን ይናገራሉ። ሐጂ ሙሐመድ አወል በወቅቱ ሰላማዊ ሰልፉ እንዲሰረዝ አቅርበዋቸው ከነበሩ መከራከሪያዎች መካከል ‹‹የኢትዮጵያን ሙስሊም ጥያቄ ሳንመልስ የሌሎች አገራትን ሙስሊሞች ጥያቄ ማንሳት ከመርሕ አንፃር ተገቢ አይደለም››የሚለው ይገኝበት የነበረ ሲሆን ዋነኛ መሟገቻ ነጥባቸው የነበረው ግን ‹‹ሰልፉ ትኩረት ውስጥ ይከትተናል፣ ያስመታናል›› የሚል እንደነበር ሐጂ ሙሐመድ አወል ዛሬ ላይ ሆነው ያስታውሳሉ።

ውዝግብ ያስነሳው ሰልፍ በመጀመሪያ ፈቃድ ተከልክሎ እንደነበር የሚገልጸው ቢላል በበኩሉ ድርጅቱ ግን ፈቃዱን ቢነፈግ እንኳ ሰልፉን ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይል በማሳወቁ ሰልፉ

ፈቃድ አግኝቶ በታኅሣሥ 4 ሊካሄድ መቻሉን ያስረዳል። ከ 30 ሺህ በላይ ሰዎች በተሳተፉበት በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ለወቅቱ የሕንድ እና የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተሮች የተጻፉ ደብዳቤዎች ተነበዋል። ‹‹ሰልፉ የሚጠበቅበትን ውጤት ባያመጣም ድምጻችንን አሰምተን ተመልሰናል››ይላል ቢላል –ዓላማውን ከውጤቱ ጋር እያነፃጸረ። ሌሎች ወገኖች ደግሞ ሰልፉ በስሜት ብቻ የተደረገ እንደነበር በመጥቀስ ወቀሳቸውን በሙነዘማ ላይ ይሰነዝራሉ። ምሁሩ በበኩላቸው ‹‹የቦስኒያን ጭፍጨፋ በመሰሉ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ድርጅቱ መንጠልጠል ያበዛ ነበር›› በማለት አካሄዱን ይወቅሳሉ። የዚህ ሰላማዊ ሰልፍ መከናወን አዲሱን ጠቅላይ ጉባዔ በምክትል ሊቀመንበርነት በሚመሩት በሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃና ሙነዘማን በመሰሉ አቻ ማኅበራት መካከል የተፈጠረውን ክፍተት የበለጠ አሰፋው።

3+8>0

በ 77 ዓመቱ ኅልማሳ ሐጂ ሙሐመድ አሕመድ ሰዒድ የሚመራው አዲሱ ጠቅላይ ጉባዔ ላይ ገና ከጅምሩ የአመራር ምርጫውን አስመልክቶ ቅራኔ የነበራቸው ማኅበራት ተቋሙ በምሥረታው የመጀመሪያ ስብሰባ የማኅበራቱን አላስፈላጊነት በመግለጽ እንዲፈርሱ መወሰኑ የማኅበራቱን ጥርስ አስነከሰበት። መጅሊሱ ይህን ውሳኔ ሲያሳልፍ ምንም ዓይነት የሕግ ማእቀፍ አልተከተለም ነበር። የኢትዮጵያ ዑለማዎች ማኅበር እንዲፈርሱ ከተወሰነባቸው ማኅበራት አንዱ ሲሆን ከወሎ አውራጃ በመወከል ከ 1966 ጀምሮ በከፍተኛ ጉባዔው የሐጅና ዑምራ ዘርፍ ውስጥ ያገለገሉት ሐጂ ምቾት አሕመድ ጠቅላይ ጉባዔው ‹‹የዑለማ ም/ቤቱ ፈርሶ ጠቅላይ ምክር ቤቱ ውስጥ ይጠቃለል››በሚል ያሳለፈው ውሳኔ ዑለማዎችን በሙሉ አስቆጥቶ እንደነበር ያስታውሳሉ። ‹‹ውሳኔው የዑለማዎችን ክብር የነካ ነበር።››

ሌሎች ወገኖች በበኩላቸው ጠቅላይ ጉባዔው ኢስላማዊ ማኅበራት በሙሉ እንዲፈርሱ ሲወስን በሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ የሚመራው ማኅበር እንዲፈርስ አለመወሰኑ የማኅበሩ አመራሮች በሐጂ ሙሐመድ አወል ላይ እንዲያተኩሩ ምክንያት ሆኗቸዋል። በሂደት የጠቅላይ ጉባዔውን ውሳኔ የተቃወሙና ሌሎች የጠቅላይ ጉባዔው ሕጋዊነት ላይ ጥያቄ ያነሱ አምስት ማኅበራት የጠቅላይ ጉባዔውን ሕልውና ለመታደግ ግንባር ፈጠሩ። እነዚህ ማኅበራት የኢትዮጵያ ዑለማዎች ማኅበር፣ የኢትዮጵያ አንሷረ ሱንና ማኅበር፣ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ድርጅት (ሙነዘማ)፣ የኢትዮጵያ ዳዕዋና እውቀት ማኅበርና በግራዝማች ሐዲስ ኑርሑሴን የሚመራው የሸሪዓ ፍርድ ቤትን አቅም ለመመርመርና ለማጠናከር የተቋቋመ ኮሚቴ ናቸው። እነዚህ ግንባር የፈጠሩ ማኅበራት ተጠሪዎችና ሌሎችም የሙስሊም ኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶ ተከታታይ ውይይቶች መካሄድ ጀመሩ። በማኅበራቱ አደረጃጀት የሚካሄዱት እነዚህ የውይይት መድረኮች በሙስሊሙ ኅብረተሰብ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመምከር ሙስሊሙ ኅብረተሰብ መብቱን ለማስከበር ሰላማዊ ሰልፍ ማካሄድ አለበት በሚል ደመደሙ።

ማኅበራቱ በጥምረት ሰኞ ኅዳር 19፣ 1987 ሰልፍ ለማድረግ ከክልል 14 መሥተዳድር ‹‹ከአሥር ሺህ ያላነሰ ሰው የሚሳተፍበት›› የሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ አወጡ። አዘጋጆቹ በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ ለሚገኙ መስጊዶች እና የሙስሊም እድሮች የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ በማቅረብም ሕዝቡን አዘጋጁት። በሰላማዊ ሰልፉ ዕለት በመርካቶ እና ዙሪያዋ የሚገኙ ሱቆች ለወትሮው ከሚከፈቱበት ሰዓት ዘግይተው እንደነበር የሚገልጸው ሁኔታውን በወቅቱ የተመለከተው የ‹‹ቢላል›› መጽሔት አዘጋጅ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ሰልፉ ወደሚጀመርበት የማዘጋጃ ቤት ሜዳ ይተም እንደነበር ያስታውሳል። በወቅቱ በማዘጋጃ ቤት ሕንፃ ላይ ይገኝ የነበረው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከሕንፃው አናት ላይ ሆኖ ያነሳው ተንቀሳቃሽ ምስል ከፒያሳ አራዳ ገበያ እስከ ለገሐር የተዘረጋው ኅዳና በሰልፈኞች ተሞልቶ እንደነበር አሳይቷል። ‹‹የሕዝቡ ቁጥር ከፍተኛ መሆን የጥያቄውን ሕጋዊነት ያሳያል›› የሚሉት ሐጂ ምቾት የሕዝቡ ቁጥር ከፍተኛነት መንግሥትን ብቻ ሳይሆን የሰልፉን አዘጋጆች ጭምር ያስደነገጠ እንደነበር ሳይጠቅሱ አያልፉም።

የሰልፈኛው ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ መሆን የሰልፈኞች ተወካዮች ከጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ይልቅ ፕሬዚደንቱ አቶ መለስ ዜናዊ ተቀብለው እንዲያናግሯቸው ምክንያት መሆን እንደቻለ ብዙዎች ያምናሉ። ሰልፈኞቹ በተወካዮቻቸው አማካኝነት 11 ጥያቄዎቻቸውን ለፕሬዚደንት መለስ ዜናዊ አቅርበው የነበረ ሲሆን ዋነኛ አንኳር ጥያቄ አድርገው ያነሱትም የጠቅላይ ጉባዔውን በአንድ ግለሰብ መዳፍ ውስጥ መውደቅ ነበር። ፕሬዚደንቱ በምላሻቸው የጠቅላይ ጉባዔውን አመራሮች ‹‹እናንተው እንደሾማችሁ እናንተው ልታወርዷቸው ትችላላችሁ››በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተው እንደሸኟቸው ኅዳር 20፣ 1987 ታትሞ የወጣው ‹‹አዲስ ዘመን››ጋዜጣ አስነብቦ ነበር። በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ እና ግርግር ተደጋግሞ ይነሳ የነበረው የሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ ስም ነበር። የማኅበራቱ ተወካዮችም ‹‹ጠቅላይ ጉባዔውን በመዳፋቸው ሥር አስቀምጠውት አምባገነናዊነትን አስፍነዋል››እያሉ ሲከሷቸው ተሰምቷል።

ከ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በሸቀጣ ሸቀጦች ንግድ የተሠማሩትና በ 1961 ለንጉሡ ፓርላማ የትግራይን አውራጃ ወክለው የተወዳደሩት፣ የኋላ ኋላም በአስመጪና ላኪነት ንግድ ተሠማርተው የነበሩት ሐጂ ሙሐመድ አወል ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ እና ከ1987 የአንዋር መስጊድ ግርግር ጋር ተያይዞ ሥማቸው ተደጋግሞ ይነሳል። የዛሬው የ80 ዓመት ጎልማሳ ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፎ ማድረግ የጀመሩት ከትውልድ ቀዬአቸው ትግራይ ክልል ነበር። በትግራይ ክልል በተለያዩ የግብረ ሰናይ ሥራዎች ተሳትፎ ሲያደርጉ ቆይተው በ 1970ዎቹ መጨረሻ ከሰባት ከማይበልጡ ሰዎች ጋር የኢትዮጲያ ቅዱስ ቁርኣን ማኅበርን መመሥረታቸውን ኅዳር 1985 ለታተመው ‹‹ቢላል›› መጽሔት ገልጸው ነበር። ከ1980 ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ በተራ አባልነት ማገልገላቸውንም ጨምረው ያስረዳሉ።

ሐጂ ሙሐመድ አወል ድርጅታቸው ቅዱስ ቁርኣን ማኅበር ከ 1982 አንስቶ ሲያደርጋቸው የነበሩ

እንቅስቃሴዎች ዘርፈ ብዙ እና አመርቂ እንደነበሩ ያስታውሳሉ። በወቅቱ በመላዋ አገሪቱ 157 መድረሳዎችና 40,000 (ዐርባ ሺህ) የቁርአን ተማሪዎችን ያስተምሩ እንደነበር የሚገልጹት ሐጂ ሙሐመድ አወል ይህ እንቅስቃሴያቸው መንግሥትንና ቤተ-ክህነትን ከፍተኛ ሥጋት ውስጥ ከትቷቸው እንደነበር ያሰምሩበታል። ‹‹ይህን ሥጋታቸውን ለመቅረፍ እኔን ከኃላፊነት ቦታዬ የማውረድ እቅድ ነበራቸው››ይላሉ ሐጂ ሙሐመድ በማኅበራቱ የተደረገውን ተቃውሞ ሰልፍ አስመልክቶ ምላሽ ሲሰጡ። ሌሎች ወገኖች የኅዳር አሥራ ዘጠኙ ተቃውሞ ሰልፍ የጥቂት ማኅበራት ሳይሆን የሕዝብ የሙበት ጥያቄን የታከከ ስለመሆኑ ቢከራከሩም ሐጂ ሙሐመድ ግን ከእንቅስቃሴው ጀርባ የቅዱስ ቁርአን ማኅበርን ሰፋፊ ሥራዎች ለማስቆም የታለመ ሤራ እንደነበር ያስረዳሉ። ‹‹በኅዳር አሥራ ዘጠኝ የተቃውሞ ሰልፍ የማኅበሩ አመራሮች እኔን ማስወገድ ይችሉ የነበረ ቢሆንም በሰሩት ስህተት ምክንያት ያሰቡት ሳይሳካላቸው ቀርቷል››የሚሉት ሐጂ ሙሐመድ ተወካዮቹ ካቀረቧቸው አሥራ አንድ ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱ ብቻ እርሳቸውን የሚመለከቱና ቀሪዎቹ ግን ስሜት የተንጸባረቀባቸው፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ሊተገበሩ የማይችሉ የነበሩ መሆናቸውን ያነሳሉ። ‹‹እስቲ አሁን ‹ሙስሊም ሚኒስትሮች ይሾሙልን›ብሎ መጠየቅ ምን ይባላል?››ይላሉ።

ከተቃውሞ ሰልፉ በኋላ የማኅበራቱ ጥምረት ከመንግሥት ባገኘው አዎንታዊ ምላሽ በመነሳት ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃን ከሥልጣን የማውረድ እንቅስቃሴ ጀመረ። ጠቅላይ ጉባዔው የሙስሊሙ ሕዝብ የጋራ ተቋም እንደመሆኑና ጉዳዩም የወቅፍ ጉዳዮችን በሚያየው የሸሪዓ ፍ/ቤት ሥልጣን (Jurisdiction) ሥር በመሆኑ የኢስላማዊ ድርጅቶቹ ጥምር ኮሚቴ ጉዳዩን ለሸሪዓ ፍ/ቤት አቀረበው። ግራዝማች ሐዲስ ኑርሑሴን ባዘጋጁት ረቂቅ መጽሐፍ አባሪ ተደርጎ የቀረበው የሸሪዓ ፍ/ቤት ውሳኔ ሐጂ ሙሐመድ አወል በማኅበራቱ አማካኝነት በሸሪዓ ፍ/ቤት ለቀረበባቸው ክስ ችሎት ቀርበው ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ እንደቀሩ ተገልጿል። የሸሪዓ ፍ/ ቤቱ ጉዳዩን ተከሳሹ በሌሉበት ተመልክቶ በሰኔ 2፣ 1986 ሐጂ ሙሐመድ አወል ከሥልጣናቸው እንዲነሱ እና ከሳሾቹ ድርጅቶችም አዲስ ጠቅላይ ጉባዔ እንዲያደራጁ ውሳኔ አስተላለፈ። ይህ ውሳኔ ከዐራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፖሊሶች በተገኙበት የጠቅላይ ጉባዔው በር ተሰብሮ በአዲስ ቁልፎች ተቀይሮ ተፈጻሚ ሆነ። ሐጂ ሙሐመድ አወል ግን የቢሮ ሰበራው የፍ/ ቤት ትዕዛዝ አካል እንዳልነበር ይገልጻሉ። ያም ሆኖ ግን ሁኔታው ሐጂ ሙሐመድ አወልን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ከመሄድና ይግባኝ ከመጠየቅ አልገታቸውም። የሐጂ ሙሐመድ አወል ይግባኝ በመደበኛ ፍ/ቤት መታየት መጀመሩ እና ‹‹የሸሪዓ ፍ/ቤትን ሥልጣንና ተግባር የሚያቃልል ነው›› መባሉ ደግም በተራው ትልቅ የውዝግብ ምንጭ ሆነ። በተለይም የሸሪዓ ፍ/ቤት ውሳኔ አስገዳጅ ሆኖ አለመገኘት ትልቅ ነውጥ ፈጥሮ እንደ ነበር ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ያስረዳሉ።

በዕለቱም እንዲህ ሆነ!

በመደበኛ ፍ/ቤት መታየት የጀመረው የሐጂ ሙሐመድ አወል ይግባኝ የሸሪዓ ፍ/ቤቱን ውሳኔ

ውድቅ ባደረገ መልኩ የራሱን ውሳኔ ማሳለፉ ብዙዎችን ያስደነገጠ ነበር። በፍ/ቤቱ ውሳኔ ዐራተኛ ገጽ ላይ ‹‹የናኢባና የቃዲ ጉባዔ ቤቶች የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን የጋብቻ፣ የቀለብ መቁረጥ፣ የሕፃናት አሥተዳደርን፣ ስለ ወቅፍ ስጦታ፣ ስለ አወራረስ ጉዳይ እንዲያዩ በአዋጅ ሥልጣን ተሰጣቸው እንጂ የገንዘብ መቀጫና የእሥራት ቅጣት እንዲወስኑ በአዋጅ በግልጽ ሥልጣን አልተሰጣቸውም። እንደ መደበኛ ፍ/ቤቶች የገንዘብ መቀጫና ነጻነትን የሚያሳጣ የእሥራት ቅጣት አይወስኑም›› የሚል ዐረፍተ ነገር ሠፍሮ ነበር። በመሆኑም የዚህ ውሳኔ ጭብጥ በተሰማባቸው የፒያሳው ኑር መስጊድና በታላቁ አንዋር መስጊድ ውስጥ መጠነኛ ግርግር እና ጉርምርምታዎች ተፈጠሩ።

የእስልምና ጉዳዮችን እንደ አዲስ ለማዋቀር እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረው የአምስቱ ማኅበራት ጥምረት በበኩሉ አዳዲስ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በማዋቀር የጀመረውን ሂደት ሲያጧጡፍ ሐጂ ሙሐመድ አወልም የራሳቸውን ጥረት በሌላ አቅጣጫ ያደርጉ ነበር። ሐጂ ሙሐመድ አወልን ከእነዚሁ ማኅበራት ተወካዮች ጋር የአዲስ አበባ የሥራ ኃላፊዎች ማደራደራቸውን ቢቀጥሉም ሁኔዎች ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሱና በሁለቱ ቡድኖች መካከል የሚደረገው የቃላት ጦርነትና ፍትጊያ እየተካረረ ቀጠለ። የመሥተዳድሩ ባለሥልጣናትም ለሁለቱም ቡድኖች ድጋፍ በመስጠት ሁኔታውን የከፋ እያደረጉት ስለመሆኑ በብዙዎች ታመነበት። ግራዝማች ሐዲስ በረቂቅ መጽሐፋቸው የመሥተዳድሩን ባለሥልጣናት አቶ ሐሰን ሺፋ እና አቶ ዐሊ ዐብዶ ለሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ ቡድን ይወግኑ እንደነበር ጽፈዋል። የወቅቱን ሁኔታ በአንክሮ ይከተታሉ እንደነበር የሚገልጹትና ከአል-አዝሐር ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ለ 30 ዓመታት ያህል በአወሊያ ት/ቤት ያስተማሩት ሐጂ ዐብደላህ ኢድሪስ ‹‹መንግሥት የሁለቱን አንጃዎች ግጭት ይፈልገው ስለነበር ሁለቱንም አንጃዎች ያግዝ ነበር›› ይላሉ። የቀድሞ የ‹‹ቢላል›› መጽሔት አዘጋጅ በበኩሉ ‹‹የመንግሥት አስፈጻሚ አካል ሥልታዊ ዝምታን መርጦ ከቆየ በኋላ የሥልታዊ ዝምታው ምንነት እና ዓላማ በየካቲት 14፣ 1987 ተገለጠ›› ይላል።

የካቲት 14 የዝሑር ሶላትን ለመስገድ አንዋር መስጊድ የገቡት የሐጂ ሙሐመድ አወል ቡድን አባል እና ወዳጅ ሐጂ ሰዓዱ ጀማል ከጥቂት ምእመናን ጋር በፈጠሩት እሰጥ አገባ እና ‹‹ራሳቸውንም ለመከላከል›› ወደ ሰማይ በተኮሱት ጥይት ምክንያት በአካባቢው ከፍተኛ ግርግር ተፈጠረ። ሁኔታውን ለማረጋጋት በአካባቢው የደረሱትን ፌዴራል ፖሊሶች (ፈጥኖ ደራሾች) ተኩስ በመቃወም ምእመኑ ወደ ፖሊሶች ድንጋይ መወርወር ጀመረ። ግጭቱም በፖሊሶችና በመስጊዱ እና አካባቢው በሚገኙ ሙስሊሞች መካከል ሆነ። ታዛዥቹ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች በዘመነ ደርግ እንኳ ተፈጽሞ የማያውቅ አስደንጋጭ ነገር ፈጸሙ። ድንጋይ በሚወረውሩባቸው ምእመናን ላይ እየተኮሱ ከነጫማቸው ታላቁ አንዋር መስጊድ ውስጥ ገቡ። የወቅቱ ኢማም ሐጂ ዙልመካን በማይክራፎን ‹‹ፖሊሶች! አላህን ፍሩ! አትተኩሱብን!›› ሲሉ ይሰሙ ነበር። የተከበረው የአንዋር መስጊድ የጦርነት አውድማ መሰለ። ሁከት እና ብጥብጡ ከግቢው ውጪም እየሰፋ ሄደ። በፖሊሶች ድርጊት የተቆጣው የአካባቢው ሕዝብ እና የጎዳና ተዳዳሪዎችም ጭምር ፖሊሶቹን እና መኪናዎቻቸውንም ጭምር ዒላማ አድርገው ጥቃት ሰነዘሩ። የፖሊስ መኪናዎችና ሞተር

ሳይክሎች ተቃጠሉ። በመጨረሻም ከሁሉም የከፋውን የአሥር ሰዎች ሕልፈት አስከተለ –አሥሩ ምእመናን ከፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ነበር ሕይወታቸውን ያጡት። ግርግሩ ከቀኑ 7 ሰዓት አንስቶ እስከ 10 ሰዓት ድረስ ቀጥሎ ነበር።

በዚያው ዕለት ምሽት የኢትዮጵያ ሬዲዮ በ 2:00 ሰዓቱ የዜና እወጃ ‹‹በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ ውስጥ በተፈጠረ የሥልጣን ሽኩቻ ሳቢያ በተቀሰቀሰ ሁከት ለጊዜው ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ሰዎች ሲሞቱ በርካታ ሰዎች መቁሰላቸውን ኢ.ዜ.አ. ዘገበ››የሚል አስገራሚ ዜና አስደመጠ። በዚያው ዕለት ምሽት ከዜና እወጃ በኋላ የወቅቱ የአዲስ አበባ መሥተዳድር ፕሬዚደንት የነበሩት አቶ ተፈራ ዋልዋ መግለጫ ሰጡ። መስጊዶችም ለሦስት ቀናት እንደሚዘጉ ተነገረ። ከግርግሩ ጀርባ ‹‹አሉ››የተባሉ የጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ አባላትና አመራሮች፣ እንዲሁም ሐጂ ሙሐመድ አወልና አጋሮቻቸው በሙሉ በዚያው ምሽት በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደረገ። ግራዝማች ሐዲስ በመጽሐፋቸው ሐጂ ሲራጅ ሙሳ የተባሉ የጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ አባል መገደላቸውን ጽፈዋል። ግለሰቡ ‹‹ሊያመልጡ ሲሞክሩ ፖሊስ ገደላቸው›› ቢባልም ማምለጥ የማይችሉና ያለመነጽር ማየት እንኳ የማይችሉ አረጋዊ እንደነበሩ ይታመናል። የግርግሩ ንዝረት ከየካቲት 14 የአንዋር መስጊድ ግርግር ሰዓታት በኋላ በተለይም ምሽቱን ታክኮ የተያዙት ሰዎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነበር። እነዚህ ከ45 በላይ ግለሰቦች በጠቅላይ ጉባዔው፣ በጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴው፣ በኢ.ሙ.ወ.ድ እና በሌሎች ሙስሊም ማኅበራት ውስጥ የታቀፉና ብዙዎቹም በመሪነት ቦታ ላይ የተቀመጡ ነበሩ። ‹‹የእነዚህ ግለሰቦች መታሰር በሙስሊሙ ኅብረተሰብ ሁለንተናዊ መስተጋብር ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽእኖ ሳይታለም የተፈታ ነበር›› ይላሉ የሙስሊሞች ጉዳይ የፊቸር ጸሐፊ ቡድን ያነጋገራቸው ምሁር። የቀድሞው የ‹‹ቢላል›› አዘጋጅ በበኩሉ ከየካቲት 14 ግርግር በኋላ መንግሥት ሲወስዳቸው የቆዩ ወሰን አልባ እርምጃዎች በግርግሩ ዕለት ምሽት የኢትዮጵያ ሬድዮ ባወራው ዜና የተቃኙ ነበር። እንደ ጋዜጠኛው በኅዳር 19 የተቃውሞ ሰልፍ ወደ 300ሺህ የሚጠጋን የአዲስ አበባ ሙስሊም ሕዝብ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ድረስ አግተልትለው የወሰዱትን የሰልፉን አደራጆች መያዝ የመንግሥት መነሻ ተግባር ነበር። የመንግሥት እርምጃ ስፋትና ትልቀት ግን ከዚህም በላይ ሆኖ ታይቷል። የአንዋር መስጊድ ግርግር በየካቲት 14 ተከስቶ በየካቲት 15 የእነቢላል ማኅበር የሙነዘማ ጽ/ቤት ታሸገ። የድርጅቱ አባላትም በወቅቱ ክስ የተመሠረተባቸው ‹‹በአገሪቱ እስልምናን በኃይል ለማስፋፋት በመጣርና ወጣቶችን የሽብር ተግባር እንዲፈጽሙ በማሠልጠን›› ቢባልም ታሳሪዎቹ የሙነዘማ አባላት ከሦስት ዓመት እስር በኋላ በጥቅምት 1990 በነጻ ተሰናብተዋል። በዚህ ቀን ታስረው ክስ ከተመሠረተባቸው ሠላሳ አምስት ግለሰቦች መካከል ሃያ ሰባቱ በነጻ ተለቅቀዋል። የሙነዘማ አባላት ከእስር በነጻ ቢለቀቁም ድርጅታቸው ግን ሥራውን እንዳይቀጥል ተደረገ። ሙነዘማ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ በታወጀው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተስፋ ጥለው በከፍተኛ ሞራል እና ትኩስ የሥራ ስሜት ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎችን የተቀላቀሉ ተቋማት እና ማኅበራት ‹‹ይብቃችሁ›› ተባሉ። ቢላል ‹‹ከዚያች ቀን በኋላ ሥማቸውን ያልሰማኋቸው በርካታ ድርጅቶች አሉ›› ይላል ሐዘን ባጠላበት መልኩ። ከእስር የተረፉት ግለሰቦች ጥቂቶች እግራቸው ወደመራቸው መሰደድን

መረጡ። ለሥራ ጉዳይ ከአገር ውጪ እንደነበሩት የሙነዘማ ሊቀመንበር ሸኽ ሰይድ አሕመድ ሙስጠፋ ያሉት ደግሞ እስራቱን በመሥጋት አለመመለስን መረጡ። አገር ቤት ያሉ ዑለማዎችና ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች ተሸማቀቁ። የዲን እንቅስቃሴዎችም ገጽታቸው እየደበዘዘ መታየት ጀመረ። እነ ሐጂ ሙሐመድ ወሌ የጀመሯቸው የቂራኣት ሐለቃዎች ተበተኑ። እነ ሙሐመድ አወል ረጃ የከፈቷቸው መድረሳዎችም ተዘጉ። ቢላል ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃ ይሠሯቸው የነበሩ በርካታ ሥራዎችን በማስታወስ ‹‹ሙሐመድ አወል ረጃ ከታሰረ በኋላ አንድም ቁርኣን ቤት አልተከፈተም›› በማለት በድፍረት ይናገራል። ሐጂ ሙሐመድ አወል ረጃም ወቅቱ የፈጠራቸውን ችግሮች በመዘርዘር በብዙ መልኩ ወደኋላ እንደመለሳቸው ይገልጹና ከ1987 በፊት 157 የቁርኣን መድረሳዎችና 40,000 (ዐርባ ሺህ) የቁርኣን ተማሪዎች እንደነበሯቸው በማስታወስ አሁን ግን በቁጥር 13 የሚሆኑ መድረሳዎች ብቻ እንዳሏቸው ሐዘን በተቀላቀለበት ስሜት ሐሳባቸውን ይሰነዝራሉ። ሁሉም በየፊናው ይሠራቸው የነበሩ ተግባሮች ተቆርጠው የወደቀ ዛፍ ሆኑ።

ከግርግሩ በኋላ የመንግሥት ዐይኖች አሁንም ድረስ በሙስሊም ድርጅቶች እና ግለሰቦች ላይ ተተክለው መቅረታቸውን የሚጠቁሙ በርካታ ድምጾች ይሰማሉ። የግርግሩ ውሽንፍር የነካቸው ሙስሊም ተቋማት እስከ መጨረሻው እንቅስቃሴያቸው ተገትቷል። የሙስሊሞች ጉዳይ ያነጋገረቻቸውን ምሁር ‹‹የየካቲት አሥራ ዐራቱ የ 1987 ግርግር እና መንግሥት እሱን ተከትሎ የወሰዳቸው እርምጃዎች 7 ዓመት ነዝሮናል››እንዲሉ ያስቻላቸውም ይህን ከግምት ማስገባታቸው ይመስላል።

ቢላል የቀድሞ ድርጅቱን ኢ.ሙ.ወ.ድ.ን (ሙነዘማን) አስመልክቶ እንደሚያስረዳው በየካቲት አሥራ ዐራቱ ግርግር ድርጅታቸው ምንም ዓይነት ሚና ያልነበረውና ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴው ጠቅላይ ጉባዔው እንዲፈርስ በወሰነበት የውሳኔ ወረቀት ላይ የኢ.ሙ.ወ.ድ የመስማሚያ ማኅተም እንዳላረፈ ያስታውስና ድርጅቱ እና አባላቱ ግን በተቃራኒው በሽብር ተግባር ተከስሰው ሥራቸውን እንዲያቆሙ መደረጉን ይጠቁማል። የሙነዘማ አባላት ግን ከምንም በላይ በስንት ልፋት ያቋቋሙት ድርጅታቸው ያለጥፋቱ መዘጋቱና ያለወንጀል ለዓመታት መታሰራቸው ዛሬም ከአሥራ አምስት ዓመታት በኋላ እንደከነከናቸው ነው። በሐሳባቸው የዳዕዋ መድረካቸውን ያስነጠቃቸውን የየካቲት 14፣ 1987 ግርግር መጥፎ አጋጣሚ ይረግማሉ። ታዛቢዎች ይህን ከግምት በመክተት መንግሥት ከግርግሩ ዕለት ጀምሮ የወሰዳቸው እርምጃዎች ቀድሞ የታሰበባቸው እንደሆኑ ይናገራሉ። ‹‹የሁለቱ አንጃዎች ጥፋት ለመንግሥት በር ከፍቷል›› የሚለው ደግሞ የቀድሞው የሙነዘማ አባል ወጣት ነው። እንደዚህ አስተያየት ሰጪ አባባል በሁለቱም አንጃዎች በኩል የተሰለፉ ግለሰቦች በወቅቱ ግባቸውን ማሳካት ባይችሉም የመንግሥትን የልብ መሻት ግን መሙላት ችለዋል።

መስታወቱ ላይ የቆመ ኡምማ

የሙስሊሞች ጉዳይ የፊቸር ጸሐፊ ቡድን ያነጋገራቸው ምሁራን በኅዳር 1987 የመንግሥት የልብ

መሻት እውን ከሆነባቸው አንኳር ጉዳዮች አንዱ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ ጠለፋ እንደሆነ ያምናሉ። የየካቲት አሥራ ዐራቱን ግርግር ተከትሎ መንግሥት የወሰዳቸው እርምጃዎች ከአንዱ ወገን ብቻ ሳይሆን በጠቅላይ ጉባዔውም (በመጅሊሱ) በኩል የነበሩ አካላትን ያስደነገጡ እንደነበር ይታመናል። ይህም መጅሊሱን ሰው አልባ ተቋም አድርጎት ታይቷል። በወቅቱ ተቋሙ መሪ ማጣቱ ‹‹ያሳሰበው››መንግሥት ግለሰቦችን በመጋበዝ ተቋሙን ዳግም እንዳቋቋመ የሚገልጹት ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ዘህረዲን በአዲሱ አደረጃጀት ዑለማዎች እንዳይካተቱ መደረጉ በብዙ መልኩ የዑለማዎችን ሞራል እና ክብር እንደነካ ያስረዳሉ። የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት በቁጥር አሥር እትሟ ከ 1987 በኋላ የመጅሊሱ ሕልውና ከዑለሞች ብቻ ሳይሆን ከሙስሊሞችም እጅ ተፈልቅቆ ለፖለቲካ ሥራ ማስፈጸሚያነት መዋል እንደጀመረ ገልጻ ነበር። ምሁራኑ ለዚህ ሐሳባቸው ማጠናቀሪያነት ከተጠቀሰው ወቅት ጀምሮ በ 1992 ከተደረገው የይስሙላ ምርጫ ውጪ ምንም ዓይነት ምርጫ አለመደረጉንና ሕዝቡ የሚያምንባቸው መሪዎች አለመቀመጣቸውን በምክንያትነት ይጠቅሳሉ።

ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ‹‹ተቋሙ ከ 1987 ወዲህ መንግሥትን መምሰል የጀመረው ከሥያሜው ነው››በማለት ‹‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባዔ› የሚለውን ‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት›ወደሚል በመለወጥ›› የሥያሜ ሽግግሩ ከሥርዓቱ ሽንነዎች ጋር ያለውን ምስስሎሽ እንደጀመረ ያሳያሉ። ሕዝበ ሙስሊሙን የማገልገል ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦችም ወደ ተቋሙ እንዳይቀርቡ በጠቅላይ ም/ ቤቱ እና በክልል እስልምና ጉዳይ ቢሮዎች ‹‹ወሐቢያ ብለው የሠየሙት ቡድን አባላት እንዳይካተቱ›› መደረጋቸውን ሸኽ ሙሐመድ ዘይን ያስረዳሉ። ሌላው አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው ‹‹እኛ አገር አንገቱን ቀና ያደረገ ሁሉ ‹ወሐቢያ›የሚል ሥያሜ ተሰጥቶት ወደ መጅሊስ ድርሽ እንዳይል ተደርጓል›› ይላሉ። ምሁራን ከዚህ በኋላ በተቋሙ ተሹመው የሚመጡ ግለሰቦች መንፈሳዊም ሆነ አካዳሚያዊ እውቀት የሌላቸው የፖለቲካ ቅጥረኞች መሆን መጀመራቸውን በልበ ሙሉነት ይናገራሉ።

ሸኽ ዐብደላህ እድሪስ ከ 1987 በኋላ ነጻ የዑለማዎች ማኅበር ለማቋቋም ከዕድሜ እና እውቀት አጋሮቻቸው ጋር ያደረጉት ጥረት እንኳ እንዳልተሳካ በመጥቀስ በ 2000 ዓ.ል የዑለማዎች የምክክር መድረክ የፈረሰበትን አሳዛኝ አጋጣሚ ያስታውሳሉ። በ 1987 ግጭት የሸሪዓ ፍ/ቤት አቅም እና ሥልጣን ዋነኛ አጀንዳ እንደነበር የሚያስታውሱት ደግሞ ሸኽ ምቾት አሕመድ ናቸው። ሸኽ ምቾት ‹‹የሸሪዓ ፍ/ቤት ሥልጣንና ኃላፊነት ለመጅሊሱ መሰጠት የለበትም›› የሚለው ሙግት ሙሉ በሙሉ እንዳከተመለት በመግለጽ ዛሬ መጅሊሱ የሸሪዓ ፍ/ቤት ውስጥ ያለውን ሚና፣ በተለይም በአዋጁ የተሰጠውን ዳኞችን የመጠቆም ሥልጣን ያወሳሉ። የቀድሞ የሸሪዓ ፍ/ቤት ቃዲ የነበሩ ሌላ ግለሰብ ግን መጅሊሱ የሸሪዓ ፍ/ቤት ውስጥ ያለው ሥልጣን ዳኞችን በመጠቆም ብቻ ያልተገደበ እንደሆነና የፍ/ ቤቱን ውሳኔዎች የማጽደቅም ጭምር የጓሮ ሥልጣን እንደተሰጠው ይናገራሉ። ሌሎችም ወገኖች የዚህን ሐሳብ እውነትነት ያጸድቃሉ። ታዛቢዎች ግን

ነገሩ የተገላቢጦሽ የሚሆንባቸው፤ በየጊዜው በሚታደስ የኤን.ጂ.ኦ ሰርቲፊኬት የሚንቀሳቀሰው መጅሊስ በአዋጅ በተቋቋመው የሸሪዓ ፍ/ቤት ውስጥ የውሳኔ ሰጪነት ሚና ማግኘቱ ነው።

1987 የፈጠረው ቀውስ እና ጠባሳ ገና የሻረ አይመስልም። ቁስሉን የሚያመረቅዙ ክስተቶች ግን በየአቅጣጫው ብቅ ብቅ እያሉ ነው። ለዚህም ነው የሙስሊሞች ጉዳይ ያነጋገረቻቸው ምሁራን ‹‹የ 1987 ዓይነት ግርግር ዛሬም ላለመከሰቱ ዋስትና የለንም›› የሚሉት። ‹‹በሰኔ 2003 የተጀመረው ‹‹አሕባሽ››ን የማስፋፋት ፕሮጀክት ፍጻሜው የ1987ን ክስተት ዳግም ለመመለስ የታለመ ነው›› የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ምሁሩ ‹‹በደፈናው ያንን ማለት ባይቻልም ምልክቶችን እያየን ነው›› ይላሉ። ሌሎች በበኩላቸው ከ2003 መባቻ ጀምሮ የነበሩ ወቅቶች ከድኅረ 1987 ጋር በጉልህ መልኩ እንደሚመሳሰሉ ምሳሌ በመጥቀስ ያስረዳሉ። መጅሊስ ለ 1987 ግርግር መነሻ የሆነው ‹‹ከእኔ ውጪ ሌላ ኢስላማዊ ድርጅት መኖር የለበትም›› የሚለው አቋሙ ምንም መሻሻል ሳይታይበት ዛሬ ላይ ተደርሷል። በ1987 ሙነዘማ በአሸባሪነት ተፈርጆ እንዲዘጋና አባላቱ ወህኒ እንዲወርዱ እንደተደረገው አሁንም በተመሳሳይ መልኩ የመጅሊስን መሪነት የማይቀበሉ ድርጅቶች እና ወገኖች በአሸባሪነትና በጸረ-ሰላም ኃይልነት መፈረጅ ጀምረዋል።

መጅሊሱ እንዲፈርሱ የሚሻቸው ድርጅቶች የሕጋዊ-ሰውነት ደረጃ ከመጅሊሱ ጋር ተቀራራቢ ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ ቢሆንም በመጅሊሱ ‹‹ቀጭን ትዕዛዝ›› ከመፍረስ አልዳኑም። የድኅረ 1987 እርምጃዎች ዐቢይ መገለጫ የነበረው የኢስላማዊ ተቋማት ፈቃድ ሥረዛ መሆኑን እነዚሁ ወገኖች በማስታወስ የድርጅቶች የሥራ ፈቃድ ነጠቃ ጥቂት በማይባሉ ኢስላማዊ ድርጅቶች ላይ መጀመሩን ይገልጻሉ። ሥራ እንዲጀምር ፈቃድ ተሰጥቶት በወራት ውስጥ ፈቃዱን እንዲመልስ የተደረገው ‹‹የሙስሊሞች ሊግ›› አንድ ምሳሌ ተደርጎ የሚቀርብ ሲሆን በተለያዩ ክልሎችም ተመሳሳይ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ ናቸው። ለእነዚሁ ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ ነጠቃ እየቀረበ ያለው ምክንያት ከድኅረ 1987 በመሠረቱ የማይለይ ቢሆንም የመጅሊሱ ሚና ግን ከፍተኛ መሆኑን ታዛቢዎች ሳይገልጹ አያልፉም። እርምጃዎቹ ኢስላማዊ የፋይናንስ ተቋማትን፣ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን፣ እንዲሁም በጥናትና ምርምር ሥራ ላይ የተሠማሩ ማዕከላትን እንኳ የሚምሩ አይመስሉም። እነዚህ ተቋማት ለሚመለከታቸው አካላት ‹‹አቤት›› ቢሉም ሰሚ አላገኙም –ልክ እንደ 1987!

የአንቀሳቃሽ ግለሰቦች እስራት፣ የዳዒዎች ግዞት እና ስደት፣ ይህን ተከትሎም በፍርሃት መሸበብ እና የኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች ወደ ኋላ መገታት ቀጣዮቹ ፈተናዎች እንደሆኑ መተንበይ እንደሚቻል ምሁራኑ ያስገነዝባሉ። ጉዟችን ወደ 2005 ሳይሆን ወደ 1987 መሆኑን የሚጠቁሙ ቅስቶች በየአደባባዩ ተተክለዋል። ግን ሕዝብ ስንት ዓመት ወደ ኋላ ይጓዛል?

---

1. ከሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄት የተወሰደ (*የካቲት 2004)*

የሰማዩን እንኳ ተዉልን!

አክመል ነጋሽ[1]

መጋቢት 2004

ይኸው ዘጠኝ ወራት ተቆጠሩ-መንግሥታዊ ድጋፍ እየተሰጠው ያለው (state sponsored) የ‹‹አሕባሽ›› አንጃ ነውጡን ከጀመረ! ባለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ የተዘጉ መስጊዶችን፣ የተከረቸሙ መድረሳዎችን፣ ከሥራ የተሰናበቱ የስግደት መሪዎቻችንን ብዛት ማን ቆጥሮ ይዘልቀዋል? በሐምሌ 2003 ሐረር በሚገኘው የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሕዝባዊ እውቅናን ከተነፈገው መጅሊስ ጋር በመተባበር አዘጋጅቶት ከነበረው የ‹‹አሕባሽ›› የማጥመቂያ ‹‹ሥልጠና›› በኋላ ብዙ ነገሮች ተለዋውጠዋል። በ‹‹ሥልጠና››ው ወቅትና ከዚያም ቀደም ብሎ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ከመጅሊስ አመራር አባላት ጋር የተማማሉበትን ‹‹አሕባሽ››ን በኢትዮጵያ የማንገሥ ቅዠት እውን ለማድረግ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ያልተፈነቀሉ ድንጋዮች አልነበሩም። እኛ በሚፈነቀሉት ድንጋዮች ላይ ረዣዥም የመንግሥት እጆች ይታዩን ነበር።

መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን የሚደነግገው የሕገ-መንግሥቱ አሥራ አንደኛ አንቀጽ አንዳንዴ የወረቀት ነብር ይመስለኛል። ምንም እንኳን አንቀጹ እና በውስጡ ያሉት ንዑሳን አንቀጾች በማያሻማ መልኩ የመንግሥትንና የሃይማኖትን መፋታት ቢያውጁም በተግባር ግን ፉርሽ ናቸው።

የኢትዮጵያ ሙስሊም ኅብረተሰብ በስፋት እንደሚያምነው የመጅሊሱን የአመራር ቦታዎች (በተለይም ከ 1987 ወዲህ) ከመደልደል ጀምሮ አሁን ትልቅ ውዝግብ እየፈጠረ እስካለው የ‹‹አሕባሽ›› አጀንዳ ድረስ መንግሥት ዋነኛው ተዋናይ ሆኖ ታይቷል። በመጅሊሱ የአመራር ወንበሮች ላይ ከተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ያለምርጫ ግለሰቦችን የሚያስቀምጠው መንግሥት መሆኑን ሕዝቡ የተመለከተባቸው የተለያዩ አጋጣሚዎች ተከስተዋል። ‹‹ሰፊውን የኢትዮጵያ ሙስሊም ኅብረተሰብ ይመራል›› በሚባለው መጅሊስ ውስጥ የውሳኔ ሰጪነትን ሚና የሚወጡ ሥውር እጆች የመንግሥትን ቀጥተኛ ትእዛዝ ለማስፈጸም የተዘረጉ ናቸው። ለዚህም ነው ተቋሙ ለተቋቋመለት ዓላማ የሚሆን አንድም ቁም ነገር ሳይሠራ ሁለት አሥርት ዓመታትን የዘለቀው። መጅሊሱ ‹‹እመራዋለሁ›› በሚለው የሕዝብ ብዛት ተመርኩዞ ሊያከናውናቸው ይገቡ የነበሩ አያሌ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ሕልም ብቻ ሆነው ቀርተዋል። አንድ ኢስላማዊ የሃይማኖት ተቋም መስጊድ ካልገነባ፣ የሃይማኖት ትምህርት ቤት ካላነፀ፣ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ካላሳተመ ምን ቁም ነገር ‹‹ሠራ›› ብለን እናወራለታለን? የኛ መጅሊስ ከነዚህ ሁሉ የለበትም፤ ምክንያቱም ለሿሚዎቹ ለማደግደግ እንጂ ሕዝበ ሙስሊሙን ለማገልገል ጊዜውም ሞራሉም የለውምና! ይህ ሁሉ የጣልቃ ገብነት ጣጣ ነው።

በሽፍንፍን ለዓመታት ቆይቶ የነበረው የመንግሥት-መጅሊስ ጋብቻ (በሌላ አነጋገር የመንግሥት ጣልቃ ገብነት) አሁን ይፋ ወጥቷል። በተለይም ከ2003 ወዲህ ‹‹አክራሪነትን ለመዋጋት›› በሚል ሰበብ (pretext) ሁለቱ ወገኖች የምድሩን የወሰኑልን ሳይበቃቸው የሰማዩንም መንገድ

ሊመትሩልን ወደ አደባባይ ብቅ ብለዋል። ‹‹አከራሪነትን ለመዋጋት›› ፌዴራል ጉዳዮችና መጅሊስ ‹‹አሕባሽ›› በሚባል ስል መጥረቢያ ‹‹ወሐቢያ›› ብለው የሠየሙትን ባሕር ዛፍ ለመገንደስ ጥረት ማድረግ የጀመሩት ከዚህ ወቅት ጀምሮ ነው። ሙስሊሙ ኅብረተሰብ የወደቀ ዛፍ ባይመለከትም ዛፉን ለመገንደስ ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸው ትላልቅ ‹‹ሥልጠና››ዎች በሁለቱ ወገኖች አማካኝነት ተዘጋጅተው በርካቶች በግዳጅ እንዲሠለጥኑ ተደርገዋል።

በ‹‹ሥልጠና››ዎቹ ላይ የተገኙ የመንግሥት ባለሥልጣናት ያለምንም መሳቀቅ በሃይማኖት ጉዳይ ገብተው ሲፈተፍቱ ታይተዋል። ይህ ሃይማኖታዊ ‹‹ሥልጠና›› ወይም አንዱን ሙስሊም በሌላው ሙስሊም ላይ የሚያነሣሣ ዘመቻ ያዘጋጀው መንግሥት መሆኑንም ነግረውን አድምጠናል። ይህም ብቻ ሳይሆን ‹‹ሥልጠና››ው ገና በስፋት እንደሚቀጥል ቃል ገብተዋል። ለተገኙት ሠልጣኖች ንግግር ያደረጉ አንዳንድ ባለሥልጣናት ከዚህም ብሶ ማን ትክክለኛ ሙስሊም፣ ማንስ ደግሞ ሓሳዊ ሙስሊም እንደሆነ ‹‹መጽሐፉን ገልጠው›› ነግረውናል። ከሃይማኖት ልሂቃን እና ከሃይማኖት አንጃዎች የትኛው ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ የተሸለ እንደሆነ ‹‹ኪታብ ገልጠው›› መስከረዋል። ከዚህም በከፋ መልኩ ሌሎቹ ቅንጅትና ኢሕአዴግ አብረው መደራደር የማይችሉትን ያህል ይኸኛው ሙስሊም ከዚያኛው ሙስሊም ጋር በፍጹም አብረው ሊሆኑ እንደማይችሉ ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ›› የተባለ ‹‹ድርሳን እየገለጡ›› አስረድተውናል። ባለሥልጣናቱ ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ የፖለቲካ ማሊያቸውን ለብሰውና ሚዲያም ጭምር ጋብዘው ነው። እንዲህ ሁሉ ሆኖ አባላቱም ጭምር በጣልቃ ገብነት ወቅሰውት መንግሥት እኔ ጣልቃ አልገባሁም እያለ ነው። ከዚህ የተሻለ ከቶ ምን ዓይነት ጣልቃ ገብነት ይኖር ይሆን?

ባለሥልጣናቱ ከዐራት ኪሎ መስጊድ ድረስ ያመጣቸው አዲስ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ባይኖርም አዲስ የፖለቲካ ስትራቴጂ መኖሩን ግን ማሸተት ይቻላል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተዋስኦ (Discourse) ውስጥ ሃይማኖት ሁሌም ሁነኛ ቦታ አለው። የዐራት ኪሎ ሰዎች ግን እስካሁን በደንብ እንዳልተጠቀሙበት የገባቸው አሁን ሳይሆን አይቀርም። አሁን ተረኛው ተመዛኙ ካርድ ሃይማኖት ሆኗል። አሁን ግን ይህ የተመዘዘ ካርድ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሳያመዝን አልቀረም። እኔ እስከሚገባኝ አንድ ሰብዓዊ ፍጡር ከብሩንና ሌሎች ምድራዊ እሴቶቹን ለሌላ ምድራዊ ጥቅም ብሎ አሳልፎ ይሰጥ ይሆናል። ለምድራዊ ዓላማ ብሎ ግን እምነቱን ቤዛ የሚያደርግ እምብዛም ይኖራል ብዬ አላምንም። ለዚህም ነው መንግሥት የጀመረው ስትራቴጂ ‹‹ብዙም አያዋጣም›› ብዬ የምሞግተው። ያም ሆኖ ግን መንግሥት አሁንም እምነት በጣለባቸው ልማታዊ ‹‹ሼኾች›› አማካኝነት አብዮታዊ ዴሞክራሲን እየሰበከ ነው።

የሥርዓቱ ወይስ የአምላክ ሎሌዎች?

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ‹‹ይመራናል›› ብለው ያቋቋሙት ተቋም (መጅሊስ) ባለፉት አሥራ ሰባት ዓመታት ከሼኽነት ይልቅ የካድሬነት መለዮ ለብሰው በሚጫወቱ መሪዎች ሲተዳደር ቆይቷል። እነዚህ አመራሮች በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ ሁሌም ‹‹እንመራዋለን›› ለሚሉት አማኝ አንዲት ቁም ነገር ከመሥራት ይልቅ ሥልጣናቸውን ለርካሽ ፖለቲካዊ ተግባር ሲያውሉት ዐይተናል። አመራሮቹ ከሚመሩት ሕዝብ ይልቅ ወንበሩ ላይ ላሳቀመጧቸው ረዣዥም የመንግሥት እጆች ሲያጎበድዱ፣ የነዚህኑ እጆች አቅጣጫ እየተከተሉ ጎንበስ ቀና ሲሉ ታዝበናል።

ወደሥልጣን ያመጣቸው እጅ ከሥልጣናቸው ለማውረድም ብዙ እንደማይቸገር ስለሚረዱ የሱን የልብ መሻት ለመሙላት ለሶላት ለተገኘው ሕዝብ መለኮታዊ ቃል ነግሮ መንፈሳዊ ኃላፊነትን ከመወጣት ይልቅ የ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲን›› እና የመንግሥተ-ዐራት ኪሎ ‹‹ቅዱሳን መጽሐፍት››ን እየገለጡ ያነበንባሉ። ዘወትር ከስግደት በኋላም ‹‹የመንግሥተ-ዐራት ኪሎ መንግሥት ትመንደግ!›› እያሉ ጌታን ይለማመናሉ። ምርጫ ሲቃረብ ደግሞ እነዚሁ ጠምጣሚ ካድሬዎች ሥልጣን ላይ ያስቀመጣቸውንና ያከረማቸውን ረዥም እጅ እያመሰገኑ ‹‹ምእመን ሆይ! ይህን ባለ ረዥም እጅ መምረጥ መንግሥተ ሰማያትን ያስወርሳል!›› ሲሉ ይሰብካሉ። ሥርዓቱ የፈጠራቸው የሼኺ ሎሌዎች እነዚህ ናቸው።

ኢማም አል ገዛሊ የተባሉ የመካከለኛ ዘመን ልሂቅ ‹‹ሃይማኖታዊ እውቀት ምድራዊ ክብር ማግኛና የሥልጣን ማደላደያ መሣሪያ በሚሆንበት ዘመን ይህንኑ ክብር ሽተው ሃይማኖታዊ እውቀት የሚማሩ ሰዎች ቁጥር ያሻቅባል›› ብለው ጽፈው ነበር። አሁን በዚህ ዘመን ያለው እውነታም ይኸው ይመስለኛል። ልማታዊ ሼኺዎች ቅዱስ የሆነውን የአምላክ መንገድ ርካሽ ፖለቲካዊ ቁማር ማሳኪያ ሊያደርጉት ላይና ታች ሲንከላወሱ ማየት የተለመደ ነው። የሃይማኖት አባት ሲባል ፍትሕ እንዲሰፍን፣ አብሮነት እንዲጸና፣ ቀናው የአምላክ መንገድ እንዳይዛነፍ ሌት ተቀን የሚጥር መሆን ነበረበት። አንድ የነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ንግግር ‹‹ከትግሎች ሁሉ ምርጡ በአምባገነን መሪ ፊት እውነትን መናገር ነው!›› ይላል። የኛ የሃይማኖት አባቶች ግን ፍትሕ ሲጓደል፣ ሙብት ሲጣስ፣ ሃይማኖት ሽቀጥ ሲሆን ከመንቀፍ ይልቅ የሥርዓቱ ሎሌዎች ሁነው የአምላክን መንገድ ይሸራሉ። ‹‹አፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል›› እንዲል ብሒሉ የዘንድሮ ‹‹ሼኾች›› ዐራት ኪሎ ጉንፋን ሲይዘው መስጊድ ውስጥ ሆነው ያስነጥሳሉ።

ልማታዊ ሼኾች... እስቲ እንጠይቃችሁ... መጽሐፉ የሚለው ይህንኑ ነው? መጽሐፉ የሚያስተምረው ስለእውነት ማደርን እንጂ ለምድራዊ ጥቅም ብሎ ሃይማኖት መሸጥን አይደለም። የአምላክን ቃል ከፍቶ ማስተማርን እንጂ ጋዜጠኛ ሰብስቦ፣ ካሜራ አስደግኖ የፈርዖንን የቅጥፈት እንቶ ፈንቶ ማነብነብ አይደለም ጀነትን የሚያስወርሰው። አልያም ከመጠምጠም ማወቅ ይቅደም! እነዚህ የምድሩን ጨርሰው የሰማዩንም ፈረስ ሊፈናጠጡ የከጀሉ ጠምጣሚዎችና የዐራት ኪሎና የመጅሊስ መቀያየጥ ጉዳይ ሰላም የነሣቸው በአዲስ አበባና በክልል የሚኖሩ ሙስሊሞች ‹‹ኧረ የፍትሕ ያለህ!›› እያሉ መጮህ ከጀመሩ ይኸው ሦስት ወራት ተቆጥረዋል። መንግሥትም ‹‹ከደሙ ንጹህ ነኝ!›› እያለ በተገኙት ሚዲያዎች ሁሉ ሐሳቡን እያስተጋባ ነው።

ሕዝቡ ብሶቱን እንዲያሰሙለት የመረጣቸው አሥራ ሰባት ተወካዮች ባለፈው የካቲት 26 ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መልስ የሚመስል ‹‹መልስ›› ተሰጥቷቸዋል። ሕዝበ ሙስሊሙ ጠምጣሚዎቹ ካድሬዎች ከሥልጣን እንዲነሱለትና ሕዝባዊ ምርጫ እንዲካሄድ ላቀረበው ጥያቄ ያገኘው ምላሽ ብዙም አዎንታዊ አይደለም። የፌዴራል ጉዳዮች መልስ በደምሳሳው ‹‹ለመጅሊሱ የአመራር ቦታዎች ምርጫ ይደረጋል›› ከማለት በዘለለ ‹‹መቼ?›› እና ‹‹እንዴት?›› ለሚሉት ጥቄዎች የሰጠው ምላሽ የለም። አላዋቂ ጠምጣሚዎቹ የመጅሊስ አመራሮች በበኩላቸው ‹‹ምርጫውን ብር ካገኘን እናካሂዳለን፤ የምርጫ መመሪያውን እያዘጋጀን ነው›› በማለት ሙስሊሙ ሳይመርጣቸው ወንበሩ ላይ መቀመጡ ሳያንሳቸው ምርጫውንም በቆሸሸ እጃቸው

እንዳይሆን ሊያደርጉት ተዘጋጅተዋል። ይህ ሁኔታ ክፉኛ ያበሳጫቸው ከ500 ሺህ በላይ የከተማዋና የክልል ሙስሊሞች ባለፈው ሳምንት አሥረኛውን የተቃውሞ ጁሙዓ በአወሊያ አካሂደዋል።

በሕዝብ የተነሱት ሌሎቹ ጥያቄዎችም እንዲሁ ከመንግሥት በኩል አዎንታዊ ምላሽ አላገኙም። ከገጠር እስከ ከተማ በግዳጅ ሲሰጥ የነበረው የ‹‹አሕባሽ›› ‹‹ሥልጠና››ም እንዲሁ ምንም ዓይነት ግዳጅ እንዳልነበረበት እነዚሁ ከኮሚቴዎቹ ጋር የተገናኙ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሞግተዋል። ይህን የመንግሥት ምላሽ ባለፈው ሳምንት አወሊያ ተገኝቶ ያደመጠው ሕዝበ ሙስሊም ንዴቱን በሚገባው መልኩ ገልጿል። ጥያቄዎቹ በአግባቡ እስኪመለሱ ድረስም ሰላማዊ ተቃውሞውን እስከመጨረሻው እንደሚቀጥል ቃል ገብቷል። አሥራ ሰባቱ ተመራጮች ጥያቄያቸውን ለሌሎች የመንግሥት ፍትሕ ቢሮዎች እስከ ጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ድረስ ለማቅረብ እንቅስቃሴ ቢጀምሩም ከባለፈው ሳምንት መባቻ ጀምሮ የመንግሥት ደህንነቶች መላወሻ አሳጥተዋቸዋል። ከሰባት በላይ የደህንነት መኪኖች የኮሚቴዎቹን አባላት ከጠዋት እስከማታ በመከታተል እና በማዋከብ ላይ ናቸው። የሕዝብን ሰላማዊ ጥያቄ በሰላማዊ መልኩ ለመንግሥት እያቀረበ ያለን ቡድን ይህን ያህል ማዋከብ ትርፉ ምን እንደሆነ አልገባኝም።

ሙስሊሙ ኅብረተሰብ የጠየቃቸው ጥያቄዎች ሕገ-መንግሥታዊ በመሆናቸው መንግሥት ‹‹ጣልቃ አልገባሁም›› እያለ መደባበቁን ትቶ ትክክለኛውን ምላሽ ለሕዝብ ሊሰጥ ይገባል። የምድሩን ትተንላችሁ ሁሉም በእጃችሁ ሆነ፤ የሃይማኖት ነጻነት ጥያቄያችንን እንኳ መልሱና የሰማዩን መንገድ ተዉልን!

---

1. ***አክመል ነጋሽ*** የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄት ሲኒየር ኤዲተር ነው፡፡

የመለስ ዲስኩር ግዝፈትና ግድፈት

አክመል ነጋሽ

ሚያዚያ12/2004

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በየጊዜው እየቀረቡ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸውን ማብራሪያዎች ሳደምጥ ቆይቻለሁ። ከቀናት በፊት ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የመብት ንቅናቄ አስመልክቶ የእሳቸው ግላዊ አቋም ምን ሊሆን ይችላል?›› ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ከእሳቸው አንደበት ምላሽ ማግኘት ችለናል። በዚሁ የማክሰኞ የፓርላማ ውሎ እና ዲስኩር ብዙዎቻችን የቀድሞን ብቃታቸው (performance) እያሽቆለቆለ መሄዱን ታዝበናል። በተለይ በሃይማኖት ጉዳይ የሰጡት ‹‹ትንታኔ›› እውነታዎችን ለጥጦ በማግዘፍና በማግደፍ የተሞላ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በዚህ ጽሑፌ የእሳቸውን ሕጸጾች ከግላዊ ምልከታዬ በመነሣትም ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

በቀዳሚነት ለጠቅላይ ሚኒስተሩ ጥያቄውን ያቀረቡት ‹‹የአጋር ፓርቲ አባል›› ጥያቄያቸውን ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ የተመራ (leading question) ማድረጋቸው መለስ ምላሹን አድበስብሰው እንዲያልፉት አጋዥ ሆኗቸዋል። ጠያቂው ‹‹የአክራሪነት አዝማሚያዎች... መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል በሚል ሰበብ... በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት...›› የሚሉ ሐረጎችን በማከል ጥያቄውን እጅግ አቅልለውላቸዋል። ምናልባትም ጥያቄው ከተፎካካሪ ፓርቲ አባል ተጠይቆ ቢሆን ኖሮ አብነቶችን በመጥቀስ ጥያቄው ከተግዳሮት ጋር ሊቀርብ ይችል የነበረ በመሆኑ የምላሻቸውም ይዘት ሊቀየር ይችል ነበር። ሆኖም ያ ባለመሆኑ የጥያቄውን ዐውድ እንዳሻቸው እንዲቀያይሩት ምክንያት ሆኗል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የመብት ንቅናቄ አስመልክቶ ምላሽ ሲሰጡ የተንደረደሩት ከሕገ-መንግሥቱ አንቀጾች ነው፤ በተለይም ስለ መንግሥትና ሃይማኖት መለያየት የሚደነግጉትን አናቅጽ። በተደጋጋሚ ጊዜ እንዳስተዋልነውም ‹‹መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል›› ለሚለው ውንጀላ የገቢው ፓርቲ ሰዎችም ሆኑ ልሳኖቻቸው የሚጠቅሱት የሕገ-መንግሥቱን የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት ድንጋጌ ነው። ‹‹መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ በመሆናቸው ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ አንገባም›› የሚል ነው የብዙዎቹ መልስ። የእሳቸውም መልስ ይኸው ነበር።

በመሠረቱ የአንድ ሕግ መደንገግ በራሱ ወንጀልን ከነአካቴው ሊያስቆም አይችልም። አሁን ባለው ሁናቴ መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱን የሚጠቁሙ የቪዲዮ፣ የድምጽ እና የሠነድ ማስረጃዎች በገፍ እየቀረቡ ሳለ እሳቸው እና መንግሥታቸው የቀረቡትን ማስረጃዎች የሚቀለብስ ሌላ ማስረጃ ከማቅረብ ይልቅ ‹‹ሕገ-መንግሥቱ ስለከለከለን አናደርገውም›› የሚል ሾላ በድፍን መልስ መስጠታቸው አግባብ አይደለም። ምክንያቱም የሕግ መኖር ወንጀል ላለመፈጸሙ ዋስትና

አይሆንም። በአገሪቱ ሙስናን፣ ሥርቆትን፣ ጾታዊ ጥቃትን ወዘተ... የሚከለክሉ የፍትሕ ብሔርና የወንጀል ሕግጋት አሉ።

የእነዚህ ሕግጋት መኖር ግን ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎች ሊገታቸው አልቻለም። እንደውም በተቃራኒው የወንጀሎቹ ቁጥር አሻቅቦ ነው የታየው። የአቶ መለስም አሥተዳደር ዳር ዳር ከማለት ይልቅ ወዳጂ ተመስገን ከሳምንታት በፊት ያቀረባቸውን የመንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ማስረጃዎች ቢመልሱ ይሻላቸው ነበር። ነገሩ ከየት አምጥተው ይመልሱታል? የመለስ ‹‹ነባሩ›› እስልምና ከሰሞኑ የገዢው ፓርቲ ሰዎች ‹‹ነባሩ እስልምና›› የሚል ቃል አለቅጥ አብዝተዋል። ከቀናት በፊት ያገኘሁትና ፓርቲው አባላቱን ሊያወያይበት ያዘጋጀው ባለ 25 ገጽ ሠነድ ‹‹ነባሩ እስልምና›› የሚል ቃል ደጋግሞ ሲጠቅስ አስተውያለሁ። ቃሏ ልክ እንደ ‹‹ውሃ ማቆር››፣ ‹‹ውጤት ተኮር››፣ ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ›› ዓይነት ቃላት አዲስና ልማታዊ ሳትሆን አይቀርም።

የሆነ ሆኖ መለስም በመልሳቸው ‹‹ነባሩ እስልምና›› የሚል ሐረግ ደጋግመው ጠቅሰዋል። መለስ ሲያስረዱ ‹‹በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የነበረው ነባሩ እስልምና ሱፊይ የሚባለው ነው›› ብለውናል። ይህ የአቶ መለስ አካሄድ አሁን መንግሥታቸው እያካሄደ ያለውን በ‹‹አሕባሽ›› አስተምህሮ የማጥመቅ ስትራቴጂ ትክክለኝነት ለማሳየትም ያለመ ይመስላል። አቶ መለስ ‹‹የሃይማኖቱ አዋቂዎች እንደነገሩን›› የሚለውን ቃል በመደጋገም ‹‹አሕባሽ›› የነባሩ ሱፊይ አስተሳሰብ አካል እንደሆነ አስረድተዋል።

‹‹ለመለስ ያስረዷቸው የትኞቹ የሃይማኖት አዋቂዎች ናቸው?›› ከተባለ አሁን ሕዝበ ሙስሊሙ ‹‹ሳንመርጣቸው በመንፈሳዊ ተቋማችን ተቀመጡብን፤ ስለማንፈልጋቸውም ይነሡልን›› ያላቸው ጠምጣሚ ካድሬዎች ናቸው። ‹‹የ‹አሕባሽ›ን ሥልጠናም ሆነ ትምህርት እየሰጠ ያለው የሙስሊሞች መንፈሳዊ መሪ ድርጅት በመሆኑ ምንም አይመለከተንም›› የሚል ስሜት ነበረው መልሳቸው። ሕዝቡ ‹‹መሪ ድርጅቴ ውስጥ የተሰገሰጉት ግለሰቦች ያልተመረጡ ናቸው፤ ምርጫ ይካሄድልን›› ብሎ፣ አቤቱታ አቅርቦ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርም ምርጫ እንደሚደረግ ተስማምቶ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ቢያንስ በመርህ ደረጃ ከሥልጣን የወረዱ ሰዎችን አቶ መለስ ‹‹መሪዎቹ›› እያሉ መጥራታቸው በጣም ያሳዝናል። በእርግጥ እሳቸው እንዳሉት ‹‹የሃይማኖት አዋቂ›› ካሏቸው ሰዎች ምክሩን አግኝተው ከሆነ ድምዳሜ ላይ የደረሱት፣ የመከሯቸው ሰዎች ተሳስተው አሳስተዋቸዋል። ይህን በእርግጠኝነት ለመናገር ደግሞ ነብይ መሆን አይጠይቅም። በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ የአስተሳሰብ መስመር (school of thought) የሚባል ጽንስ ሐሳብ አለ። የዚህ ጽንስ ሐሳብ ዓይነተኛ ባሕሪ ከአንድ ልዩ ሥርዓት ጋር በልዩ ሁኔታ መቆራኘትን (specialization) አመልካች ነው። ለምሳሌ ሱፊይ (ተሰዉፍ) ማለት መንፈሳዊ (spiritual) ነገሮች ላይ በጣም የሚያተኩር መስመር እንደማለት ነው። ይህ የአስተሳሰብ መስመር በተገለጸው ሁኔታ ራሱን ከመንፈሳዊነት ጋር ያስተሳሰረ እንጂ ከሌላው ሙስሊም ተለይቶ ‹‹የተለየ ሙስሊም›› የሚባልበት ቀመር የለም።

ወደ መሠረታዊው ነጥብ ስንመጣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹አሕባሽ›› የነባሩ እስልምና አስተምህሮ ወይም ሱፊይ እንደሆነ ነግረውናል። በመሠረቱ አሕባሽ ራሱን ‹‹ሱፊይ›› ብሎ ይጥራ እንጂ

‹‹ሱፊይ›› አይደለም። ለዚህ ደግሞ የእሳቸው ንግግር በራሱ መልስ ይሰጠናል። ‹‹ነባሩ እስልምና ነው›› ያሉት የአሕባሽ እንቅስቃሴ የተጀመረው ዐብደላህ አል ሐረሪ በተባለ የሐረር ሰው መሆኑን ነግረውናል። ዐብደላህ አል ሐረሪ ደግሞ የሞተው ከዛሬ ሰባት እና ስምንት ዓመታት በፊት ነው። እስልምና ግን በኢትዮጵያ ላለፉት 1400 ዓመታት ቆይቷል። ታድያ መለስ ‹‹ነባር›› የሚሉት ከ 20 ዓመታት በፊት የተፈበረከን አንጃ ነው?

እንደ አቶ መለስ ንግግር ዐብደላህ አል-ሐረሪ በተወለዱበት ሐረር አካባቢ በ1930ዎቹ ትምህርታቸውን ማስተማር ስላልቻሉ ኢትዮጵያን ለቅቀው በሌሎች አገሮች አስተምህሮታቸውን አስፋፍተዋል። ይህም ከቀዳሚው ንግግር ጋር ፊት ለፊት የሚላተም ነው። ምክንያቱም ዐብደላህ አል ሐረሪ ትምህርቱን ማስተማር ሳይችል የቀረውና የተገፋው አቶ መለስ ‹‹ሱፊይ›› ያሉት ነባር ማኅበረሰብ የሰውየውን ትምህርት ሊቀበለው ስላልፈለገ እና ስለተጠየፈው ነው። ወይም በመለስ መዝገበ ቃላት ‹‹ከ 20 እና 30 ዓመታት በፊት የገባው›› ሠለፊያ ገፍቶት አይደለም። ይህ መከራከሪያ ‹‹አሕባሽ›› የነባሩም ሆነ የ‹‹ሱፊይ›› መስመር አካል እንዳልሆነ ያሳየናል።

ከሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮች አንጻር ስናየውም ‹‹አሕባሽ›› መንግስትም ሆነ እነሱ ራሳቸው እንደሚሉት ‹‹ሱፊይ›› አይደለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እውቅና ያለውና ሥርዓተ ትምህርቱን በሱፊይ የአስተሳሰብ መስመር የቀረጸው የግብጽ አል-አዝሐር ዩኒቨርሲቲ የ‹‹አሕባሽ›› አንጃ የሱፊያን የአስተሳሰብ መስመር እንደማይከተል ሃይማኖታዊ ብያኔ ሰጥቷል። በ‹‹ሱፊይ›› የአስተሳሰብ መስመር ልሂቅ የሆኑትና እንደ ዓለም አቀፍ ማጣቀሻ የሚወሰዱት ኢማም ወሕበቱ ዙሐይሊም እንዲሁ አንጃው የ‹‹ሱፊያ››ን የአስተሳሰብ መስመር በጭራሽ የማይከተል ስለመሆኑ በተመሳሳይ መልኩ ብያኔ ሰጥተዋል። የ‹‹አሕባሽ›› አንጃ መሥራች ዐብደላ አል-ሐረሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ አሉ የተባሉ የ‹‹ሱፊያ›› ልሂቃንን ማክፈራቸው (ከእስልምና ወጥተዋል ብለው ብይን መስጠታቸው) ግለሰቡም ሆነ አንጃቸው ሱፊያ አለመሆኑን አስረጂ ነው። ሸኽ ሐቢብ ዐሊ ጀፍሪ፣ ሸኽ ሙሐመድ ሰዒድ ረመዷን አል ቡጢ፣ ሸኽ ሽዕራዊ እና ሌሎችም በርካታ የሱፊያ ልሂቃን ሁሉ ‹‹ሙስሊም አይደሉም›› ተብሎ በ‹‹አሕባሽ›› አንጃ ብይን ተሰጥቶባቸዋል። እነዚህ ሁሉ ነጥቦች መለስም ሆኑ መካሪዎቻቸው ‹‹አሕባሽ›› ሱፊይ አለመሆኑን፣ የነባሩን እስልምና አስተምህሮም ያልተከተለ መሆኑን የሚያስገነዝቧቸው ይመስለኛል። ‹‹ሠለፊይ›› መጤው እስልምና?አቶ መለስ በንግግራቸው ከ 30 እና 20 ዓመታት በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የእስልምና ዓይነት ‹‹ሠለፊይ›› የሚባለው እንደሆነ ነግረውናል።

ስለዚህ ቡድንም ትንታኔ ሲሰጡ ‹‹የሃይማኖት አዋቂዎቹ ነገሩኝ›› ማለትን አልመረጡም። የዚህ አስተሳሰብ ተከታዮች ጥቂቶቹ የአልቃይዳ አባላት እንደሆኑና በብዙ የሽብር ተግባሮች ላይ እንደሚሳተፉም ነግረውናል። ስለ‹‹አሕባሽ›› ሱፊይነት ‹‹ዑለማዎቹ ነገሩኝ›› ያሉት አቶ መለስ ስለ ‹‹ሠለፊይ›› ብዙ ደስ የማይሉ ነገሮችን ሲናገሩ ‹‹አዋቂ›› አለመጥቀሳቸው በጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን በመረጃ ያልተደገፈ እና ወገንተኛ ዕይታ ያሳያል። በመሠረቱ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ‹‹ይሄ ሱፊይ ነው፤ ይሄ ሠለፊይ ነው›› የማለት ሥልጣን ማን ሰጣቸው? ይህን ክፍፍል ሲሠሩስ መነሻቸው ምንድን ነው? የሃይማኖቱ ሰዎች የራሳቸው የቁርአን እና የሐዲስ መመዘኛዎች አሏቸውና። አቶ መለስ ‹‹አንተ ሱፊይ ነህ። አንተ ሠለፊይ ነህ›› የሚል ምደባ ማስቀመጣቸው አሁን የኢትዮጵያ

ሙስሊም ልዩነቶቹን ትቶ በአንድ ላይ ለአንድ ዓላማ መቆሙ ስላላስደስታቸው ይመስላል። ወይስ የትናንቱን የልዩነት ጊዜ መመለስ ተመኝተው? አቶ መለስ አንድ ቦታ ‹‹ሙስሊም›› ማለቱን ትተው ‹‹ክርስትያኑ እና ሱፊው በሰላም ይኖር ነበር›› ብለዋል። ተመለከታችሁት!? ‹‹ክርስትያኑና ሱፊው...››! ይህ ምን ማለት ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር?

እንደ አቶ መለስ እምነት የሱፊይ እስልምና በኢትዮጵያ ከሌላው ሃይማኖት ጋር ተቻችሎ ለዘመናት ኖሯል። ምንም እንኳ አቶ መለስ ሱፊያን ‹‹ሰላማዊና ተቻችሎ የኖረ›› ብለው ቢጠቅሱትም እንቅስቃሴውን ግን ትኙ (passive) አድርገው ከመግለጽ አልተቆጠቡም። ይህ ምናልባትም የኢትዮጵያን ‹‹ሱፊያ›› ካለማወቅና ካለመገንዘብ ይመስለኛል። አቶ መለስ እንዳሉት የቀድሞዎቹ ሥርዓቶች አድሎአዊ አሥተዳደሮች ነበሯቸው። እነዚህን አድሎአዊ አሥተዳደሮች በነፍጥ ጭምር ታግለው ሃይማኖቱ ለዚህ ትውልድ እንዲደርስ ያደረጉት ቀደምት ‹‹ሱፊይ›› አባቶቻችን ናቸው።

በኢትዮጵያ ታሪክ በርካታ እስላማዊ ሡልጣኔቶች (መንግሥታት) እንደነበሩ ይታወቃል። እነዚህ ሁሉ ሡልጣኔቶች ምሥረታቸውን ያገኙትም ሆነ ይተዳደሩ የነበሩት በቱባ ሱፊዮች ነው። በሊቢያ አረመኔውን ፋሽስት የጣልያን ቅኝ ገዥ ሲታገሉ የነበሩት ዑመር ሙኪታር ‹‹ሱፊይ›› ናቸው። ታሪካዊቷን እየሩሳሌም ከመስቀል ጦረኞች አላቅቆ በሙስሊሞች እጅ ያገባው ጦረኛ ሶላሐዲን አል አዩቢም ‹‹ሱፊይ›› ነበር። ይህ ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስን የመከሯቸው ሰዎች (በእርግጥም መከረዋቸው ከነበር) መሳሳታቸውን ያሳያል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ‹‹ሠለፊይ›› የገለጹት ባሕሪ በብዙ መልኩ እውነቱን ያገናዘበ አይደለም። ስለ ‹‹ሠለፊይ›› ሲያወሩ በስፋት የሄዱበት ‹‹እስላማዊ መንግሥት›› የሚለውን ቃል ነው። ‹‹ሠለፊይ›› በሌላው ዓለም እንዳደረገው ኢትዮጵያ ውስጥም እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት እንቅስቃሴ ያደረገ መሆኑን ቢጠቅሱም አስረጂ አድርገው ሊያቀርቡት የሚችሉት የምሳሌ እንኳ ማስረጃ ማጣታቸው የነገሩን ትክክል ያለመሆን ያሳብቃል። አቶ መለስ የሚሏቸው ሰዎች በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት ጥረት እያደረጉ ከሆነ ማስረጃ የሚመስል ነገር ለምን ለፓርላማው አባላት አላቀረቡም? በቁጥር የማነስም ጉዳይ በአቶ መለስ ንግግር ተዳስሷል።

ሠለፊዮች ‹‹መንግሥት ቁጥራችንን አሳነሰብን›› የሚል ዘመቻ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል። ይህ ምኑ ከወንጀል ጋር እንደሚገናኝ አይገባኝም። ከጥቂት ዓመታት በፊት የአማራ ሕዝብ ቁጥር ከተጠበቀው በላይ ማነሱን ተከትሎ አንድ የገዢው ፓርቲ የፓርላማ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ ‹‹ቁጥራችንን አሳነሳችሁብን›› በሚል ሙግት አስነስተው እንደነበር ትዝ ይለኛል። የሕዝብ ቁጥር በብዙ መልኩ ብዙ ትርጉም በሚያስጥበት አገር የቁጥር ማነስ አለማነስ ጥያቄ ለምን በጠቅላይ ሚኒስተሩ መዝገበ ቃላት ከእስላማዊ መንግሥት ምሥረታ ጋር ይያያዛል? ለጥያቄዎቻችንስ ምላሽ የሎትም?በማክሰኞው የአቶ መለስ ንግግር አሁን እየተነሣ ያለውን የሙብት ጥያቄ ‹‹ሠለፊይ›› ብለው ካሰቡት ወገን የመጣ ብቻ ተደርጎ ነው የቀረበው።

የሙብት ጥያቄው ግን የትኛውንም የአስተሳሰብ መስመር ሳይለይ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እየተንጸባረቀ መሆኑ አይጠፋቸውም። በሚሊዮን የሚቀጠሩ ሰዎችን ጥያቄም ‹‹የጥቂቶች››

ብለው መግለጻቸው ተገቢ አይደለም። ንቅናቄውንም አሁን በጎረቤት አገራት በግብጽ፣ በሊቢያ፣ በቱኒዚያ እየተካሄደ ካለው ማዕበል ጋር አቆራኝተውታል። ሕዝቡ ያነሣው ከመንግሥት ሥልጣን ጋር ያልተነካካ ንጹህ አገራዊ የሙብት ጥያቄ ቢሆንም ከሌላ አገር፣ በተለይም ከዐረብ አገራት አጀንዳዎች ጋር ተሳስሮ ቀርቧል። ይህ የሚመነጨው ምናልባትም የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ኢትዮጵያዊነት ካለመቀበል ይሆናል። ይህ ሁሉ ሆኖም ግን አቶ መለስ መሠረታዊውን የሕዝብ ጥያቄ መመለስ አልተቻላቸውም። መንግሥት "ሕገ-መንግሥትን በማስከበር ሽፋን ሃይማኖት ውስጥ ገብቶ የሚፈጽመውን ተግባር ሊያቆም ይገባል" የሚለው ጥያቄ ከእሳቸው ምላሽ አላገኘም። ጠቅላይ ሚንስትሩ የ"አሕባሽ"ን የግዳጅ ሥልጠናዎች በተመለከተ መንፈሳዊ ተቋሙ (መጅሊስ) በሥልጠናዎቹ ላይ "ብትመጡ ጥሩ ነው" ስላለን ብቻ ተገኝተን ስለ ሕገ-መንግሥቱ አስተምረናል›› ቢሉም ሕዝቡ የሚያውቀው ግን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና የፍትሕ ቢሮ ኃላፊዎች በነበሩበት መጀሊሱ ሥልጠናዎቹን በግዳጅ ጭምር ሲሰጥ እንደነበር ነው።

የሙብት እና የነጻ መሪ ድርጅት ጥያቄውን አቶ መለስ "የጥቂቶች" በሚል ሽፋን የእስላማዊ መንግሥት ምሥረታ ሩጫ አድርገውታል። "ጥያቄ እያቀረበ ያለው" የሚሉት የ "ሠለፊያ" ቡድን ብዙ እየሠራ መሆኑን ነግረውናል። አቶ መለስ በመደምደሚያቸው ይሄ እንቅስቃሴ "በእንጭጩ መቀጨት አለበት" ብለዋል። በአቶ መለስ ኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም የዴሞክራሲ እና ሙብት ጥያቄ ማንሳት በሽብር ተግባር አስፈርጀዋል።

ዋይ ኢትዮጵያ።

የመጅሊስ ምርጫ፡ ከ‘ግሎባል’ ወደ ‘ማዘጋጃ’

ቢን ምህ

ግንቦት 2/2004

በ2001 የቀድሞ መጅሊስ ሹማምንት የእነ አቶ ኤሊያስ ሬድማን ቡድን እንዝህላልነትን ለማረምና ሙሰኞችን ለፍርድ ለማቅረብ በሚል ሰበብ በግሎባል ሆቴል በተሰየሙ ጉባዔተኞች አዲስ፤ ታማኝና የአህባሽ ጥምቆች (ቅምጦችም ይሆናሉ- የፖለቲካ)፤ አረንጓዴ ጠምጣሚዎች አቶ አህመዲን ጨሎን ራስ አድርገው ሌሎች ደግሞ በተዋረድ ተሹመው (ተመርጠው አላልኩም) በጓሮ በር ወንበሩን ያዙት፡፡ እኛም ከዛሬ ነገ አቶ ኤሊያስ በ50 ሚሊዮን ብር ሙስና ተከሶ ፍርድ ቤት ሲቆም (ወይም ሲቀመጥ) ለማየት በጉጉት ስንጠብቅ፡ ስንጠብቅ .... (የዋሆች!) ተረስቶ ቀረ- ወይ አለማወቅ! ለካስ ለመሾም ሙስና ዋነኛ መስፈርት ሆኖ ኖሯል!

እነ ጨሎም ቢሮውንና ሙስናውን ከተላመዱ በኋላ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ’አህባሽ’ን የማጥመቅ ዘመቻ እንደ ዋና የቤት (ቢሮ) ስራ ተሰጥቷቸው ተረከቡ፤ ከዚያም ቅድመ-ማፅዳት ስራ ጀመሩ፡፡ ‘IIRO’ን ማባረር፣ አወሊያን መረከብ፣ ለመንግስት መረጃ ማቀበል፤ የሙስሊሙን የልብ ትርታ መለካት ወዘተ.... (ስንቱ ይዘረዘራል??)..

በመጨረሻም ከሊባኖስ 200 የአህባሽ “ዓሊሞችን” በማስመጣት በሃምሌ 2003 በሐረር ከተማ ማጥመቁን በይፋ ጀመሩት፡፡ ቀጥሎ በሌሎችም ቦታዎች አፋፋሙት፡፡ ህዝበ-ሙስሊሙም ነገሩን በሹክሹታ፤ በፊት-መፅሃፍ (facebook) ጫካ፤ በጋዜጣና መፅሄቶች መቃወሙን ተያያዘው፡፡ ተቃውሞው በውጭ ሃገራት አይሎ ነበርና በNovember 21, 2011 በአሜሪካ የተቃውሞው ሰልፍ ፈነዳ፡፡ በሀገር ውስጥ ግን ፍርሃት እንደነገሰ ነው፡፡ ሆኖም በታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ የአወሊያ ኮሌጅ መዘጋትና መምህራንና ኢማም መባረርን ተከትሎ በጀግኖች የአወሊያ ተማሪዎች አገር ውስጥም የተቃውሞ ሰልፍ ፈነዳ፡ አዲሳባዎችም አጎራባቾችም ሆኑ ክፍለ-ሀገሮች ከቤታቸው፤ የፊት-መጽሀፍ (facebook) ታጋዮችም ከጫካው በመውጣት የተቃውሞ ትግሉን ተቀላቀሉ፡ የቅሬታ ፊርማም ተጧጧፈ፤ ጥያቄውም ከአወሊያ ጉዳይ ወደ መጅሊስ ይውረድ አደገ፤ መጅሊሶችም ጨነቃቸው፤ ተቃውሞውም ጠነከረ፤ በኮሚቴ ተዋቀረ፤ ወደ ክፍለ-ሀገርም ተሰራጨ፡፡ ሀገራዊም ሆነ፡፡

ተቃውሞው እስካሁን የተዋጣለት አካሄድ መሄድ ችሏል፤ ከመቼውም በላይ አንድነት ጠንክሯል፤ ድጋሜ ላይላላም ሙስሊሞች ተማምለዋል፤ ግፊቱ አንዋር መስጅድ ላይ ከትሟል፤ የመንግስት ባለስልጣናትንም አወዛግቧል፤ ወደ ዓለምም ተስተጋብቷል፡፡

በጀት ለ2004

መጅሊስም በጥር ወር ላይ የ2004 አመታዊ በጀቱን ይፋ አደረገ፤ 636 ሚሊዮን ብር!! (“ከየት መጣ?” ብሎ መጠየቅ ያስቀስፋል!) “ለአወሊያም 6 ሚሊዮን ብር ስለተመደበለት ሰልፉን

ትታችሁ ወደ ቤታችሁ ግቡ” ተባለ!! “አል-ቁድስ” ጋዜጣም ተገዛ፤ በቅርቡም የሀገር ውስጥ ዊኪሊክስ ይፋ እንዳደረገው ከበጀቱ ውስጥ 203 ሚሊዮን ብር የሚሆነው በአቶ ጨሎ ልጅ የግል ቁጠባ ሂሳብ መግባቱን፤ ለ“አል-ቁድስ” ጋዜጣ በየወሩ 88ሺህ ብር መሰጠቱን፤ አብዛኛው ገንዘብ ለአህባሽ ስልጠናና ለጫት ወጭ እንደሚውል መታቀዱን ሰማን- ጆሮን አትስማ አይሉት፡፡

የጉልቻ ለውጥ ዜና

አሁንም በሀገር ውስጥ ዊኪሊክሰ መረጃዎች መሰረት ሚያዚያ 19/2004 እጅግ መራር ዱብ እዳ ወረደ! በአቶ መለስ የፀጥታ አማካሪ፤ የቀድሞ የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ፀጋዬ በርኸ እና በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር ‘ሙፍቲ’ ሽፈራው ተ/ማሪያም በኩል መጅሊሶች ከስልጣናቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲወርዱ ተነገራቸው፤ መቼም “ከስልጣንና ከጫት ላይ መነሳት ይከብዳል" ይላሉ- የሚያውቁት፡፡ እናም የኦሮሚያና የአዲሳባ መጂሊሶች አለቃቀሱ አሉ፤ ምርጫም በሰኔ ወር እንደሚካሄድ ተነገራቸው (ለነገሩ ከአሁን በኋላ ምን ሊያደርግላቸው- እኛ ከወረድን ሰርዶ አይብቀል ነውና ነገሩ!)- በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር በጀት መዳቢነትና አመራር ሰጪነት ብሎም በዑለማዎች ም/ቤት (በመጅሊሱ የተቋቋመ) ሽፋንነት- ልጅ አባቱን ሊመርጥ!!

ይህንን ዜና ተከትሎ ግንቦት 1 ቀን በአዲሳባ ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ የ”ነባሩ” እስልምና ተከታዮች (ለ“አህባሽ” በአቶ ሽፈራው ተ/ማሪያም የተሰጠ አዲሱ ለምድ) ብቻ ለጉባዔ ታደሙ፤ መከሩም፤ ዘከሩም፤ በመጨረሻ ላይ የእነ ጨሎ ልጅን ጅማሮ አጠናክሮ የሚቀጥል፤ ድክመታቸውን የሚያርም፤ “ጊዜያዊ” የመጅሊስ ፕሬዚዳንት ለመሾም ጠንካራ ታጋይ ማፈላለጉን ተያያዙት፤ ከብዙ ቁፋሮ በኋላ አንድ ጀግና ብቅ አሉ- ከትግራይ ሸህ ከድር ማህሙድ ይባላሉ፡፡

ሸህ ከድር የትግራይ ክልል መጅሊስ ፕሬዚዳንት የነበሩ ሲሆን ከወር በፊት ሚያዚያ 1 ቀን ስልጣናቸውን አስረክበው በታላቅ ሽኝት ለዕድገት ወደ አዲሳባ መጥተው የዑለማዎች ም/ቤት ፕሬዚዳንት አማካሪ በመሆን ተሹመው ለአንድ ወር ያህል ካገለገሉ በኋላ ነው-ትላንት ለ”ጊዜያዊ” የፌዴራል መጅሊስ ፕሬዚዳንትነት የታጩት(“ጊዜያዊ” በመጅሊስ የዘመን አቆጣጠር ገደብ የለውም)፡፡ ከአንድ ወር በኋላም ስልጣናቸውን ይረከባሉ ተብሎ ይጠበቃል-ምናልባት ህዝበ-ሙስሊሙ ቁሞ ከጠበቃቸው!

ይድረስ ለክቡር አቶ መለስ!

ክቡርነትዎ ሦስቶቹ መሰረታዊ ጥያቄዎቻችንን እደግማቸዋለሁ!

1. የመጅሊሳችንን መሪዎች እኛው፣ ከእኛው፣ ለእኛው፣ በነፃነት፤ በግልፅ፤ ያለማንም ጣልቃ-ገብነት በመሳጅዳችን እንምረጥ!!! ስለዚህ ሚኒስትር ሽፈራው የሚባሉት የርስዎ መንግስት ቱባ ባለስልጣን ‘ጥቁሩን አህባሽ አውርደው “ነጩን አህባሽ” (በራስዎ ቋንቋ የ“ነባሩ እስልምና ዑለማዎች”) እንዳይተኩልን’፡፡ ምክንያቱም ጉልቻ ቢለዋወጥር ወጥ አያጣፍጥምና! ክቡርነትዎ....ሰምተዋል!? መጅሊሱ በስንት አባቶቻችን ደም

እንደተመሰረተ በአይንዎ አይተዋል! ደም፤ ህይወት፤ ገንዘብ፤ ጊዜና ጉልበት ተከፍሎበታል……..!

2. አወሊያም ሆነ ሌሎች የህዝበ ሙስሊሙ ተቋማት እንደመጅሊሱ በብዙ መስዋዕትነትና ትግል የቆሙ ናቸው፤ ስለዚህ ለዚህ ለአዲሱ (ይቅርታ! ለ“ነባሩ” ማለቴ ነው) ሃይማኖት ማጥመቂያም ሆነ ለፖለቲካ ስራ መጠቀም አይቻልም፡፡ ሙስሊሙ እንደሰራቸው የራሱ ንብረት ሆነው በራሱ ሰዎች ይተዳደሩ!!!
3. አህባሽ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ1994/5 ጀምሮ በ’NGO’ነት በራሱ ማዕከላት እንደሰበከው ዛሬም መስበክ ይችላል፤ ነገር ግን ተገደንና ተስፈራርተን በሙስሊሙ ህዝብ ተቋማት ውስጥ ያለ አግባብ ሊጫንብን አይገባም፤ ነውርም ነው፤ ኢ-ሰብዓዊም ነው፤ ኢ-ህገ-መንግስታዊም ነው!!

ጥያቄዎቹ አለቁ፤ በቃ አራት ነጥብ(፡፡) አይጨመ(ም)ሩ፤ አይቀነ(ን)ሱ..(‘ጨ’ ና ‘ቀ’ ይጠብቃሉ!)- አራት ወራትን አሳለፉ!!! ስለዚህ ለሚያልፍ ቀን የማያልፍ ጥፋት አይስሩ! ጥቁር ታሪክ አይስሩ!

ይድረስ ለሙስሊም ኢትዮጵያውያን!

ውድ ሙስሊም ወንድምና እህቶቼ፤ እናትና አባቶቼ

ይህ ሃይማኖታዊ የሙብት ጥያቄ ትግላችን ከፍተኛው ጡዘት ላይ ደርሷል-በአላህ ፈቃድ! በዚህም ሁለት ጥቁር ነጥቦች መቼም አይረሱንም-የካቲት 26 ፌዴራል ጉዳዮች “መልሶቹ”ን የተፋቡት ቀን እና ሚያዚያ 19-የአሳሳ ንፁሃን ሙስሊም ወንድሞቻችን በፖሊሶች ጭፍጨፋ በግፍ ህይወታቸው ያለፈችበት ቀን! (አላህ ጀነትን ያጎናፅፋቸው!)

ስለዚህ፤

1. አሁንም ቢሆን አንድም ጥያቄያችን በአግባቡ አለመመለሱን በማወቅ ለሌሎችም በአግባቡ ማስረዳትና ሴራውን ማጋለጥ ብሎም በትግላችን ዙሪያ ሰፊ ግንዛቤ መስጨበጥ….
2. አንድነታችንን በጠበቀና ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከየመሳጅዳችን ቅጥር ግቢዎች ሳንወጣ የተቃውሞ ድምጾቻችን አጠናክሮ ማሰማት (አደራ ስሜታዊነትን እናስወግድ)
3. ማንኛውም ወገን በሚበትናቸው ማስፈራሪያዎችና ዛቻዎች ሳንረበሽና ራሳችን ለራሳችን የደህንነት ኃይል በመሆን ሰላማዊ ተቃውሞአችንን ሊበክሉ የሚቃጡ ሰርጎ ገቦችን በጥንቃቄ መከታተል፤ መሳጅዶቻችን በንቃትና በትጋት መጠበቅ- ለትልቁ ዓላማችን ወሳኝ ነውና!
4. ወደድንም ጠላንም ይህ ተቃውሞ ላይመለስ 11ኛው ሰዓት ላይ ደርሷል! ይህ ጥያቄ ከተቀለበሰ ትልቅ አደጋ አለው፤ ትልቅም ታሪካዊ ጠባሳ ጥሎ ማለፍም ብቻ ሳይሆን ምናልባት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ድጋሜ ላይነሳ ተቀብሮ ሊቀር ይችላል፤ እንደ ቀላል ነገር ካየነው እስልምናን በኢትዮጵያ ውስጥ አጣብቂኝ ውስጥ ማስገባቱ አይቀሬ ነው፤

ለዚያ ደግሞ ተጠያቂዎቹ እኛው ነን፡፡ ስለዚህ ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን እያንዳንዳችን የእስልምና ተሟጋች መሆን ይጠበቅብናል!!

5. መረጃ ኃይል ነው! መረጃን በጊዜው፤ በዕውነተኝነት፤ በአስቸኳይ ለሌሎች ማቀበል ለሰላማዊ ትግላችን ወሳኝ ነው፡፡
6. ለክርስቲያን ወገኖቻችንና ለሌሎችም ኢትዮጵያዊያን የትግላችንን መነሻና እስካሁን የተጓዘበትን ሂደት ማስረዳት አለብን፡፡
7. በምናደርገው ሰላማዊ ተቃውሞ ዙሪያ መጠነ-ሰፊ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን መስራት አለብን፡፡ ስለዚህ ትዕይንቶችን በድምፅና በምስል በመቅረፅ ወደ ኢንተርኔት መረጃ ቋቶች መስቀል፤ ትዕይንቱንም በፅሁፍና በምስል መለጠፍና ለዜና አውታሮችም ማቀበል...ወዘተርፈ.....

እዚህ ላይ ይብቃኝ፤ ትግሉ ግን ይቀጥላል!!

ድል ለኢስላም ነው!! አሏሁ አክበር!! አሏሁ አክበር!!

የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ጉዞና የሰላማዊ ትግሉ ሁነቶች- ከጥር እስከ ግንቦት 2004

ቢን ሞህ

ግንቦት 29/2004

መግቢያ

ከወራት በፊት በአወሊያ የተፈጠረውን የአህባሽና የመጅሊስ ተቃውሞን ተከትሎ ህዝበ-ሙስሊሙ የሚያምንባቸውንና "ጥያቄዬን ለመንግስት ያቀርቡልኛል፣ መፍትሄ ያፈላልጉልኛል" ያላቸውን ከመካከሉ መርጦ ህጋዊነትን በተላበሰ መልኩ እንዲጓዙ ትልቅ ኃላፊነት በማሸከም "የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ" ብሎ መሰየሙ ይታወሳል፡፡ በዚህም ፅሁፍ ውስጥ ጸሃፊው የኮሚቴውን ውልደት፣ መዋቅርና ስልታዊ ጉዞ፣ ስኬትና ጥንካሬዎች፣ እንዲሁም ስጋትና ተግዳሮቶችን ለህዝበ-ሙስሊሙ በግልጽ በማቅረብ ግላዊ ሀተታውን ያሳያል፡፡

ይህ ፅሁፍ የጸሃፊው ትዝብት፣ እምነት፣ ጥንቅርና ትንተና እንጂ የኮሚቴው አቋም አለመሆኑ እንዲታወቅለት ፀሃፊው በአፅንኦት ያሳስባል፡፡

ተቃውሞን ከሰላቅ

በመጅሊሱ የሰላምና ጸጥታ ሃላፊ አቶ ጀማል ተፈርሞ ታህሳስ 21/2004 አወሊያ ግቢ የደረሰው ደብዳቤ 50 የአረብኛ መምህራንን በማሰናበት ኮሌጁን ሲዘጋ፣ የ20 ዓመት አገልጋይ ኢማም ሐጅ ዑመርንም ከነምክትላቸው ከስራ አገደ፡፡[1] ይህ ውሳኔ ያስቆጣቸው የኮሌጁና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ታህሳስ 24 ቀን "ኢማሙና መምህራኖች ይመለሱልን፣ ኮሌጁ ይከፈት!" በማለት የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት ጀመሩ፣ በሁለተኛው ቀን አቶ ጀማል ወደ አወሊያ ጎራ በማለት በስላቅና በፌዝ "የተባረሩት በስህተት ነውና ነገ ይመለሳሉ" ቢልም ተፈፃሚ ሳይሆን ከሳምንት በላይ ዘለቀ፤ ማክሰኞ ጥር 1 ቀን የመጅሊሱ ዋና ጸሓፊ አል-ሙህመድ ሲራጅ መጥቶ ሌላ ስላቅ ሲጨምርበት ተቃውሞው ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋገረ-"የመጅሊስ አመራሮች ይውረዱ!" "አሸዕብ..ዩሪድ..ኢስቃጠል..መጅሊስ!" በሚል ህብረ-ዜማ ታጅቦ፡፡ ተማሪዎቹ ተቃውሞውን ወደ 24 ሰዓት ሲያሳድጉት መጅሊሶች በመደናገጥ ጫና ቢፈጥሩም ተማሪዎቹ "ጁሙዓ አወሊያ እንገናኝ!" ግብዣቸውን አጧጧፉት፣ በዚህም ጥር 4 አርባ ሺህ የሚገመቱ ምዕመናን አወሊያ ሰገዱ፡፡ ለሳምንትም ቀጠሮ ያዙ፤ ተማሪዎቹ ተቃውሞውን ለመቀጠል ሲሞክሩ ቅዳሜ ረፋዱ ላይ መጅሊስ ከግቢው አስወጣቸው፡፡ ተማሪዎቹ ከግቢው መልቀቃቸው ንዴት የፈጠረባቸው ሌሎች ግለሰቦች እሁድ ዕለት ግቢውን በመሙላት በቁጣ "መጅሊስ መውረድ አለበት!" ሲሉ ተወያዩ፡፡ ለቀጣዩ አርብም ቀጠሮ ያዙ፡፡[2]

የኮሚቴው ልደት

በጥር 11 ዓርብ 60ሺህ በሚገመቱ ሙስሊሞች ትዕይንተ-ህዝብ ሲካሄድ ጥያቄውም ከተማሪ አጀንዳነት ወደ ህዝብ አጀንዳነት በይፋ ተላለፈ፡፡ 20 አባላት ያሉት በዳዒያንና ወጣቶች ብቻ የተሞላ ኮሚቴ ተዋቀረ፣ ኮሚቴው የተቃውሞ ፊርማ ማሰባሰቡን ተያያዘው፣ የህዝቡን ስፍር የለሽ በደሎችና ጥያቄዎች ወደ ሰባት በመጨመቅ ለመንግስት ለማቅረብ ሲንቀሳቀስ ባለሙያዎችን ሲያማክር የውክልና ሂደቱ ትክክለኛ ቅርጽ አለመያዙን በመረዳትና ስብጥራቸውን በመመርመር ማሰተካከል እንደሚገባቸው በመስማማት በቀጣዩ ዓርብ ጥር 18 ፊርማውና ስብጥሩ በአዲስ መልክ እንዲካሄድ ለህዝብ አቀረቡ፤ በዚህም ዳዒያን፣ ወጣቶችን፣ አባቶችን፣ ምሁራንና ነጋዴዎችን ያቀፈ 17 አባላት ያሉት ኮሚቴ ተዋቅሮ በአንድ ቀን ብቻ ከ60 ሺህ በላይ ፊርማ ተሰበሰበ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከ500ሺህ በላይ የውክልና ፊርማ ተረከበ፡፡ ከየክልሎችና ከተሞች፣ እንዲሁም ከውጭ ሀገር ከሚኖሩ ሙስሊም ኢትዮጲያውያን ከሚላኩ የድጋፍና ውክልና ደብዳቤዎች፣ የአቋም መግለጫዎች፣ ብሎም በወኪል መልዕክተኞች አማካኝነት አጠቃላይ ከሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት ውስጥ ወደ 45.8% [3] የሚገመቱ ኢትዮጲያውያን ሙስሊሞች "ጥያቄያችንን ለመንግስት አድርሱልን" ብሎ ሃላፊነት ሰጣቸው፡፡[4]

ጉዞ ምዕራፍ፡ አንድ.....እስከ የካቲት 26

ይህን የመጀመሪያውን ጉዞ ብዙዎች "ተስፈኛው ምዕራፍ" (optimistic period) ይሉታል፡፡ ለዚህም መንግስት የሙበት ጥያቄውን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚመልሰው ያላቸውን ሙሉ እምነት በማስታወስ፡፡ ኮሚቴውም ኃላፊነትን ተረክቦ ራሱን በማዋቀር ሰብሳቢ(አሚር)-ዑስታዝ አቡበክር አህመድን፣ ምክትል ዑስታዝ አህመድ ሙስጠፋን፣ የህዝብ ግንኙነት-ዑስታዝ አህመዲን ጀበልን እና ሌሎችንም ሰይሞ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት በመወያየት፣ ባለሙያዎችን በማማከር፣ ልምዶችን በመቅሰምና የችግሮቹን አንኳር መንስኤ ነቅሶ በማጥናት ጥያቄዎቹን ይበልጥ ወደ ሶስት(3) በመጭመቅ ሲያስቀምጥ በቀዳሚነት "አሁን ያሉት የመጅሊስ አመራሮች ተነስተው በህዝብ በሚመረጡ አዳዲስ አመራሮች ይተኩ"፣ "የአህባሽ አስተምህሮ በግዳጅ አይጫንብን" እና "አወሊያና ሌሎች ተቋሞች በሙስሊሙ በተመረጡ ይመሩ" የሚሉ ሲሆን የሁሉንም ብሶትና ጭቆና በማካተታቸው ከመቼውም በላይ አገር አቀፋዊነትን የተላበሱ አገራዊ መነሳሳትንና አንድነትን የፈጠሩ ሆኑ፡፡ አንደኛው ጥያቄ "መሪ ድርጅታችን ለህዝብ ይመለስ"፣ ሁለተኛና ሶስተኛው ደግሞ "መንግስት እጅህን አንሳልን" የሚሉ አንድምታ አላቸው፡፡

ጥያቄዎቹን በደብዳቤ መልክ ከሰደሩ በኋላ የመንግስት በሮችን ለማንኳኳት አሃዱ ሲሉ አቶ ጁነይዲን ሳዶ በግሉ ቢሮው ይቀጥራቸዋል፣ እነሱም በቀጠሯቸው መሰረት በዕለቱ ቢሮው ሲገኙ ስብሰባው የእምነት ጉዳዮችን ወደሚመለከተው ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መዛወሩን ሲነግራቸው፣ የፌ/ጉ/ሚ በበኩሉ በሚኒስትር-ዴዕታው በኩል ሌላ ቀጠሮ ለየካቲት 10 ይሰጣቸዋል፣ ከዚያም እንደገና ተጨማሪ ቀጠሮ ለየካቲት 26 በመስጠት "ጥያቄያችሁ ገብቶናል፣ መፍትሄ ያገኛል" በማለት ጊዜ ለመግዛት ሞክረዋል፡፡

ምንም እንኳ ጥሩ ተስፋዎች ቢኖሩም መጅሊስ የሚሰራውን ፀያፍ ድርጊቶች መቀጠሉንና ተቆጭ ማጣቱን፣ ብሎም የአህባሽ አሊሞች በሬዲዮና የመጅሊሱ ፕሬዜዳንት ክብር ተስጥቶት በኢቴቪ (የካቲት 14) መደስኮሩን ተከትሎ የጥያቄውን መልስ ተስፋ ሊያጨልመው ችሏል፡፡ ቀኑም ደረሰና ከጧት መጅሊሶች ከሰዓት ኮሚቴው በአንድ ጠረጴዛ ተሰየሙ..ከሰብሰባ መሪዎች ፖለቲካ የሚተነፍጉ ቃላቶች ሲረጩ ከመድረክ ደግሞ ኢስላማዊ ቃላቶች…አልተገናኙቶ! የሁለት አለም ሰዎች ይሉሃል ይህ ነው፡፡ ስብሰባ መሪዎቹ በፍረጃ ወዲያው ሊቋጩት ቢሞክሩም ወደ 6 ሰዓት የፈጀ የጦፈ ክርክር አደገ ነገር ግን ስብሰባው ሳይቋጭ በእረፍቷ ሰዓት ውስጥ ያንኑ ህቡዕ ውሳኔያቸውን በአንድ "የግል" ራድዮ ጣቢያ ንፋስ ለቀቁ፡፡

ጉዞ ምዕራፍ፡ ሁለት…..እስከ ሚያዚያ 19

ከየካቲት 26 በኋላ ነበር ኮሚቴው ሁሉ ነገር የገባው፣ ትልቅ ቁጣን አስከተለ፣ ተቃውሞው ይበልጥ ጦፈ፣ ኮሚቴውም መልሶቹን እንደማይቀበል በደብዳቤ ለፌደራል ጉዳዮች ካሳወቀ በኋላ ባለ7 ገጽ ደብዳቤ የጠ/ሚንስትሩን ቢሮ ጨምሮ ለ10 የመንግስት መ/ቤቶች አስገባ፣ ጠ/ሚሩንም በአካል ለማናግር ቢሞክር…ጸጥ….መልስ የለም፡፡[6] የተቃውሞን መጠንከርና ወደ ሌሎች መሳጂድና ክልሎች መዛመቱን የተረዳው መንግስት የተቻለውን ሁሉ ጉዳዮን ለማጠልሸት ሞከረ፡፡ ኮሚቴውም የአንድ ወር እረፍት በመስጠትና ሰላማዊነቱን በማሳየት ሲሞክር፣ የመንግስትን ባህሪ በጥልቀት ከሚያውቁ ሰዎች ነገሮችን ሲረዳ፣ የጠ/ሚኒስትሩም ሚያዚያ 5 ቀን በፓርላማ ብቅ ብለው ከማሳቅ ይልቅ ማሳቀቅ በበዛበት ውሏቸው የፍረጃ አቋማቸውን ሲያውቅ፣ ይህም ይባስ ቁጣን ጨምሮበት ቀጠሮው ደርሶ የ1966ቱን ታሪካዊ ድግግሞሽ ትዕይንተ-ህዝብንም ለማስታወስ ሚያዚያ12 ወደ አንድ ሚሊዮን (በሀገሪቷ ታሪክ ትልቁ) የሚገመት ምዕመናን በአወልያ ተገኝቶ ሰላማዊ ተቃውሞውን አሰማ፣ ይህም አለምን በማስደመሙ ለህዝብ እይታ በአልጀዚራ በኩል ለመጀመሪያ ጊዜ ለአለም ብቅ አለ፡፡ ኮሚቴው አሁንም ሌላ ቀጠሮ በመስጠት ባለ22 ገጽ "የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መደጋገም የእምነት መብት ጥያቄን ህገ ወጥ አያደርውም" በሚል የአቋም ደብዳቤ ጉዳዩን ይበልጥ ለማብራራት ሞክሯል፡፡[7] ተቃውሞውም በአንዋርና በኑር መስጅዶች ቀጠሎ ሳለ ሚያዚያ 19 የአሳሳ ንጹኃን ምዕመን በፖሊሶች መገደልን ተከትሎ ሌላ ትልቅ ቁጣ አስከተለ፡፡

ጉዞ ምዕራፍ፡ ሶስት…..እስከ…

አካሄዱ ያላማረውና የመንግስትን የወደፊት የጥፋት እቅዶች[7] የተረዳው ኮሚቴው ከተክቢራ ሌላ የዝምታ ተቃውሞን ለሀገሪቱ በማስተዋወቅ ሙቀቱን ለማብረድና ሰላማዊነቱን በድጋሜ በማሳየት ሴራዎችን ለማክሸፍ ሰርቷል፡፡ በዚህም አካሄድ ለሚሰነዘሩ ውንጀላዎች አፀፋዊ መግለጫ በማውጣትም ማስተባበሉን አበክሮ የሰራበት ሲሆን፤ ለአካሄዱ መረጃን መሰረት በማድረጉ የተዋጣለት ጉዞ መሄድ ችሏል፤ ይህም አካሄዱና ህግን መሰረት ማደረጉ ሰላማዊና

ለሰላም መቆሙን ከማመልከቱም አልፎ የመንግስትን ክስ ያዜሮዋል(vanish)፡፡ ይህ የሚያሳየው የኮሚቴውን ብስለትና የንቃት ደረጃ ከፍታ ሲሆን መንግስት ኮሚቴውን ከህዝቡ ለመገንጠልና ለይቶ ለመምታት ያመቸው ዘንድ የሚደረገውን ያለ ግልፅ ማስረጃ መግለጫ እንዲሰጥ ጉትጎታዎችንና የማሳሳት ዘመቻዎችን ከግምት ውስጥ እንድናስገባ ስለመረጃ ሃይልነት በተግባር ከማሳየትም አልፎ ሁላችንም የድርሻችንን መረጃዎችን በማጠናቀር እንድናገዘው መረጃ ለማገኘት እንዴት እንደተቸገረ በመግለጽ በማስረዳት አካሄዱን መስመር ማሲያዝ ችሏል፡፡

ተግዳሮቶች (challenges)

1.**ፍረጃና ማጠልሸት፡** መጅሊሱ “አል-ቁድስ” ጋዜጣን ጥር ላይ በመግዛት የኮሚቴው አባላትን ስብዕና በማጉደፍ ስራውን አንድ ሲል መንግስት በተራው በሬድዮ ፋና፣ በኢቴቪ፣ በ“ሪፖርተር”፣ “አዲስ ዘመን” እና “ሰንደቅ” ጋዜጦች በመጠቀም የዶ/ር አልስተር ስሚዝ አራቱንም የማስቀየሻ ሥልቶች (diversionary tactics)[5] በተራም ሆነ በጣምራ መተግበሩን ተያያዘው፡፡ በተለይ “አዲስ ዘመን” ጋዜጣ “ነፃ አስተያየት” አምድ ሶስተኛ ገፅ ላይ እንደሚፅፉ በሚነገርላቸው ቱባ የሃገሪቱ ባለስልጣናት (እንዴ ዊኪሊክስ ሚስጥራዊ መረጃ መሰረት) ያለማንጠልጠያ (ጄኔራል፣ ክቡር፣ ሚኒስትር) በፈጠራ ስማቸው ኮሚቴውንም ሆነ አጠቃላይ ትግሉን “ፀረ-ኢትዮጲያ፣ ፀረ-ልማትና ፀረ-ህገ-መንግስት፣ ፀረ-ሰላም ሃይሎች፣ ፀረ-ዲሞክራሲ፣ ስልጣን ናፋቂዎች፣ አክራሪ፣ አሸባሪ፣ ዋሀብያ፣ ሰለፊያ፣ ድብቅ አላማ ያላቸው፣ ኢስላማዊ መንግስት ናፋቂዎች፣ ፀረ-መቻቻል፣ የውጭ ተላላኪዎች፣ ጥቂቶች፣ በግብር ያኮረፉ፣ የጠረባ ቡድን….”[8] እያሉ በመፈረጅ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ወደ ማሸማቀቅ፣ ለሃገሪቷ ስጋትና ምናባዊ ጭራቅ (scapegoat) አድርጎ በመሳል ሌላውን ህብረተሰብ ከጎናቸው ለማሰለፍ ያደረጉት ሙከራ፤

2.**ማዋከብና ማስፈራራት፡** የኮሚቴውን አባላት እስከ ሰባት በሚደርሱ የደህንነት መኪኖች የማዋከብና ማስፈራራት፤ የስልክ ንግግሮችን መጥልፍና እንደካሴት ድምጽን መቅረፅ፤ ኢሜሎችን በመፈተሽ ፣ ስልክ በመደወል ማስፈራራት፣ የግል ኮምፒተሮችን መቀማትና ስብሰባዎችን በማጨናገፍ ሌሎችም የሚድረጉ ውጣ ውረዶች መብዛት (ለህዝቡ መረጋጋት ሲሉ ባይነግሩንም)፤

3.**ጥርነፋና ግድያ፡** “ቲ-ሸርት ለብሰሃል፣ ወረቀት በትነሃል፣ አወሊያ ሂደሃል፣ ፊልም አይተሃል/በኮምፒዩተር ጭነሃል፣ ሽብር ነዝተሃል፣ አህባሽን ተቃውመሃል፣ መስጅድ ስግደሃል....(ለሴቶችም ይሰራል)”በማለት እየጨመረ የመጣውና ለጆሮ የሚታክት መታሰር፣ መገረፍ፣ ከስራና ፓርቲ አባልነት መባረር፣ አልፎም አሳዛኝ ግድያዎች (አላህ ለሞቱት የሰማዕታትን ደረጃ ያጎናጽፋቸው) ቁጥር ማሻቀብ ከፈተናም በላይ ትልቅ ስጋት ሆኗል፤

4. **ተለዋዋጭ አቋሞች፡** መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱን ከመካዱም አልፎ ትላንት በግልጽ "አህባሽዬ" እያሉ ሲያንቆለጳጳሰው የነበረውን ጠ/ሚኒስትሩን ጨምሮ ሽምጥጥ አድርገው መካዳቸውና "ሱፍያ ነው""ነባሩ እስልምና ነው" ማለታቸው ሌላ ምሽግ መሆኑ፤

5.**ጠመቃና መስፋፋቱ፡** የተቃውሞው ውጥረት ቀጥሎ እያለ የአህባሽ ጠመቃ በአዲስ መልኩ መቀጠሉ ለውዝግብ፣ እስራትና ግጭቶች የቅርብ መንስዔ(immediate cause) መሆኑ፤

6. **ማግለልና መድሎ፡** ኮሚቴውን "ከነቃህ ይቀራል"በሚመስል መልኩ "አይንህን ላፈር" በማለት መንግስት የውይይት መድረኮችን ሁሉ ዝግ ማደረግ ሰላማዊ ጉዞውን ለመጠምዘዝ ከመጅሊስ ጋር ቅልጥ ያለ ፍቅር ውስጥ መግባቱና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

ስኬቶች *(successes)*

1.**አንድነት መጠንከር፡** የዳዒያያን ልዩ ተሰጥኦ፣ ችሎታና ልምድ ከግምት ውስጥ ካለማስገባት የተነሳ (እገሌ ሲራ ብቻ፣ እገሌ ተውሂድ ብቻ፣ ተሰውፍ ብቻ፣ ሀዲስ ብቻ፣ ስለአንድነት ብቻ....) እና የኢስላም ጠላቶችን ውንጀላና ፍረጃ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በማስተጋባትና በማራገብ፣ ሁለት ዋነኛ ምክንያቶች የተፈጠሩትን ትናንሽ "ልዩነቶች" በመሰረቱ መፈጥር ያልነበረባቸውን የአህባሽ መምጣት ከስር መሰረቱ ማጥፋቱ፣ ለመከፋፈል የሚደረጉ ሩጫዎችን መልስ ምትና ብሽሽቅ በሚመስል መልኩ በእየመሳጂዱ የሚደረጉ የአንድነትና ሶደቃ ፕሮግራሞች በሀገር አቀፍ ደረጃ መካሄዳቸው፣ በውጭ ሀገራትም እንደዚሁ ትግሉን ለማገዝ ያለልዩነት ታጥቀው መነሳታቸው፤

2. **ሀገራዊ መነቃቃት፡** "አህባሽ ማነው ምንድን ነው?" የሚለውን ለመረዳት የሚደረጉ ሩጫዎችና ዳዒያንም ህዝበ-ሙስሊሙን ለመታደግ ሲሉ በሚያደርጓቸው ጥሪዎች ለኢስላማዊ መነቃቃት አዲስ ምዕራፍ መከፈቱ፤

3.**ንቃተ-ህሊና ማደግ፡** ከሁሉም በላይ የኮሚቴው ንቃተ-ህሊና በፍጥነትና ባማረ ሁኔታ ነገሮችን በመረዳት ተንታኞችን በሚያስደምም ሁኔታ የትግሉን አቅጣጫ(በአላህ ፈቃድ) በብቃትና በጥራት በጥቂት ወጭዎች(ጥፋቶች) ማስኬድ መቻሉ፣ ይህም ንቃተ-ህሊና ከሌላው ህብረተሰብ በተሻለ መልኩ በሁሉም ህዝበ-ሙስሊም ላይ በተዋረድ ማደጉ፤

4.የአህባሽ ኑፋቄ ለአለም መጋለጥ፡ የአህባሽ ምናባዊ "አህለ-ሱና ነኝ" ባይነትና ስውር ኑፋቄው ከኢትዮጲያ(ሶስት መጽሃፍትና ሲዲዎች መታተም)አልፎ በአለም ታላላቅ ምሁራን በቴሌቪዥን ሳይቀር መተቸቱ፣ በድረ-ገፆች እንደልብ መፃፉ ከሙስሊሙ አልፎ አዲስ ለሚሰልሙ ምዕራባውያን ትልቅ ግብዓት ከመሆን በላይ አህባሽን ለመጀመሪያ ጊዜ ትልቅ ውርደት ማከናነቡ፤

5. **ከወንበር ወረዱ፡** የመጅሊስ አመራሮች "ከእኛ በላይ ማን አለ" እያሉ ሲጀነኑ በድንገት "ከስልጣናችሁ ውረዱ" መባላቸውና ምርጫ እንዲካሄድ መወሰኑን እንደ ስኬት ሲታይ ይህም ለወደፊቱም ለገንዘብ ብለው ለሚሯሯጥ ድንገት "ውረዱ" መኖሩን እንዲገነዘቡ ማደረጉ፡፡

6.**የገጽታ ለውጥ፡** አህባሽ (የሀበሻ ብዙ ቁጥር) የኢትዮጲያውያንን አረባዊ ስያሜ ይዞ በአረቡ አለም በኑፋቄነቱ የፈጠረውን ለሀበሾች ጥሩ ያልሆነ የጅምላ ፍረጃ ገጽታ (image) በዚህ ትግል ሂደት ውስጥ መቀየር መቻላችን እንደ አንድ ስኬት ማየት ይቻላል፡፡

ስጋቶች (risks)

1. **አፀፋዊ ስርፀት** (backfire bow)፡ እንደ ሙስጠፋ አክዮል አባባል "ኢስላማውያን ያለምንም ጭቆና ሲኖሩ የበለጠ ዘመናዊ ሲሆኑ የአስተዳደር ግዴታም ሲጫንባቸው የበለጠ በተግባር (more pragmatic) ይገልፁታል!" በማለት ይገልፃሉ፡፡[11] እውነታውም ይህ ሆኖ ሳለ በሀሰት ውንጀላ የሚሰነዘሩ ጭቆናዎች፣ እስራቶች፣ ግርፋቶች፣ ግድያዎችና ስቃዮች ሲበረቱና ከአቅም በላይ ሲሆኑ ሰብዓዊ የመከላከልን ባህሪይ መሰረት በማድረግ አክራሪነት ከሌለበት ምድር እንዳይወለድ ትልቅ ስጋት መኖሩ፤

2.**ነጥሎ መምታት፡** መንግስት ካለው ልምድ በመነሳት ኮሚቴውንና የተወሰኑትን ሰዎች ነጥሎ በመምታትና በማሰር የተቃውሞውን ተኩሳት "ማብረድ" በሚል እሳቤ ሊፈፅመውና የባሰ ውጥረት ውስጥ እንዳይገባ ትልቅ ስጋት መኖሩ፤

3. **ምርጫና አግላይነቱ፡** የመጅሊሶችን መውረድ ተከትሎ ለምርጫም ሆነ አመራረጥ ስርዓትና ሂደቱ ላይ ሙሉ በሙሉ ኮሚቴውን በማግለል የሚያደርጉት የ"ምርጫ" ሩጫ ከጥቅሙ ጉዳት ስለሚያመዝን ለተጨማሪ ወጥረት መንገድ መጥረጉ፤

4. **ለኮሚቴው ልሣን መስጠት፡** ትግሉ የሁሉም ህዝበ-ሙስሊም በመሆኑና ማንኛውም ግለሰብ መረጃ የመስጠትም ሆነ የመቀበል መብት ስላለው በተለያዩ መንገዶች ሁሉም የራሱን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፣ ኮሚቴው ግን የተቋቋመው በአወሊያ ነውና ስብሰባም የሚጠራው ሆነ ሪፖርትና አዳዲስ መረጃዎችንም የሚያቀርበው አውሊያ ግቢ ነው፡፡ ነገር ግን ባለፈው በፌስቡክ "ድምፃችን ይሰማ" ፔጅ የተላለፈውን ዘግናኝ የፊርዶስን ሞት (አላህ የሰማዕታትን ደረጃ ይስጣት) ተከትሎ በኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን እንደተላለፈው አይነት በኮሚቴው ሰብሳቢዎች በግልፅ ያለተላለፈ መረጃን እነደ ኮሚቴው ልሳን አድርጎ መውሰድ ለኮሚቴው ህልውና እንደስጋት መታየቱ፤

5.**ሀገራዊ ቀውስ፡** ከላይ የተጠቀሱት ስጋቶችና ውጥረቶች ተዳምረው ከቀጠሉ ብሶትን በመቀስቀስ ሀገራዊ መልክ ያለው ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስ እንዳያስከትል ያሰጋል፡፡[12]

መፍትሄዎች *(solutions)*

የዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ መፍትሄው አጭርና ቀላል ሲሆን መንግስት ህገ-መንግስቱን ከወረቀት ባለፈ ተግባራዊ በማደረግ መጅሊስን ለህዝበ-ሙስሊሙ መልሶ እጁን ከሃይማኖታዊ ድርጅቶች በመሰብሰብ ለዜጎች ተግባራዊ ዴሞክራሲ በማጎናጸፍ፤ [13]

ሶስቱን መሰረታዊ የህዝበ-ሙስሊሙን ጥያቄዎች በቅንነት በመመለስም ሆነ ኮሚቴውንና በህዝብ በሚመረጡ አስመራጮችን ያካተተ ግልፅ ትክክለኛ፣ ነጻና ፍትሃዊ የመጅሊስ ምርጫ ማካሄድ፣ አህባሽንም "ወይ በመድራሳህ ወይ ወደ ሊባኖስህ" ብሎ በመፋታት እርቅ ማውረድ፤ [14]

ያለአግባብ የታሰሩትንና የታገቱትን በአስቸኳይ በመፍታት፣ የመጅሊስ ጥፋቶችን፣ "ምክራዊ" ውድመቶችንና ድርጅት የማፍረስ ቅጣቶችን በማንሳት በአስቸኳይ ወደ ስራ እንዲገቡና ጤናማ ህይወት እንዲመሩ እድል መስጠት ወሳኝ ነው፡፡

ድል ለኢስላም ነው! አላሁ አክበር!

ENDNOTES

1. "ሠለፊያ" ጋዜጣ፣ ቁጥር 550/1፡ ጥር 4 & 11፡ 2004

2."የሙስሊሞች ጉዳይ" መፅሄት ቁጥር-17፡ የካቲት 2004 www.yemuslimochguday.net

3. CIA: The World Fact Book (2007)

4. "የኢትዮጲያ ሙስሊም የት ነው?" መፅሃፍ የካቲት 2004, ገጽ 391-399

5. "የሙስሊሞች ጉዳይ" መፅሄት ቁጥር-18፡ ሚያዚያ 2004

6. "ሰውቱል ኢስላም" ጋዜጣ የካቲት 09፡ 2004

7. ሸህ ጣሃን የመግደል እቅድ፣ ኢሳት ዜና ግንቦት 3፡ 2004 www.ethsat.com

8. "ሰውቱል ኢስላም" ጋዜጣ ሚያዚያ 19/25፡ 2004

9. "አዲስ ዘመን" ጋዜጣ የካቲት 21, መጋቢት 8/9/12/28….,ግንቦት 17፡ 2004 እና ሌሎችም

11. Alemayehu Fentaw, Ethiopia: Are Islamists Coming? TRANSCEND Media Service, May 23, 2012. https://www.transcend.org/tms/?p=19256

12. Jawar Mohammed, Meles' recycled old tactics being rendered obsolete by a new and shrewd adversary, www.ayyaantuu.com, May 25, 2012.

13. Jawar Mohammed, Growing Muslim Activism and the Ethiopian State: Accommodation or Repression, www.opride.com , March 23, 2013.

14. Alemayehu Fentaw, Is the specter of the Arab Spring haunting Ethiopia? Open Democracy, June 04, 2012.http://www.opendemocracy.net/alemayehu-fentaw/is-specter-of-arab-spring-haunting-ethiopia

አንድነታችን- የ"ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ" ትልቁ ውጤት

ዑመር አህመድ ረመዳን

ግንቦት 25/2004

የሰው ልጅ በመልክና በቁመና እንደሚለያየው ሁሉ በአመለካከትም ይለያያል፡፡ አብዛኛውም ሰው የየራሱን አመለካከት ይዞ መኖርን ይመርጣል፡፡ ነገር ግን ልዩነቱን እንደያዘ ከሌሎች ጋር በአንድነት መኖር ይችላል- *የግሉን ለግሉ በማድረግ በጋራ ጉዳዮች ላይ አንድ በመሆን*፡ በሌላ አነጋገር "በልዩነት ውስጥ አንድነትን በመፍጠር" ማለት ነው፡፡

አንድነት (ህብረት) ውበት ነው፡፡ አንድነት ጥንካሬ ነው፡፡ አንድነት ሀይል ነው፡፡ ሰዎች በየአካባቢያቸው የሚከሰቱ ማህበራዊ ችግሮችን ለማስወገድ የሚችሉት አንድ ሁነው ሲንቀሳቀሱ ነው፡፡

"አንድነት" በኢስላም አይን ሲታይ ደግሞ ለጋራ ጥቅማችን የምናደርገው ትስስር ብቻ ሳይሆን ሀይማኖታዊ ግዴታም ሆኖ ይገኛል፡፡ ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ዓሊም ዶ/ር ጀይላን ኺድር ሚያዚያ 28/2004 ዓ.ል. በአየር ጤና አንሷር መስጂድ ተዘጋጅቶ በነበረው የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ላይ በአጽንኦት እንደተናገሩት "በቁርአን፣ በሱንና እና በአላህ የአንድነት ገመድ መተሳሰር በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በዓለም ሙስሊሞች ላይ ግዴታ የተደረገ ኢስላማዊ ደንብ ነው፡፡ ይሄን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) በቁርዓኑ ሲናገር "ሁላችሁም በአላህ ገመድ ተሳሰሩ፣ አትለያዩም" ብሎናል፡፡

አላህ ሱ.ወ. ዋጂብ (ግዴታ) ያደረገብን ኢስላማዊ አንድነት ለህይወታችን በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ነብዩ መሀመድ ሰ.ዐ.ወ. ሙስሊሞች ሊረዳዱና ሊተባበሩ እንደሚገባ በሐዲሳቸው ሲያስተምሩ እንዲህ ይላሉ፤

"አንድ ሙሰሊም ለሌላው ሙስሊም ወንድም ነው፡፡ መጥፎ ሊተገብርበትና ለሌላ ወገን አሳልፎ ሊሰጠው አይገባም፡፡ የአንድ ሙስሊምን ጉዳይ ያሟላ፣ አላህ የርሱን ጉዳይ ይሞላለታል፡፡ከአንድ ሙስሊም ላይ አንዳች ችግር ያነሳ፣ አላህ በፍርዱ ቀን ችግሩን ያነሳለታል፡፡ አንድን ሙስሊም የጠበቀና የተከላከለ አላህ በፍርዱ ቀን እሱን ይጠብቀዋል፣ይከላከልለታል፡፡" (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ካለመተባበር ወደ መተባበር

ከጥቂት አመታት በፊት በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ዘንድ ሲታይ የነበረው መከፋፈልና መቆራቆስ ናላችንን አዙሮት ነበር፡፡ በጥቃቅን ምክኒያቶች የሚፈጠሩ ሽኩቻዎች ሙስሊሞችን ሆድና ጀርባ

እስከ ማድረግ ደርሰዋል፡፡ የመጅሊስ አመራር ተብለው የተሾሙብን "ሀጂዎች" እና "ሼኮች" ችግሩን ከማስወገድ ይልቅ እንደ እብድ ገላጋይ ዱላ እያቀበሉ ህዝበ ሙስሊሙን ሲያናቁሩት ነበር፡፡ ዘንድሮ ግን የባሰውን አመጡብን፡፡ "ህገ-መንግስት እናስተምራለን" በሚል ሰበብ ኢማሞችና ሙአዚኖቻችንን በስልጠና አዳራሾች ውስጥ እያጎሩ *"እስከዛሬ የቆያችሁበት አስልምና የተበከለ ነው፡፡ ስለዚህ ሁላችሁም ሸሀዳ በድጋሚ መያዝ አለባችሁ፡፡ ለዚህ ደግሞ ቅድመ ግዴታው "ኢብን ተይሚያህ ካፊር መሆኑን ማወጅ ነው"* የሚል ሰበካ ጀመሩ፡፡ ይሄኔ ግን ህዝበ ሙስሊሙ "በቃኝ!" አለ፡፡ *"እንዲያውም እስከዛሬ በጫንቃችን ላይ ለጨፈራችሁት በህግ መጠየቅ አለባችሁ"* የሚል ድምጽ አሰማ፡፡ *"አሸሻዕቡ ዩራዱ ኢስቃጠል መጅሊስ!"* በሚል መፈከር ዙሪያ ተሰለፈ፡፡

"እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ነበንው ነው!" ነገሩ፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ለረጅም ጊዜ በራሱ ተቋም ላይ የሚምነሸነሹትን የመጅሊስ አመራሮች አይቶ እንዳላየ ቢያልፋቸውም "ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ"ን (Ahbashism Campaign) ግን ሊያስተናግድላቸው አልቻለም፡፡ ለወትሮው በየምክንያቱ ሲናቆር የነበረው ሁሉ "ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ"ን ለማክሸፍ በአንድነት ተሰልፏል፡፡ ሙስሊሞችን በተበከለ ፍልስፍና ለማጥመቅ የተወጠነውን "ይሁዲ ሰራሽ" እቅድ አከሽፏልም (ያልተቋጨ ጉዳዮች ቢኖሩም እንኳ)፡፡ የአንድነትን ውጤት በተግባር አሳይቷል፡፡ የህብረት ጥቅምንም በተጨባጭ አስመስክሯል፡፡

አል-ሓምዱሊላህ!!

የአንድነታችን መሰረቶች

በሙስሊሞች ጉዳይ መጽሄት የሚያዚያ ወር እትም ላይ አቡ ሃቅ የተባሉ ወንድማችን *"ቀጣይ ፈተናዎቻችንና የመፍትሄዎቻችን ቁልፎች"* በሚል ርእስ በጻፉት መጣጥፍ የአንድነትን አስፈላጊነት ሲያትቱ እንዲህ ብለው ነበር፡፡

"ለምንድነው አንድነት የሚያስፈልገን? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ሶስት ነገሮችን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

አንደኛ፡- የአላህ ትዕዛዝ ስለሆነ! ቁርኣን "በአላህ ገመድ አንድ ሆናችሁ ተያያዙ፣እንዳትለያዩ" ይላል፡፡ ይህን የአንድነት ስሜት አጠናክረን እንድንይዝ አላህ ስለሚያዘን የአላህን ትዕዛዝ መፈጸምም ጭምር ነው፡፡

ሁለተኛ፡- በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ውስጥ የኖርን ሰዎች ተመሳሳይ የሆኑ ታሪኮችን አሳልፈናል፡፡ ተመሳሳይ የሆኑ ገድሎችን ሰርተናል፡፡ ተመሳሳይ የሆኑ ጭቆናዎችንም አሳልፈናል፡፡ በአሁኑ ጊዜም ተመሳሳይ በሆነ ፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ እየኖርን ነው፡፡ ለወደፊትም ተመሳሳይ የሆኑ ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን እንጋራለን፡፡ ስለዚህ በጣም የተያያዝንና የተጣመርን ነን፡፡ አንዳችን ላይ የሚደርሰው ችግር በሌላው ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ

ቀላል ባለመሆኑ የሚያስተሳስሩን ገመዶች ጠንካራ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሙብታችን ሲጣስ በጋራ መቆም የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ግዴታ ይሆናል፡፡

ሶስተኛ፡- በአንዳንድ አካባቢዎች አነስተኛ ሆነው የሚኖሩ ሙስሊሞች አሉ፡፡ ለነዚያ ሙስሊሞችም ድምጻችንን ለማሰማት እንድንችል አንድ መሆናችን ወሳኝነት አለው፡፡ ሁላችንም በአንድነት ተጋግዘን የሚደርስባቸውን ጭቆና ለማስወገድ ካልጣርን በሌላ ማህበረሰብ ተውጠው በበደልና ጭቆና ውስጥ ይሰነብታሉ ማለት ነው፡፡"

የትግላችን ዋነኛ ውጤት

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባለፉት አስር ወራት ሲያስተጋቧቸው የነበሩት "የአህባሽን የተጣመመ አስተምህሮት አንፈልግም ፣ያልመረጥናቸው የመጅሊስ ባለስልጣናት አይወክሉንም" የሚሉ መፈክሮችና እምነትን በነጻነት የማራመድ ሙብት ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ምላሽ ባያገኙም በታሪክ ማህደር ላይ ሊሰፍር የሚገባ አንድ አቢይ ቁም ነገር አስመዝግበዋል፡፡ ይህም አንድነታቸውን ለማጠናከር መቻላቸው ነው፡፡ በዚህም የሙስሊሙን ህብረት እንደ ጦር የሚፈሩ ሀይሎች ካስቀመጡላቸው ወጥመድ ውስጥ በመግባት ይፈጥሩት ከነበረው ከፍተኛ የመፈረካከስ አደጋ ለማምለጥ ችለዋል!፡፡ በሌላ በኩል አሁን የተፈጠረው ህብረት መጪው የኢትዮጵያ ሙስሊም ትውልድ (generation) በጤናማ መሰረት ላይ የተገነባ ይሆን ዘንድ የመነሻ ግብአት ሊሆን ይችላል የሚል ተስፋን ያሳድራል፡፡

ለነገም ቢሆን አንድነት

ዛሬ በኢስላም ላይ የተጋረጠው አደጋ አቀራርቦናል፡፡ "ከአክራሪነት የጸዳ መንገድ ነው" ተብሎ በአሜሪካ፤ ጽዮናዊያን፤ ፌዴራል ጉዳዮች ወዘተ... የተጨበጨበለት የ"አሕባሽ" ፈተና የማንቂያ ጥሪ ሆኖልን አንድነታችንን የሙጥኝ ብለናል፡፡ ነገስ? ወደ ድሮው ሽኩቻና ግለኝነት ልንመለስ ነው? "ውሃ ሊቋጥሩ" በማይችሉ ሰበባ ሰበቦች እያተፋጨን ህብረታችንን ልናበላሽው ነው? አንድነት የሚያስፈልገው በመከራና ጭንቅ ጊዜያት ብቻ ነው?

አይሆንም ያ ጀመዓ! ኢስላም ምን ጊዜም ቢሆን በአንድነት ያዛል፡፡ ዛሬ ተአምራዊ ውጤት ያሳየንበትን ህብረት ነገም ቢሆን መቀጠል አለብን፡፡ የኢስላም ጠላቶችን ፋታ የነሳንበት አንድነታችን ዘላቂ እንዲሆንልን እስከመጨረሻው መጣር አለብን፡፡

"ዘመቻ ጥምቀተ አሕባሽ" በተሰኘው ክፉ ውጥን ጽዮናዊያን የፈበረኩት የአሕባሽ ፍልስፍና በኛ ላይ እንዲሞከር የተፈረደብን ሕብረታችንን ባለማጥበቃችን ነው፡፡ አሁን ፈተናውን ለመቋቋም የቻልነው ደግሞ አንድ በመሆናችን ነው፡፡ ስለዚህ በከባድ ጥረትና መስዋእትነት የገነባነውን ህብረት መንከባከብ አለብን፡፡ ፈጣሪያችን አላህ (ሱ.ወ) እርዳታውን የሚለግሰን አንድነታችንን ካጠበቅን ብቻ ነውና፡፡ ማን ያውቃል? አላህ (ሱ.ወ) አህባሽ የተባለውን የጥመት ቡድን ወደ

ኢትዮጵያ የላከበት ዋነኛ ምክንያት ኢስላማዊ አንድነት በውስጡ ያዘለውን ከባድ መልእክት ለኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ማስተማር ቢሆንስ?

አላህ ከኛ ጋር ይሁን!... ያ አላህ ኢስላማዊ አንድነታችንን ጠብቅን!... አሚን...

Ethiopian Muslims and the Ahbash Controversy

Muhammad Ali Alula al-Hashimi*

February 2012

Al-Ahbash Movement, also known as the Association of Islamic Charitable Projects.

It all began back in July 2011. The Ethiopian government, through the offices of the Islamic Supreme Council of Ethiopia, called a conference to be attended by the known Islamic scholars and leaders of Ethiopia. The scholars and leaders dutifully heeded the government summons. It was not long after the start of the conference that most of the attendees walked out in disgust at the proposals that were placed before them. The Ethiopian government was essentially delivering an edict — that had been prepared with the help of Haggai Erlich, the Israeli-Zionist author specializing in Ethiopian history — that henceforth all Ethiopian Muslims would be mandated to follow the particular controversial, indeed heretical, teachings of the Lebanese Ahbash Movement.

The attendees could not believe what they were hearing. Here was a secular government that had huddled with an Israeli-Zionist writer to dictate to the 40 million-plus Muslims of the Federal Republic of Ethiopia how they should, indeed must, practice their religion from now into the foreseeable future. Clearly, the conference was an insult on three counts:

1. The Ethiopian government, at the very least, is in violation of the Ethiopian Constitution. Article 11 of the Ethiopian Constitution under

"Separation of State and Religion" says: (i) state and religion are separate; (ii) there shall be no state religion; and (iii) the state shall not interfere in religious matters and religion shall not interfere in state affairs (emphasis added).

2. The government apparently is showing complete contempt for Ethiopian Muslims by inviting an Israeli Zionist to help in its nefarious project. As Muslims the world over know, the Zionists of Israel have been involved in the systematic ethnic cleansing, indeed the uninhibited genocide, of the predominately Muslim people of Palestine for more than half a century. Furthermore, the racist Zionist project has as part of its satanic agenda to destroy the Dome of the Rock and Masjid al-Aqsa, the third holiest religious site in the Islamic world.

3. Most egregious of all is the government's boldfaced audacity to think that Muslims anywhere, let alone in Ethiopia, can be dictated to about how to practice their religion. The first revelation, indeed command, to the Prophet Muhammad (pbuh) was to, "Read in the name of Your Sustainer, The Master of all creation" (96:1). This fundamental command was meant for every Muslim to study and learn to the maximum extent of his or her intellectual capacity the religion in all of its intricacies with a free mind and free will in order to arrive at a level of unassailable certainty as to the veracity of the teachings of Islam. Furthermore, it has been recorded in the generous Qur'an, the exact revealed words of Allah (swt), the Creator, to His Prophet Muhammad (pbuh) that there is no compulsion of any kind in religion. But the Ethiopian government seems hell-bent on compelling the Muslims of Ethiopia to believe in a way that has been chosen by the government. How ludicrous and indeed dangerous! The Ethiopian government apparently is courting disaster and preparing for its own demise. The Muslims of Ethiopia, particularly the youth, are not going to sit idly by in the face of this horrendous insult.

Who are the Ahbash?

Al-Ahbash ("the Ethiopians") Movement, also known as the Association of Islamic Charitable Projects, is a movement based in Lebanon, yet ironically founded by an Ethiopian shaykh, now deceased, by the name of 'Abdullah ibn Muhammad ibn Yusuf al-Harari al-Shi'bi al-Abdari, also known as al-Habashi (the Arabic word "ahbash" is the plural of the word "habashi"). It is a movement that devoutly follows the teachings of the late shaykh. By the late 1980s, al-Ahbash had become one of Lebanon's largest Islamic movements. Al-Ahbash became a key player in Lebanese politics attracting a wide following among the Sunni urban middle class by advocating pluralism and tolerance. Al-Ahbash established branches in Australia, Canada, Denmark, France, Sweden, Switzerland, the Ukraine, and the United States.

